አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3554 | ቅዳሜ ታህሳስ 25 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




# የምሁራንን አርበኝነት የሚሻው ሀገራዊ ጉዳይ

## “ምሁራን መፍትሔ አሳሽ መሆን አለባቸው”

**የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ድ/ር)**



ፎቶ- ከገፀ ድር

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 75ኛ ዓመት የምስረታ በዓልን በማስመልከት በተዘጋጀው መድረክ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርበዋል

**በሳህሉ ብርሃኑ**

ኢትዮጵያ ያለፈ ታሪኳ ከባህር በር ጋር የተቆራኘ፣ የነገ ተስፋዋ ደግሞ ከአድማስ ባሻገር ካለው ሰማያዊው መንገድ ጋር የተሳሰረ ስለመሆኑ ብዙዎች ይስማማሉ። የታሪክ አጋጣሚዎችና ፖለቲካዊ ውሳኔዎች ገፍትረው ከባህር ዳርቻ አርቀዋት የሌሎች ሀገራት ጥገኛ አድርጓት እንጂ ኢትዮጵያ ለዘመናት የባህር በር ባለቤት ሆና መቆየቷን ታሪካዊ ድርሳናት ይመሰክራሉ፡፡

ዛሬ ላይ ግን የባህር በር ጥያቄ ቅንጦት ፍለጋ ሳይሆን የህልውና ጉዳይ ሆኖ ከኢትዮጵያውያን ፊት ተደቅኗል። ከ120 ሚሊዮን በላይ ህዝብ የሚኖርባት ሀገር የባህር በር አልባ መሆኗ፣ የነገው ትውልድ የሚሸከመውን የታሪክ ዕዳ ከባድ ያደርገዋል። ይህ ችግር ከመድረሱ በፊት አሁን እንቅስቃሴ ተጀምሯል፤ በዚህ ታሪካዊ አጋጣሚ የሁሉም ዜጋ በተለይም ደግሞ የምሁራን ብዕርና አዕምሮ ያስፈልጋል።

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

### በራስ አቅም የሚተገበር የስራ ላይ ልምምድ

16



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

በመንግስት በጀት እየተተገበረ ባለው ብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ ተሳታፊ ወጣቶች

### ልጆች፤ ስለ ገና ጨዋታ ምን ያህል ታውቃላችሁ?

17



ግራፊክስ ከፋይል

የገና ጨዋታ ከፊል ገፅታ

### የበዓላቱ ተጨማሪ ድምቀቶች

15



ፎቶ- ከፋይል

ለመዝናኛነት ተመራጭ እየሆኑ ከመጡት መካከል ፋውንቴን ተጠቃሽ ነው

# ከበዓላት ባሻገር

## “መረዳዳት ባህል ሆኖ እንዲቀጥል መስራት ይገባል”

**የሶሻል አንትሮፖሎጂ መምህርና ተመራማሪ ገብሬ ይንቲሶ (ፕ/ር)**

**በስንታየሁ ምትኩ**

በኢትዮጵያ ‘መስጠት አያጎድልም’፤ ‘ያለውን የሰጠ ንፉግ አይባልም’ የሚሉ በማህበረሰቡ ዘንድ ስጦታ ማበርከትን፣ መደጋገፍንና በጎ ማድረግን የሚያበረታቱ አባባሎች አሉ። በሀይማኖታዊ አስተምሕሮውም ስጦታ ወይም መስጠት ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው መልካም ተግባር ነው፡፡

ያለንበት ወቅት ደግሞ በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት (የገና በዓል) የሚከበርበት ነው። የገናን በዓል ስናነሳ ደግሞ ዋነኛ መለያው

ወደ ገጽ 5 ዞሯል



ፎቶ- ከፋይል

የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ድጋፍ ለሚሹ ወገኖች ማዕድ ሲያጋሩ

# መንገድ ያገናኛቸው ፈላጊ እና ተፈላጊ

- **የመንገድ መሰረተ ልማት መሟላቱ ያሻቸውን ያህል ምርት እንዲሸምቱ እድል እንደሰጣቸው ተጠቃሚዎች ገልጸዋል**

**በፋንታነሽ ተፈራ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኑሮ ውድነትንና የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት በከተማዋ የመግቢያ በሮች የግብርና ምርቶች ማከፋፈያ የገበያ ማዕከላትን ገንብቶ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ እያደረገ ይገኛል፡፡ የገበያ ማዕከላቱ በዋናነት በግብይት ሰንሰለቱ ውስጥ የሚታየውን የደላላ ጣልቃገብነት ለማስቀረት እና ወደ ከተማዋ የሚገባውን ምርት በመጠንና በጥራት

ወደ ገጽ 13 ዞሯል



# ርዕሰ አንቀፅ



## የመደጋገፍ ባህላችን ተጠናክሮ ይቀጥል!

ኢትዮጵያውያን ለዘመናት በደስታና በሐዘን ጊዜያት አብሮነትንና መረዳዳትን እንደ ትልቅ ማኅበራዊ ሀብት ገንብተናል። ‘ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል’ የሚለው የቆየ አባባላችን፣ ማኅበረሰቡ እርስ በእርሱ እንዲደጋገፍና እንዳይገፋፋ አድርጎታል ማለት ይቻላል። መረዳዳት በባህላችን ውስጥ እንደ ግዴታ ሳይሆን እንደ ሰብዓዊ ክብርና እንደ መንፈሳዊ ግዴታ ተቆጥሮ ለትውልድ ሲተላለፍ የቆየ እሴታችን ነው። ይህ እሴት አሁንም በከተማችን ውስጥ እንደ አዲስ እየታደሰና እየለመለመ ይገኛል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መረዳዳትንና በጎነትን የመንግሥታዊ ተግባራት አንዱ አካል አድርጎ በመቅረጽ፣ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ተስፋ የሚሰጡ ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል። በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ መደጋገፍ የቃላት ድርደራ ሳይሆን በተግባር የሚታይ ውጤት ሆኗል። መረዳዳትና መደጋገፍ ከችግር መውጫ መንገዳችን ብቻ ሳይሆን፣ እኛነታችንን የምንገልጽበት መለያችን ነው፡፡ ይህ ተግባር የከተማዋን ነዋሪዎች በማስተሳሰር ረገድ ትልቅ ፋይዳ እያበረከተ ይገኛል።

በተለይም በበዓላት ወቅት በኢኮኖሚ አቅማቸው ዝቅተኛ የሆኑ ወገኖቻችን በዓሉን ተደስተው እንዲያሳልፉ ማድረግ ላይ ብርቱ ጥረት እየተደረገ ነው። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየበዓላቱ የሚከውነው የማዕድ ማጋራት፣ የቤት ዕድሳትና የተለያዩ የበዓል መዋያ ቁሳቁሶችን የመለገስ ተግባር ‘ለብቻ መብላት ለብቻ መሞት ነው’ የሚለውን ሀገራዊ አባባል በመቀየር ‘አለንላችሁ’ የሚል ጥልቅ ወገንተኝነትን እያሳየ ይገኛል። ፍቅር የሚገለጸው በማካፈል ነው፤ እኛ ስንሰጥ ለሌላው ብቻ ሳይሆን ለራሳችንም ሰላምና ደስታን እንሰጣለን፡፡

ይሁን እንጂ መረዳዳት የመንግሥትና የጥቂት በጎ አድራጊዎች ብቻ ተግባር ሆኖ መቅረት የለበትም። ባለሀብቱንና ወጣቱን ጨምሮ እያንዳንዱ የከተማዋ ነዋሪ ይህንን የቆየ ባህላችንን ወደ የዕለት ተዕለት ተግባሩ ሊቀይረው ይገባል። ከጎናችን ያለውን ጎረቤታችንን ማየት፣ የተራበውን ማብላትና የተቸገረውን ማገዝ የታላቅነት መገለጫ ነው። ይህ መደጋገፍ በስፋትና በተደራጀ መልኩ በማኅበረሰቡ ውስጥ ስር ሲሰድ፣ ማኅበራዊ ፍትሕን ከማስፈኑ ባለፈ፣ የከተማዋን ሰላምና ልማት በጽኑ መሠረት ላይ ለመገንባት ያስችለናል።

አሁን የተጀመረውና በመንግሥት ደረጃ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው የበጎነት ሥራ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት። በዓላት ሲመጡ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ጊዜያት እጃችን ለበጎነት መዘርጋት ይኖርበታል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እያከናወነ ያለው የሚደነቅ ተግባር በህዝባዊ ንቅናቄ ታጅቦ ሲቀጥል፣ በከተማችን ውስጥ የትኛውም ወገን “ብቻዬን ነኝ” የሚል ስሜት እንዳይሰማው ያደርጋል። የወደፊት አዲስ አበባችንን በውብ ሕንፃዎች እና መሰል መሰረተ ልማት ስራዎቿ ብቻም ሳይሆን፣ በመተሳሰብና በፍቅር በሚገነባ ጠንካራ ማኅበራዊ ግንብ ልናስውባት ይገባል።

# የእኔ እይታ

**ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።**

## ውሃ ሲወስድ አሳስቆ እንዳይሆን!

**በሰናይ ምግባሩ**

በህይወት ዑደት ውስጥ ነገሮችን የምናይበት፣ የምንረዳበት አለፍ ሲልም የምንጠቀምበት መንገድ ማስተዋል የታከለበት ሊሆን ይገባዋል። የአንድን ነገር ሂደቱን ብቻም ሳይሆን መዳረሻውን እና የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ጭምር ሚዛን ላይ አስቀምጦ ማየት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ የማህበራዊ ትስስር ገፆች አጠቃቀማችንን ለአብነት ማንሳት ወደድኩ፡፡

አሁን ያለው የቴክኖሎጂ ዘመን ግለሰቦችን ጭምር የሚዲያ ባለቤት አድርጓል፡፡ ማንም ሰው ስልኩን በመጠቀም መረጃዎችን ማሰራጨት የሚችልበት ደረጃ ላይ ደርሶል፡፡ ይህ መሆኑ ጊዜው ግድ የሚለው ብቻም ሳይሆን በአግባቡ ከተጠቀምንበት ገንቢ የሆነ አስተዋጽኦ ስላለው በደምሳሳው ጉዳት አለው ብሎ መፈረጅ አይቻልም። ስልካችንን በመጠቀም ለፈጠራ ስራ የሚያግዙ፣ አንድን ርዕሰ ጉዳይ በጥልቀት ለመረዳትም የሚያስችሉ እና መሰል መልካም ነገሮችን እንድናከናውን በማድረግ ረገድ ሚናቸው አይተኬ ነው፡፡ በተቃራኒው ሲሆን ደግሞ ጥፋቱ በዚያው ልክ ነው፡፡

የማህበራዊ ትስስር ገጾች ላይ የምናስተላልፋቸው መልዕክቶች ምን ያህል የሀገርን ህልውና አደጋ ላይ የማይጥሉ ናቸው? ምን ያህል ኢትዮጵያዊ አንድነትን የማይሸረሽሩ ናቸው? ምን ያህል ከትውልድ ወደ ትውልድ ሊተላለፉ የሚችሉ አኩሪ እሴቶቻችንን ያከበሩ ናቸው? የሚለውን ለአፍታ ቆም ብለን ራሳችንን መጠየቅ፣ ከቤተሰቦቻችንና ጎደኞቻችን ጋር ሀሳብ መለዋወጥ ግድ ይለናል ባይ ነኝ፡፡

አንዳንድ ጅምሮቻችን ደስ የሚሉ አይደሉም፡፡ ለሀገር፣ ለትውልድ፣ ለእሴቶቻችን የሚቆረቆሩ ሰዎች “ውሃ ሲወስድ አሳስቆ” እንዲሉ ከአሁኑ አንድ በሉት የሚል ውትወታ እና ጩኸት ጀምረዋል፡፡ መንግስትም አስተማሪ የሆነ እርምጃ መውሰድ ጀምሯል፡፡ ነገር ግን በቂ አይደለም። እያንዳንዳችን በዚህ ላይ አይተኬ ሚናችንን በኃላፊነት ስሜት መወጣት መቻል አለብን፡፡

ተግሳጹ እና ምክሩን ከራሳችን፣ ከጎደኞቻችን መጀመር መቻል አለብን። የሚተላለፉ ይዘቶች በጥንቃቄ መሆን እንዳለባቸው ሀሳብ መለዋወጥ አለብን፡፡ ብዙ ተከታይ ለማግኘት፣ አለፍ ሲልም ገንዘብ ለመስራት ሲባል ኃላፊነት በጎደለው መልኩ መንቀሳቀስ ጉዳቱ ለራስም፣ ለቤተሰብም፣ ለማህበረሰብም፣ ለሀገርም ነው፡፡ “እኔ ከዚህ አይነት የተዛባ እና የተሳሳተ መልዕክት ከማስተላለፍ ተቆጥቤለሁ ወይ?” ብለን እንጠይቅ፣ ክፍተትም ካለ እናርም፡፡ ምክንያቱም የሰውን ጉድፍ ለማውጣት ከመሞከር በፊት የራስን ማስቀደም ስለሚያስፈልግ። ከዚህ በተጨማሪም የማይበጅ መልዕክት የሚያስተላልፉ ጎደኞቻችንን ቆም ብለው ራሳቸውን እንዲያዩ የበኩላችንን አዎንታዊ አስተዋጽኦ መጫዎት ይጠበቅብናል፡፡ “ውሃ ሲወስድ አሳስቆ” እንደሚባለው አሁን በጥቂቱም ቢሆን እያስተዋልን ያለነው ተገቢ ያልሆነ ድርጊት በእንጭጩ ካልተቀጨ ሀገር እስከማፍረስ ሊደርስ እንደሚችል መገንዘብ አለብን ብዬ አስባለሁ፡፡ የእናንተስ እይታ ምን ይሆን?

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች**

**ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ**

**ግንቦት 1985 ዓ.ም ተመሰረተች**

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜልባ ፕሪንቲንግ ፐብሊሺንግ ኤንድ ፓኬጂንግ ሼር ካምፓኒ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ለይላ መሀመድ
ይግለጡ ጓዴ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ
ፋንታነሽ ተፈራ

**ዋና አዘጋጅ**
ምህረቱ ፈቃደ
Mehretu@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 34/55

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# የምሁራንን... ከገጽ 1 የዞረ

ምሁራን የታሪክን ጠባሳ መርምረው፣ የሕግና የዲፕሎማሲውን አቀበት አስተካክለው፣ በሰላማዊና በፍትሐዊ መንገድ ሰማያዊውን በሯን የምታንኳኳበትን የዕውቀት ካርታ የመንደፍ ታሪካዊ አደራ ወድቆባቸዋል። ይህ ጽሑፍም ኢትዮጵያ ከባህር ጋር ያላትን የቆየ ቁርኝትና ይህንኑ ታሪካዊ ግንኙነት ዳግም ለማጣመር ምሁራን ሊጫወቱት የሚገባውን ወሳኝ ሚና ይፈትሻል። አስቀድመን ግን አንዳንድ ምሁራንና ጥናታዊ ጽሑፎቻቸውን በዋቢነት በመጥቀስ ምሁራን የአንድን ሀገር ብሔራዊ ጥቅም በማስጠበቁ ረገድ ሊወጡት ስለሚገባው ኃላፊነት መረጃዎችን እንጥቀስ፡፡




የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 75ኛ ዓመት የምስረታ በዓልን በማስመልከት የተዘጋጀው የውይይት መድረክ ተሳታፊዎች

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 75ኛ ዓመት የምሥረታ በዓልን ምክንያት በማድረግ "የምሁራን ሚና ለሀገራዊ ብልጽግና" በሚል ርዕስ የጥናታዊ ጽሑፍ ያቀረቡት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፣ ለሀገር ዕድገት ከምሁራን ጠንካራ ተሳትፎ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል። ጉዳዩን ሲያብራሩም፣ "ሀሳብ የለውጥ ኃይል ነው። ምሁራን ደግሞ የለውጥ ወኪሎች ናቸው። ምሁራን በማኅበረሰብ ውስጥ የሚፈጥሩት ለውጥም ሀገርን ወደ ብልጽግና ይወስዳል።" ብለዋል፡፡

ምሁራን ችግር ፈቺና መፍትሔ አሳሽ መሆን ይጠበቅባቸዋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፣ ምሁራን በስሜታዊነት የሚነዱ ሳይሆኑ ሀሳብ አክባሪና አፍቃሪ፣ ጥልቅ አሰላሳይ፣ አንባቢ፣ ችግር ፈቺና መፍትሔ አሳሽ መሆን እንዳለባቸውም አሳስበዋል፡፡

የኢትዮጵያ ምሁራን በሁለንተናዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ሚና በሚመለከት ሰፊ ውይይት የተካሄደ ሲሆን፣ የመደመር መንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሀገራዊ የብልጽግና ጉዞ ላይ አይተኬ ሚና እንዳላቸው በጽኑ ያምናል፣ ለተግባራዊነቱም እየሰራ ይገኛል በማለት ገልፀዋል ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)።

አያይዘውም ተቋማቱም የመማር ማስተማር እንዲሁም የምርምር ስራዎችን ከቴክኖሎጂ ጋር በማናበብ ወደ ፈጠራና ተግባር መለወጥ ይጠበቅባቸዋል። ይህም የኢትዮጵያን ብልጽግና በተደመረ አቅም ለማፋጠን ሚናው ከፍተኛ ስለመሆኑ አውስተዋል።

ምሁራን በዕውቀታቸውና በምርምር አቅማቸው የህብረተሰቡ አንቂ ተደርገው ይወሰዳሉ። በተለይ በአዳጊ ሀገራት ምሁራን የረጅም ጊዜ ስትራቴጂዎችን በመንደፍ የሀገር ግንባታ ዋና ተዋናይ መሆን እንዳለባቸውም 'Bridge Builders: The Role of Intellectuals in Developing Countries' የተሰኘው ጥናታዊ ጽሑፍ ላይ ሰፍሯል፡፡ በአንድ ሀገር የፖሊሲ ቀረጻ እና ስትራቴጂክ ውሳኔዎች ውስጥ የምሁራን ተሳትፎ አለመኖር ደግሞ በተቃራኒው ሀገሪቱን ለስሜታዊ እና ለጊዜያዊ ውሳኔዎች ተጋላጭ ያደርጋታል። ምሁራን የረጅም ጊዜ ስትራቴጂዎችን በመንደፍ፣ ሳይንሳዊ መረጃን መሠረት ያደረጉ የፖሊሲ ምክረ-ሀሳቦችን የማቅረብ ኃላፊነት አለባቸው። እንደዚሁም የተወሳሰቡ ዓለም አቀፍ ሁኔታዎችን በመተንተን ሀገሪቱ ልትከተለው የሚገባውን ዲፕሎማሲያዊ መስመር በማመላከት ረገድም ያላቸው ድርሻ ቀላል እንዳልሆነ በጥናታዊ ጽሑፍ ቀርቧል።

አሜሪካዊው የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር ስቴፈን ክራስነር "Defending the National Interest" በሚለው መጽሐፋቸው፣ ብሔራዊ ጥቅም የአጭር ጊዜ የፖለቲካ ፍላጎት ሳይሆን የረጅም ጊዜ የሀገር ህልውና መሆኑን ይገልጻሉ። ምሁራን በመንግስት መዋቅር ውስጥ ሆነውም ሆነ በገለልተኛነት፣ ከቡድን ጥቅም ይልቅ ለሀገር ዘላቂ ጥቅም ቅድሚያ የሚሰጡ ፖሊሲዎችን የመቅረጽ ሚና እንዳላቸውም አመላክተዋል።

ብሔራዊ ጥቅም የሚጠበቀው በወታደራዊ ኃይል ብቻ ሳይሆን በባህል፣ በእሴቶች እና በዲፕሎማሲም ጭምር እንደሆነ ሳይንቲስቱ አመላክተዋል። አክለውም፣ ምሁራን ደግሞ የአንድን ሀገር ገጽታ በመገንባት፣ የባህል ተጽዕኖን በማሳደግ እና ዓለም አቀፍ ተቀባይነትን የሚያመጡ የፖሊሲ አማራጮችን በማመንጨት ረገድ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ስለመሆኑም ያብራራሉ።

ምሁራን በታሪክ፣ በጂኦ-ፖለቲካ እና በኢኮኖሚክስ ያላቸውን ዕውቀት በመጠቀም ሊመጡ የሚችሉ የውስጥ እና የውጭ ስጋቶችን አስቀድሞ የመተንበይ እና ለአደጋዎች የመፍትሔ አቅጣጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የምሁራን ኃላፊነት በዚህ ደረጃ ከፍ ያለ ከሆነ ዘንዳ ለኢትዮጵያውያን የህልውና ጉዳይ ሆኖ ከፊት ለፊታቸው የተደቀነው የባህር በር ጥያቄ ምላሽ እንዲያገኝ ምን ሊሰሩ ይገባል? የሚለው ጥያቄ ወሳኝ ስለመሆኑ እንረዳለን፡፡

የኢትዮጵያ ምሁራን የባህር በር ጥያቄ በሚያነሱበት ወቅት "መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ፤ ሂዱና ተዋጉ" የሚላቸው ሳይሆን "በጉዳዩ ዙሪያ ተባብረን እንስራ" የሚል መሪ ባለበት በዚህ ወቅት ሊወጡት የሚገባው ኃላፊነት ከፍተኛ እንደሆነ አያጠያይቅም፡፡ እዚህ ጋር ሊነሳ የሚገባው ወሳኙ ጥያቄ ታዲያ ኃላፊነታቸው ምን ይሁን? የሚለው ነው፡፡

> **"ኢትዮጵያ የባህር በር ለማግኘት እያደረገች ያለው ዲፕሎማሲያዊ እና ፖለቲካዊ ጥረት ውጤታማ እንዲሆን የሀገሪቱ ምሁራን ሚናቸው ብዙ ነው"**

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሰላምና ደህንነት መምህርና ከፍተኛ ተመራማሪው ሙሉጌታ አየለ (ዶ/ር) ለዚህ ጥያቄ ምላሽ አላቸው፡፡ እርሳቸው እንደሚሉት ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ካሉ የባህር በር አልባ ሀገራት መካከል በሕዝብ ብዛት ቀዳሚዋ ናት። ይህ ተፈጥሯዊ ጸጋ መታጣት ለኢኮኖሚ እድገት፣ ለብሔራዊ ደህንነት እና ለጂኦ-ፖለቲካዊ ተጽዕኖ ትልቅ ማነቆ ሆኖ ቆይቷል። ኢትዮጵያ የባህር በር ለማግኘት እያደረገች ያለው ዲፕሎማሲያዊ እና ፖለቲካዊ ጥረት ውጤታማ እንዲሆን የሀገሪቱ ምሁራን ሚናቸው ብዙ ነው፡፡

የአንድ ሀገር ብሔራዊ ጥቅም እንዲከበር ልዩነቶች ላይ ከመጠመድ ይልቅ አንድ በሚያደርግ አጀንዳ ላይ መስራት ያስፈልጋል የሚሉት ደግሞ የህግ ባለሙያው አቶ ኪያ ፀጋዬ ናቸው። የባህር በር ጥያቄውን አጠናክሮ መቀጠል፣ የተለያዩ አማራጮችን ማቅረብ እንደሚያስፈልግ የሚገልፁት የህግ ባለሙያው አቶ ኪያ በተለይም ምሁራን በውስጥ ያሉ ትናንሽ ችግሮችን እና ልዩነቶችን ወደ ጎን በመተው ብሔራዊ ጥቅምን ማስቀደም እንደሚገባ ያሳስባሉ።

ብዙውን ጊዜ የባህር በር ጥያቄ ከፖለቲካዊ ትርክት ጋር ብቻ ተያይዞ ይታያል። ሆኖም ምሁራን ይህ ጉዳይ ከእያንዳንዱ ዜጋ የዕለት ተዕለት ኑሮ ጋር ያለውን ትስስር ማሳየት አለባቸው። የኢኮኖሚክስ ምሁራን አንድ ምርት ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ የሚከፈለው የወደብ ኪራይ እና የሎጂስቲክስ ወጪ በሸማቹ ላይ የሚያሳድረውን ጫና በቁጥር አስደግፈው ማቅረብ አለባቸው። ለምሳሌ በየዓመቱ ለወደብ ኪራይ የሚወጣው በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር በሀገር ውስጥ ቢቀር ምን ያህል ፋብሪካዎችን መገንባት ይችል እንደነበር ማሳየት ህዝባዊ ንቃትን እንደሚፈጥር ሀሳባቸውን ያካፈሉን ምሁራን ያስረዳሉ።

የታሪክ እና የማህበራዊ ሳይንስ ምሁራን ኢትዮጵያ ከባህር ጋር የነበራትን ጥንታዊ ቁርኝት እና የወደብ ማጣት በሀገራዊ ኩራት ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ በማስተማር፣ ጉዳዩ የትውልድ ጥያቄ መሆኑን ማስረፅ ይኖርባቸዋል። በመገናኛ ብዙሃን እና በትምህርት ተቋማት አማካኝነት ህዝቡ ስለ ሀገሩ ጥቅም ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖረው ማድረግ አለባቸው። ይህም ህዝቡ በስሜት ሳይሆን በእውቀት ላይ ተመስርቶ ሀገራዊ ጉዳዮችን እንዲደግፍ ወይም እንዲሞግት ይረዳል ይላሉ ሙሉጌታ (ዶ/ር)።

በእርግጥም ምሁራን ችግር ተናጋሪ ብቻ ሳይሆኑ መፍትሔ አመላካች መሆን አለባቸው። ለዚህም ከጎረቤት ሀገራት ጋር በምን አይነት የኢኮኖሚ ውህደት ወይም የጋራ ልማት ስምምነት የባህር በር ማግኘት እንደሚቻል የፖሊሲ አማራጮችን ማመንጨት አለባቸው። የባህር በር ከመገኘቱ በፊትና በኋላ ሊኖር ስለሚገባው የባህር ኃይል ዝግጁነት፣ የባህር ላይ ደህንነት እና የንግድ መርከቦች አስተዳደር ምሁራን የቅድመ ዝግጅት ጥናቶችን ማቅረብ እንደሚጠበቅባቸውም አስተያየት ሰጪዎቹ ያስረዳሉ።

በሌላም በኩል የኢትዮጵያ የባህር በር የማግኘት ጥረት እንዲሳካ ምሁራን ከፖለቲካዊ ወገንተኝነት ነፃ በሆነ መልኩ ለሀገር ጥቅም ቅድሚያ መስጠት ያለባቸው ሲሆን፣ መንግስትን በበሰለ ሀሳብና ጥናት የማማከር፣ ህዝቡን በሳይንሳዊ መረጃ ማንቃት እና ዓለም አቀፉን ማህበረሰብ በዲፕሎማሲያዊ ጽሑፎች ማሳመን የምሁራኑ ኃላፊነት ስለመሆኑ አብራርተዋል የሰላምና ደህንነት ከፍተኛ መምህርና ተመራማሪው ሙሉጌታ አየለ (ዶ/ር)። ይህ ሲሆን የባህር በር የማግኘት ጥረቱ ከፍላጎት አልፎ ወደ ተግባራዊ ስኬት ሊቀየር የሚችልበትና ምሁራንም ታሪክ የሰጣቸውን አደራ ተወጥተዋል ማለት ይቻላል፡፡

በዓለም ላይ ወታደራዊና ስትራቴጂካዊ ቦታዎችን ለመቆጣጠር እየተደረገ ያለው ሽኩቻ ከፍተኛ ነው፡፡ የቀጣናው የፀጥታ ሁኔታ ድንገት ቢደፈርስ ችግር ውስጥ የሚገባው የወጪ ገቢ ንግድ ስርዓቱ ብቻ ሳይሆን የሀገሪቱ ደህንነት ጭምር ነው፡፡ "አንዳንድ ሀገራት ብዙ ኪሎ ሜትሮችን አቋርጠው መጥተው እኛ አፍንጫችን ላይ ባለ ነገር የበይ ተመልካች መሆን አይገባንም" የሚሉት ሙሉጌታ (ዶ/ር)፣ የባህር በር ጉዳይ ሸቀጥ ከማስገባትና ማስወጣ የተሻገረ የደህንነት ጉዳይ ስለመሆኑ በማስረዳት ህዝቡን ማንቃት የምሁራኑ ኃላፊነት ነው ይላሉ፡፡

ሙሉጌታ (ዶ/ር) በማጠቃለያ ሀሳባቸው ምሁራን ፈርጀ ብዙ ሚና እንዳላቸውና በአንድ በኩል እንደ ዜጋ የሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እንደሚመለከታቸው ገልፀው፣ በሌላም በኩል የሞራልና የህግ ግዴታ እንዳለባቸው አፅንኦት ሰጥተዋል። ምሁራን ሊያደርጓቸው ይገባል ያሏቸውንም ጉዳዮች ጨምረው ሲገልፁ፣ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ላይ ቀርበው መሞገት፣ እውነታቸውን ማስረዳት፣ የመጻፍና ጥናት ማድረግ፣ ኮንፈረንሶችን ማዘጋጀት፣ ሳይንሳዊ ሙግት ማቅረብም ይኖርባቸዋል ብለዋል፡፡

አያይዘውም የተለያየ ቋንቋ የሚናገሩ ምሁራን ዓለም አቀፋዊ መገናኛ ብዙሃን ላይ ቀርበው ወደብ ያለውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በተጨባጭ ማስረጃዎች አስደግፈው ማስረዳት እንዳለባቸውና በግለሰባዊ ብቻ ሳይሆን በተቋም ደረጃም ተደራጅቶ መስራት እንደሚገባም ይመክራሉ፡፡

ሰሞኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጌዲዮን ጢሞቴዎስ (ዶ/ር) የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባካሄደው የ5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 6ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ቀርበው እንደገለፁትም የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ የውስጥ ልዩነቶችን የሚሻገር የትውልድ ጥያቄ ነው ብለዋል። አያይዘውም ኢትዮጵያ ያቀረበችው የባህር በር ጥያቄ የመንግሥት ወይም የአንድ ፓርቲ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን ትውልድ ተሻጋሪ ግብ ያለው የትውልድ ጥያቄ እንደሆነ ገልጸዋል።

# በባዛሮች የሚከናወነው ሸመታ ምን መልክ አለው?

- **በአዲስ አበባ ከተማ የገና በዓልን ምክንያት በማድረግ በቂ የምርት አቅርቦት እንዲኖር በትኩረት መሰራቱ ተጠቁሟል**

**በሸዋርካብሽ ቦጋለ**

ባዛሮች ለኢኮኖሚ ዕድገት ያላቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፤ ሰፊ የንግድ ልውውጥ የሚካሄድባቸው የኢኮኖሚ ሞተሮች ተደርገውም ይታሰባሉ። የስራ ዕድል መፍጠር፣ ለአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች የንግድ መድረክ ማመቻቸት፣ የሸቀጦና አገልግሎቶች ዝውውርን ማፋጠን፣ የቱሪዝም መስህብ በመሆን የውጭ ምንዛሬ ማመንጭት ከብዙ የባዛር ጥቅሞች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

ከሁሉ በላይ ባዛሮች ሸቀጦች በተመጣጣኝ ዋጋ፣ በበቂ መጠንና በጥራት የሚገኙባቸው ስፍራዎች መሆናቸው ተመራጭ የገበያ ስፍራ ያደርጋቸዋል፤ በተጨማሪም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን በማፋጠን፣ ድህነትን በመቀነስ እና የንግድ ትስስርን በማጠናከር ረገድም የማይተካ ሚና አላቸው። ባዛሮች በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብም ያንቀሳቅሳሉ፡፡

በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ዙሪያ የተለያዩ ጥናታዊ ፅሑፎችን የሚያስነብበው 'ኢኮንስቶር' (econstor) ገፀ ድር የባዛሮች ኢኮኖሚያዊ ድርሻ (Economic Role of Bazaars) በሚል ርዕስ ባወጣው መረጃ እ.ኤ.አ ከ2024 እስከ 2025 ባለው ጊዜ፣ የባዛሮች አካል የሆነው የዓለም የችርቻሮ ንግድ ድርሻ (Retail Market) ከ30 ትሪሊዮን ዶላር በላይ እንደሚደርስ አስፍሯል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ከ2 ቢሊዮን በላይ ሰዎች መደበኛ ባልሆነው የንግድ ዘርፍ ውስጥ እንደሚገበያዩ የሚያትተው የ'ኢኮንስቶር' መረጃ፣ ባዛሮች የዚህ ዘርፍ ማዕከል እንደሆኑና በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት፣ ዘርፉ ከሀገራቱ አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት (GDP) ውስጥ እስከ 30 በመቶ የሚሆነውን ድርሻ እንደሚይዝ ያመላክታል፡፡ ይህ ማለት በቢሊዮን የሚቆጠሩ ዶላሮች በየቀኑ በእነዚህ ገበያዎች ውስጥ ይሽከረከራሉ እንደማለት ነውም ይላል።

በቱርክዬዋ ከተማ በኢስታንቡል ውስጥ የሚገኘው ግራንድ ባዛር የዓለማችን ትልቁ የባዛር ገበያ ሲሆን፣ በዓመት ከ90 ሚሊዮን በላይ ጎብኚዎችን ያስተናግዳል። በቀን በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር ያንቀሳቅሳል። የመካከለኛው ምስራቅ እና የሰሜን አፍሪካ ሀገራትም ትልልቅ ባዛሮች እንዳሏቸውና በዚህም ሸማቾቻቸው፣ ነጋዴዎቻቸውና ሀገራቱም ተጠቃሚዎች ስለመሆናቸው መረጃው ያትታል፡፡

አሁን አሁን የባዛር ግብይት በኢትዮጵያም እየተለመደ መጥቷል፡፡ በተለይ በበዓላት ሰሞን የባዛር ሁነቶች በስፋት ይታያሉ፤ ግብይቱም በዚያው ልክ ይጧጧፋል፡፡ ኃይማኖታዊ፣ ባህላዊ በዓላት በሚከበሩባቸው ወቅቶች የምርት እጥረትና ያልተገባ የዋጋ ጭማሪ እንዳያጋጥም ባዛሮች ይሰናዳሉ፡፡ በሸማቾች ላይ ሊደርስ የሚችልን የኑሮ ጫና ለመከላከል መንግስት፣ የሸማችና የአምራች ማህበራት እንዲሁም የንግዱ ማህበረሰብ ተናብበው የሚሰሩባቸው የባዛርና ኤግዚብሺን መድረኮች በስፋት ይዘጋጃሉ፡፡







ፎቶ- ከገፀ ድር

የባዛር ሁነቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ በቁጥር እየበዙና አገልግሎታቸውም እየዘመነ መጥቷል

**"በከተማዋ የገና በዓልን ምክንያት በማድረግ 633 ሺህ 400 ዶሮ፣ 15 ሚሊዮን እንቁላል፣ 90 ሺህ 294 ኩንታል የሰብል ምርቶች እንዲሁም 416 ሺህ 205 ኩንታል አትክልትና ፍራፍሬ ለገበያ ቀርቧል"**

መጪውን የገና በዓል አስመልክቶ በአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ አካባቢዎች የኢንዱስትሪና የግብርና ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርቡባቸው የገና ኤግዚቢሽንና ባዛር ዝግጅቶች በመካሄድ ላይ ይገኛሉ፡፡ እንደ ክፍለ ከተማ ከተዘጋጁ የገና ባዛርና ኤግዚቢሽን መድረኮች መካከል በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የተዘጋጀው ባዛር አንዱ ነው፡፡ በስፍራው ተገኝተን ባደረግነው ቅኝት የሞቀ የንግድ ልውውጥ ሲደረግ አስተውለናል፡፡

አጣና ተራ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በተዘጋጀው በዚህ ባዛር ሽንኩርት፣ ዘይት፣ እንቁላል፣ ዶሮ እና ሌሎች የግብርና ምርቶች በስፋት ቀርበዋል። ጫማና አልባሳትን ጨምሮ ሌሎች የኢንዱስትሪ ውጤቶችም እንዲሁ በየፈርጁ ተዘጋጅተዋል፡፡

በባዛሩ ግብይት ሲፈፅሙ ያገኘናቸው ወይዘሮ ወሰን ታደሰ የተባሉ የአካባቢው ነዋሪ በበዓላት ሰሞን በሚዘጋጁ ባዛሮች እየተገኙ ሸመታ የማድረግ ልምድና ፍላጎት እዳላቸው ጠቁመው፣ ይህም እንዲህ ባሉት የገበያ ስፍራዎች ምርቶች በበቂ መጠን፣ ጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ የሚገኙ በመሆኑ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

አቶ ዳዊት በርሄ የተባሉ የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ነዋሪ በበኩላቸው በባዛሩ አልባሳት፣ የስጦታ እቃዎች፣ የምግብና መጠጥ ምርቶች፣ የቤት ዕቃዎች በአጠቃላይ ከበዓል ጋር ተያይዞ የሚሸመቱ ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ እንደሚቀርቡ ጠቁመው፣ በንፅፅር ከሌሎች የገበያ ስፍራዎች ባነሰ ዋጋ የሚፈልጓቸውን ምርቶች መሸመታቸውን ገልፀዋል፡፡

እንደ አቶ ዳዊት ገለፃ፣ ባዛሮች ከአቅርቦት አኳያ በጣም ጥሩ የሚባሉ ናቸው፡፡ ለበዓልም ሆነ ለእለታዊ ፍጆታ የሚፈለጉ ምርቶችን የማግኘት ዕድል ይሰጣሉ፡፡ ለትራንስፖርት የሚወጣ ወጪን በማስቀረት ብሎም ጊዜንና ገንዘብን በመቆጠብ ረገድም አጋዥ ናቸው፡፡

የገና በዓልን አስመልክቶ በተዘጋጀው ባዛር ላይ የቀረቡ ምርቶች በአካባቢያቸው ካለው ዋጋ አንፃር ተመጣጣኝና በአቅማቸው መሸመት የቻሉበት እንደሆነ ጠቁመው፣ ከዘይት ጀምሮ ሌሎች ማጣፈጫዎችና የልጆች አልባሳትን በተሻለ ዋጋ መግዛታቸውን ገልፀዋል፡፡

የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ንግድ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ አብዱልዋህድ በድሩ የበዓል ሰሞንን አስመልክቶ የምርት እጥረት እንዲሁም የዋጋ ንረት እንዳይከሰት የባዛሮች መዘጋጀት ወሳኝ እንደሆነ ገልፀው፣ አንደ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማም በሁለት ቦታዎች የገና ባዛር መዘጋጀቱን አስታውቀዋል፡፡

ባዛሮቹ የክፍለ ከተማው ነዋሪዎች ለበዓል የሚያስፈልጋቸውን የፍጆታ እቃዎች ያለምንም እንግልት በተመጣጣኝ ዋጋ በቅርበት እንዲያገኙ ከማድረግ ባለፈ በህገ ወጥና ስግብግብ ነጋዴዎች እንዳይበዘበዙ በማድረግ ረገድ አይነተኛ ድርሻ እንዳላቸውም ገልፀዋል፡፡

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በተለምዶ አጣና ተራ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ በተዘጋጀው ባዛር አስራ አምስት የሸማች ማህበራት፣ አንድ ዩኒየን፣ በግል የተደራጁ ኢንተር ፕራይዞች እና ሌሎች የንግዱ ማህበረሰብ ተሳታፊ መሆናቸውንም ጠቁመዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሃቢባ ሲራጅ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ የገና በዓልን ምክንያት በማድረግ የምርት እጥረትና የዋጋ ንረት እንዳይከሰት አስፈላጊው ዝግጅት ተደርጓል ብለዋል፡፡

ለበዓሉ የሚያስፈልጉ የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶች በበቂ መጠን በባዛሮች፣ በመንግስት የገበያ ማዕከላት እንዲሁም በቅዳሜና እሁድ ገበያዎች ለከተማዋ ነዋሪዎች በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርቡ ሰፊ ስራዎች መሰራታቸውን ተናግረዋል፡፡

የምርት አቅርቦት ዝግጅቱ ሁሉንም የፍጆታ ምርቶች ያካተተ ሲሆን፣ በዓሉን ምክንያት በማድረግ ተፈላጊነታቸው የሚጨምሩ እንደ እንቁላል፣ ዶሮ፣ የዳልጋ ከብት፣ በግና ፍየል የመሳሰሉት ላይ ልዩ ትኩረት ተደርጓል ብለዋል፡፡

ምርቶቹ ከመደበኛ ገበያዎች በተጨማሪ በንግድ ቢሮ፣ ህብረት ስራ ኮሚሽን፣ አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን፣ ኢንዱስትሪ ቢሮ እና አዲስ አበባ ንግድ ስራች ድርጅት አስተባባሪነት በሚካሄዱ ባዛሮችና የግብይት መዳረሻዎች እንደሚቀርቡ ቢሮ ኃላፊዋ ሳይጠቅሱ አላለፉም፡፡

እንደ ቢሮ ኃላፊዋ ማብራሪያ፣ በአዲስ አበባ ከተማ የገና በዓልን ምክንያት በማድረግ 279 ሺህ 620 የዳልጋ ከብቶች እንዲሁም 294 ሺህ 620 በግና ፍየል በካራ አሎ፣ በአቃቂ፣ በብርጭቆ፣ በቄራና በሸጎሌ የቁም እንስሳት የገበያ ማዕከላት ለግብይት ቀርበዋል፡፡

በተጨማሪም 633 ሺህ 400 ዶሮ፣ 15 ሚሊዮን እንቁላል፣ 90 ሺህ 294 ኩንታል የሰብል ምርቶች እንዲሁም 416 ሺህ 205 ኩንታል የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች በግብይት ማዕከላቱ መቅረቡን አስረድተዋል፡፡

ህብረተሰቡ ለበዓሉ የቀረቡ ምርቶችን በአቅራቢያው በተዘጋጁ ባዛሮች፣ በመንግስት፣ የገበያ ማዕከላት እንዲሁም በቅዳሜና እሁድ ገበያዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ግብይት እንዲፈፅም ጥሪ አቅርበዋል። አክለውም ህብረተሰቡ በበዓል ግብይ ወቅት ህገ ወጥ ግብይትና የዋጋ ጭማሪ ካጋጠመው በቢሮው ነፃ የስልክ መስመር 8885 ላይ በመደወል ጥቆማ በመስጠት ህገ ወጥነትን እንዲከላከል ጥሪ አቅርበዋል።

በበዓላት ወቅት የሚዘጋጁ ባዛሮችና ኤግዚቢሽኖች ለሸማቹ ማህበረሰብ ብቻም ሳይሆን ለነጋዴውም የተሻለ ገቢ ለማግኘትና አዳዲስ ደንበኞችን ለማፍራት መንገድ የሚከፍቱ እንደሆኑ ተጠቁሟል።

## ከበዓላት... ከገጽ 1 የዞረ

ስጦታ ማበርከት ነው፡፡ የእምነቱ አባቶች አስተምህሮ እንደሚያሳየው፣ የገና በዓል አንድም የሰው ልጅ ህግን በመተላለፉ ከገባበት ኃጢያትና ባርነት ነፃ ለማውጣት ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ነው፡፡ ሌላው ኢየሱስ ክርስቶስ በመወለዱ ከሩቅ ምስራቅ የመጡ የጥበብ ሰዎች (ሰብዓ ሰገል) እጅ መንሻ ወርቅ እና ዕጣን ከርቤ ስጦታ አበርክተዋል፡፡ በዚህ መነሻነትም በገና ሰሞን ስጦታ ማበርከትና መለዋወጥ የተለመደ ነው፡፡ስጦታ በኢትዮጵያውያን ባህል የቆየና የተለመደ ባህል ነው፡፡ በአዲስ አበባ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በተለይ በበዓላት ሰሞን አቅም የሚያንሳቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በዓልን በደስታ እንዲውሉ ማዕድ ማጋራትን ጨምሮ የተለያዩ ስጦታዎችን ማበርከት እየተለመደ መጥቷል፡፡

ወይዘሮ ትዕግስት ሁጂራ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 ማዘር ትሬዛ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ነዋሪ ናቸው፡፡ እሳቸውን ጨምሮ አምስት የቤተሰብ አባላትን በሳምንት ሁለት ቀን "ሰንደይ ማርኬት" እየሰሩ በሚያገኙት ገቢ የቤት ኪራይ፣ የቤት ፍጆታና የልጆች የትምህርት ወጪ በመሸፈን እየኖሩ እንደሚገኙ ይናገራሉ፡፡

ኑሯቸው ከእጅ ወደ አፍ የሚባል እንደሆነ የሚናገሩት ወይዘሮ ትዕግስት፣ ከዚህ ቀደም በተለይ በበዓል ወቅት ዶሮም ሆነ ሌሎች አስፈላጊ ግብአቶች መግዣ የሚሆን አቅም አጥተው በራቸውን ዘግተው ደስታ ርቋቸው ያሳልፉ እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በተለያዩ ጊዜያት በማዕድ ማጋራት በሚደረግላቸው ድጋፍ በዓልን በደስታ ማሳለፋቸውን ይናገራሉ፡፡ ለ2018 ዓ.ም አዲስ ዓመት ለበዓል ማሳለፊያ አንድ ሊትር ዘይት፣ 5 ኪሎ ግራም ዱቄት፣ አንድ ኪሎ የአተር ክክ እና አንድ ኪሎ ምስር ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡ ከዚህ ቀደም በነበሩ በዓላት ዶሮ እና እንቁላል ጭምር ድጋፍ አግኝተዋል፡፡ በዚህም ልጆቻቸውንና ቤተሰባቸውን "ምን አበላቸዋለሁ" ብለው ሳይጨነቁ ደስተኛ ሆነው ማሳለፋቸውን ገልጸው እንዲህ ዓይነት ያለው ለሌላው የማካፈልና የመተጋገዝ ልምድ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

በዚያው አካባቢ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ የሺ ሽኩርም እሳቸውን ጨምሮ አምስት የቤተሰብ አባላትን ያስተዳድራሉ። ኑሯቸውም ከእጅ ወደ አፍ የሚባል እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ በበዓል ሰሞን ሲኖራቸው ዶሮና ሌሎች የቤት ውስጥ ፍጆታዎችን አሟልተው፤ ሳይኖራቸው ደግሞ እንደሌላው ጊዜ ራሳቸውን አሳምነው በባዶ ቤት ያሳልፉ እንደነበር ያነሳሉ፡፡ በማዕድ ማጋራት የሚያገኙት ድጋፍ በዓልን ሳይጎድልባቸው ከቤተሰባቸው ጋር ተደስተው እንዲያሳልፉ እንዳገዛቸው ተናግረዋል። "ድጋፉ አስደሳች ነው፤ ተመስገን ነው የምለው፤ ከእኛም የባሱ፣ መንቀሳቀስ የማይችሉ፣ ጧሪና ደጋፊ የሌላቸው፣ አልጋ ላይ የሚውሉ አቅመ ደካሞችን መደገፍ ያስፈልጋል፡፡" ሲሉ ድጋፉ መጠናከር እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡


ፎቶ- ከገፀ ድር
የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ድጋፍ ለሚሹ ወገኖች ማዕድ ሲያጋሩ

> "በጎ ፈቃደኝነትን ባህሉ ያደረገ ማህበረሰብ ሲኖር በኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች ያሉ ጉድለቶች እየተሞሉ፣ ማህበራዊ ፍትህ እየተረጋገጠ ይሄዳል"

ይህንን መነሻ በማድረግ ስጦታ ምንድን ነው? የስጦታና መደጋገፍ ባህል ፋይዳው እስከምን ድረስ ነው? እንደ አዲስ አበባ ማዕድ ማጋራትን ጨምሮ ስጦታ ባህል እንዲሆን ምን እየተሰራ ነው? ስንል ዳሰሳ አድርገናል፡፡

የሶሻል አንትሮፖሎጂ መምህርና ተመራማሪው ገብሬ ይንቲሶ (ፕ/ር) ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፣ "ስጦታ አንድ ሰው ለሌላ ሰው ወይም ወገን ያለ ክፍያ፤ መልስ ሳይጠብቅ በነፃ የሚሰጠው ነገር ነው፡፡ ስጦታውም ዕቃ፣ ገንዘብ፣ ጊዜና የተለያየ ሀብትና ንብረት ሊሆን ይችላል። ስጦታ በግለሰብ ወይም በድርጅትም ሊሰጥም ይችላል፡፡ ስጦታ ፍቅርንና ቸርነትን ለመግለፅ ይደረጋል፡፡ በተለይ ያለው ለሌላው በሚሰጥበት ጊዜ አብሮነትን ያጠናክራል"፡፡

ባህላችንን በደንብ ስለማናየው እንጂ በሀገራችን የዳበረ የመስጠት ባህል እንዳለ የሶሻል አንትሮፖሎጂ ተመራማሪው ገብሬ (ፕ/ር) ያነሳሉ፡፡ "ለልጆች ስጦታ ማበርከት፣ በሀዘንና ደስታ ጊዜ፣ የታመመን ሰውና ዘመድ ለመጠየቅ ሲሄድ በባዶ እጅ ሳይሆን የተለያየ ስጦታ በመያዝ ነው፡፡ በቤተ እምነቶች በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በገና በዓል ስጦታ ማበርከት በተለይ በከተሞች ዘንድ እየተለመደ መጥቷል፡፡ በእስልምና እምነት በበዓል ወቅት ፆም ሲፈታ መልካም ማድረግ (ሱና) በፈጣሪ ዘንድ የተወደደ ተደርጎ ይወሰዳል"፡፡

በየብሔረሰቡም ስጦታ ማድረግ የተለመደ እንደሆነ የሚያነሱት የሶሻል አንትሮፖሎጂ ተመራማሪው ገብሬ (ፕ/ር)፣ እሳቸው በወጡበት በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የአሪ ብሔረሰብ የዘመን መለወጫ በዓል (ዲሽታ ጊና) በሚከበርበት ወቅት አስቀድሞ ከ10 ወይም 15 ቀናት በፊት ሰዎች ከሚያከናውኗቸው ተግባራት መካከል ያለው ለሌለው ድጋፍ ማድረግ ይጠቀሳል፡፡

ስጦታ የሚያስገኘው ጥቅም ዘርፈ ብዙ እንደሆነ የሶሻል አንትሮፖሎጂ ተመራማሪው ገብሬ (ፕ/ር) ያነሳሉ። "በመስጠት ደስታና እርካታ ይገኛል። ወዳጅነት ይጠናከራል፡፡ ህይወት ይታደሳል፡፡ ሰጪው ብቻ ሳይሆን ተቀባዩም ችግሩ ይቀረፍለታል፤ ክብርና ደስታም ይሰማዋል፡፡ ስጦታ ሲደረግ የሚያይ ታዛቢም እውቀትና ልምድ ይሆነዋል፡፡ 'ለካስ እንደዚህ ማድረግ ይቻላል' የሚል ስሜት ይፈጥርበታል"፡፡

"ስጦታን ባህል ስናደርግ ማህበራዊ ትስስርና መተባበር እየተጠናከረ ይሄዳል። መተሳሰብና መደጋገፍ ይኖራል። በተቋማት የሚደረገው ስጦታም በተደራጀ መልክ ድጋፍ ለሚፈልጉ ወገኖች ተደራሽ ለመሆን ይረዳል።" ብለዋል፤ የሶሻል አንትሮፖሎጂ ተመራማሪው ገብሬ (ፕ/ር)።

### እንደ ከተማ ምን እየተሰራ ነው?

በአዲስ አበባ ከተማ የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ወይዘሮ አስራት ንጉሴ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፣ "በክረምትና በበጋ የበጎ ፈቃድ መርሃ ግብር ከከተማ እስከ ወረዳ ድረስ አሰራር በመዘርጋት እና ማህበረሰቡንና ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ በርካታ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። በዚህም የበርካታ ዜጎችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ማቃለል ተችሏል"፡፡

በበዓል ሰሞን ከሚደረጉ የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች መካከል ማዕድ ማጋራት አንዱ ሲሆን ዜጎች በተለይ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙት እንደ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በዓልን በፈገግታ ተሞልተው ተደስተው እንዲያሳልፉ አስችሏል፡፡ በዚህ መርሃ ግብርም ባለፉት ሰባት ዓመታት በድግግሞሽ 7 ሚሊዮን የከተማዋ ነዋሪዎች ተጠቃሚ መሆናቸውን ከአዲስ አበባ ከተማ የህብረተሰብ ተሳትፎ እና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።

ወይዘሮ አስራት እንደገለፁት፣ እንደ ማዕድ ማጋራት ያሉ የበጎነት ስራዎች ለህብረተሰቡ ያላቸው ፋይዳ ዘርፈ ብዙ ነው፡፡ የዕለት ጉርሳቸውን ለመሸፈን የሚቸገሩ አቅመ ደካሞች፣ የሀገር ባለውለታዎችና አካል ጉዳተኞችና እጅ ያጠራቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ማቃለል አስችሏል። 'የሚደግፈኝ ወገን አለኝ' ብለው ተስፋ እንዲሰንቁ አድርጓል፡፡

ማህበራዊ መስተጋብርን በማጠናከር፣ ማህበራዊ ፍትህን በማረጋገጥ፣ የወንድማማችነትና እህትማማችነት እሴትን በማጎልበት፣ ማህበረሰብ በመንግስት ላይ ያለውን እምነት በማሳደግ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ነው፡፡

ማዕድ በማጋራት ወይም በሌላ መልክ በሚሰራው የበጎነት ስራ ድጋፍ የሚደረግላቸው ብቻ ሳይሆን ለጋሾችም ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ወይዘሮ አስራት ይናገራሉ፡፡ ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች ማዕድ በማጋራትና በተለያየ መልኩ በመሳተፍ ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን ሲወጡ ከማህበረሰቡ ጋር ያላቸው ትስስር፣ መተማመንና መቀራረብ እያደገ ይመጣል፡፡ እውቅናና ምስጋና ያገኛሉ፤ ድርጅቶች ምርታቸውን መሸጥ ይችላሉ። በማህበረሰቡ ውስጥ "የኔ ተቋም ነው" የሚል የባለቤትነት ስሜት ይፈጥራል። ስማቸውና የድርጅታቸው ማንነት (ብራንድ) ከፍ ይላል፡፡

የአዲስ አበባ ህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ርዕይ በጎ ፈቃደኝነት ባህሉ ያደረገ ማህበረሰብ ተገንብቶ ማየት እንደሆነ ያነሱት ምክትል ኮሚሽነር ወይዘሮ አስራት፣ በጎ ፈቃደኝነትን ባህሉ ያደረገ ማህበረሰብ ሲኖር በኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች ያሉ ጉድለቶች እየተሞሉ፣ ማህበራዊ ፍትህ እየተረጋገጠ ይሄዳል፡፡

ማዕድ ማጋራትና መሰል የስጦታ ተግባራት ወንድማማችነትና እህትማማችነት እሴት፣ ማህበራዊ መስተጋብር እንዲያድግ አድርጓል፡፡ በጎ ፈቃደኝነት ባህል ያደረገ ትውልድ የሚገነባበት ዕድል ተፈጥሯል፡፡ በጎነት በፖለቲካው መስክ የበጎነት ስራዎች መረዳዳት፣ መካፈል፣ መደጋገፍና አብሮነትን በማጠናከር ሰላማዊና የተግባባ ማህበረሰብ በመፍጠር አስተዋፅኦ እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡

መደጋገፍና መተጋገዝ የኢትዮጵያውያን የቆየ ባህልና እሴት ነው፡፡ በሀይማኖት አስተምህሮዎችም የሚደገፍ በጎ ተግባር ነው፡፡ በጎነት ባህል እንዲሆን

ወደ ገጽ 22 ዞሯል

# ማስታወቂያ

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የ8ኛ ዙር መሬት ሊዝ ጨረታ ማስታወቂያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ በየካ፣ በንፋስ ስልክ ላፍቶ፣ በኮልፌ ቀራንዮ፣ በአቃቂ ቃሊቲ፣ በአዲስ ከተማ፣ ለሚ ኩራ፣ በጉለሌ ፣ ቂርቆስ እና ልደታ ክፍለ ከተሞች የሚገኙ ለተለያዩ አገልግሎቶች የተዘጋጁ የልማት ቦታዎችን በጨረታ አወዳድሮ በሊዝ ለማስተላለፍ ይፈልጋል፡፡

**በዚሁ መሠረት በጨረታው ለመሳተፍ የምትፈልጉ ተጫራቾች**

1. ለአንድ የጨረታ ሰነድ የማይመለስ ብር 2,300.00 (ሁለት ሺህ ሶስት መቶ ብር) በlandleasedocument.aalb.gov.et:(https://www.landleasedocument.aalb.gov.et) በመግባት በኦን ላይን በቴሌ ብር በመክፈል የጨረታውን ሰነድ ከ ታህሳስ 27/2018ዓ.ም እስከ ጥር 12/2018 ዓ.ም ከቀኑ 9 ሰዓት ድረስ መግዛት ይችላሉ፡፡
2. ማንኛዉም በዚህ የመሬት ሊዝ ጨረታ ለመሳተፍ የፈለገ ተጫራች በተራ ቁጥር 1 ላይ በተገለጸዉ ዌብ ሳይት በመግባት የጨረታ ሰነድ ለመግዛት በመጀመሪያ በስሙ የቴሌ ብር አካዉንት በመክፈት ከአካዉንቱ ተቀናሽ በማድረግ ሰነዱን መግዛት ይጠበቅበታል፡፡
3. ተጫራቾች ቦታዎቹ የሚገኙበት ቦታ በመሄድ አጠቃላይ የቦታዎችን ሁኔታ በማየት ዋጋ ማቅረብ አለባቸዉ፡፡
4. አንድ ተጫራች በአንድ የጨረታ ዙር ከአንድ ቦታ በላይ መጫረት አይችልም፡፡ በመሆኑም ከአንድ በላይ ቦታ ተጫርቶ ከተገኘ ተጫራቹ ከጨረታ ውጪ ይሆናል፡፡
5. ተጫራቾች ሞልተዉ የሚያቀርቡት የጨረታ መልስ ማቅረቢያ ሰነድ በተጫራቾች መመሪያ ላይ በቀረበው መስፈርት መሠረት መሆን ይኖርበታል፡፡
6. ተጫራቾች የሚወዳደሩበት ቦታ ስፋት በመነሻ ዋጋ ተባዝቶ የሚገኘዉን ጠቅላላ ዋጋ 50% የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በባንክ የክፍያ ማዘዣ /ሲፒኦ/ ለየቦታ ኮዱ በጋዜጣው ላይ የተቀመጠውን መጠን ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡ይህ ሳይሆን ቢቀር ወይንም ከ 50% ቢያንስ ተጫራቹ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከውድድር ይሰረዛል፡፡ እንዲሁም አንድ ተጫራች ሌላው በሰጠው ዋጋ ላይ ተንተርሶ ዋጋ ማቅረብ አይችልም፡፡ ከአዲስ አበባ ውጪ ከሚገኙ ባንኮች ሲፒኦ ስታሰሩ አዲስ አበባ ከሚገኙ ባንኮች በኔትዎርክ የተያያዘ መሆን አለበት ይህ ሳይሆን ቀርቶ ችግር ቢፈጠር መ/ቤቱ አይጠየቅም፡፡
7. ተጫራቾች የጨረታ መልስ ማቅረቢያ ሰነድ ስትመልሱ፣
   - 7.1 ኦርጅናል ሲፒኦ (CPO)
   - 7.2 የመስሪያ ቤቱ ማህተም ያረፈበት የጨረታ መልስ ማቅረቢያ ሰነድ
   - 7.3 የተጫራቹ መታወቂያ ኮፒ
   - 7.4 ሰነድ ለመግዛት በቴሌ ብር የተከፈለበት ስሊፕ (ደረሰኝ)
   - 7.5 ኦርጅናል የአቅም ማሳያ ማስረጃ
   - 7.6 ተጫራቹ የሚጫረተው በተወካይ ከሆነ የተወካይ መታወቂያ እና የውክልና ማስረጃ ኮፒ
   - 7.7 የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነ ማንኛውም ተጫራች ከሚኖርበት ሀገር በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ /ቆንስላ ጽ/ቤት/ የተሰጠውንና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተረጋግጦ የፀደቀ መታወቂያ(Yellow Card) የዋናውን ኮፒ ከመልስ ማቅረቢያው ጋር ማያያዝ አለበት፡፡
   - 7.8 የንግድ ማህበራት ለሆኑት በሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ፅ/ቤት የፀደቀ የማህበሩን መመስረቻ ፅሑፍ እና መተዳደሪያ ደንብ ፎቶ ኮፒ ሌሎች ህጋዊ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች ከሆኑ ህጋዊነታቸውን የሚያረጋግጥ ሰነድ እና የታደሰ ምስክር ወረቀት ፎቶ ኮፒ
   - 7.9 ጨረታውን የሚሳተፉት ባልና ሚስት በአንድ ሰነድ ከሆነ ህጋዊ የጋብቻ ማስረጃ ኮፒ እና በአንድ ወገን ስም የተሰራ የጨረታ ማስከበሪያ ሲፒኦ ማቅረብ አለባቸዉ፡፡
   - 7.10 በአንድ የጨረታ ሰነድ ከአንድ ሰው በላይ ሆነው ለመወዳደር ከፈለጉ ከሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ፅ/ቤት የተረጋገጠ የተደራጁበትን ህጋዊ ማስረጃ ኮፒ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
   - 7.11 በአጠቃላይ ከላይ የተገለጹትን ማስረጃዎች በፖስታ በማሸግ የጨረታ ቁጥር እና የቦታ መለያ ኮድ በፖስታዉ ላይ በመፃፍ ጥር 12/2018 ዓ.ም እስከ ቀኑ 11፡30 ሰዓት ድረስ ለም ሆቴል አካባቢ ኤም ኤ (MA) ህንፃ ላይ በሚገኘው በከተማው መሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ለዚህ በተዘጋጀ የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡
8. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ጥር 13/2018 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ጀምሮ በ3 ተከታታይ ቀናት በቦሌ ክ/ከተማ አስተዳደር አዳራሽ የሚከፈት ሆኖ ዝርዝሩ በውስጥ ማስታወቂያ ይገለፃል፡፡ ተጫራቾች ቦታውን በአካል ለመመልከት ከፈለጉ በ 27/04/18 ዓ.ም ፣ 30/04/18 ዓ.ም እና በ04/05/18 ዓ.ም ጠዋት ከ3፡00 ሰዓት - 6፡30 ሰዓት እና ከሰዓት 8፡00 ሰዓት - 11፡30 ሰዓት ለጨረታ የተዘጋጁ ቦታዎች በሚገኙበት ክ/ከተማ **የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት** ድረስ በመቅረብ ለዚህ ስራ በሚመደቡ አስጎብኝዎች አማካኝነት ቦታዎቹን መመልከት ይቻላል፡፡
9. ጨረታውን ያላሸነፉ (ተሸናፊ) ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙትን ሲፒኦ የጨረታው አሸናፊዎች በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከተገለፀበት ከ15 የስራ ቀናት በኃላ ባሉት 15 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ መ/ቤቱ (ቢሮው) ለባንክ በመላክ ወዳሰሩበት የባንክ ሂሳብ ተመላሽ ይደረጋል፡፡ በካሽ ያሰሩ ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትናውን ለመረከብ በቅድሚያ የሲፒኦውን ጉርድ ኮፒ ማቅረብና ማንነቱን የሚገልጽ መታወቂያ በመያዝ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ቀርበው መውሰድ አለባቸው፡፡ ከላይ በተገለጸዉ የጊዜ ገደብ ውስጥ ቀርበው ካልወሰዱ ለሚፈጠረው ችግር አጫራቹ መ/ቤት ተጠያቂ አይሆንም፡፡
10. መስሪያ ቤቱ (ቢሮው) የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይንም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
11. ለተጨማሪ መረጃ የመሬት ልማት አስተዳደር ቢሮ፡-

**በስልክ ቁጥር +251111570595 Website: https://www.aalb.gov.et/**

t.me/addisland Addis Ababa City Land Development Administration and Bureau መረጃ ማግኘት ይቻላል፡፡

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ

### በቂርቆስ ክ/ክተማ 8ኛው ዙር የመሬት ሊዝ ጨረታ የወጡ ቦታዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የጨረታ ቁጥር | የቦታ ኮድ | ክ/ከተማ | ወረዳ | የቦታው ደረጃ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | የቦታው አገልግሎት | የህንፃ ከፍታ | የቦታው መነሻ ዋጋ | ቅድሚያ ክፍያ በ% | የችሮታ ጊዜ በአመት | የክፍያ ማጠናቀቂያ ጊዜ በአመት | የሊዝ ዘመን በአመት | የአቅም ማሳያ | ሲፒኦ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቂር/ክ/ከ/01/18 | LDR-KIR-MIX-00015132 | ቂርቆስ | 11 | 1/2 | 1919 | HDMR | max G+29 | 2165.47 | 40 | 2 | 5 | 60 | 13,433,000.00 | 2,077,768.47 |

### በን/ስ/ላፍቶ ክ/ክተማ 8ኛው ዙር የመሬት ሊዝ ጨረታ የወጡ ቦታዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የጨረታ ቁጥር | የቦታ ኮድ | ክ/ከተማ | ወረዳ | የቦታው ደረጃ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | የቦታው አገልግሎት | የህንፃ ከፍታ | የቦታው መነሻ ዋጋ | ቅድሚያ ክፍያ በ% | የችሮታ ጊዜ በአመት | የክፍያ ማጠናቀቂያ ጊዜ በአመት | የሊዝ ዘመን በአመት | የአቅም ማሳያ | ሲፒኦ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ን/ስ/ላ/ክ/ከ/01/18 | LDR-NIF-MIX-00014090 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 1/3 | 597 | LDMR | max G+19 | 1900.19 | 40 | 2 | 5 | 60 | 2,786,000.00 | 567,206.72 |
| 2 | ን/ስ/ላ/ክ/ከ/02/18 | LDR-NIF-MIX-00014092 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 1/3 | 557 | LDMR | max G+19 | 1900.19 | 40 | 2 | 5 | 60 | 2,599,333.33 | 529,202.92 |
| 3 | ን/ስ/ላ/ክ/ከ/03/18 | LDR-NIF-MIX-00014142 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 1/3 | 225 | LDMR | max G+9 | 1900.19 | 40 | 2 | 5 | 60 | 525,000.00 | 213,771.38 |
| 4 | ን/ስ/ላ/ክ/ከ/04/18 | LDR-NIF-MIX-00015042 | ን/ስ/ላፍቶ | 14 | 2/2 | 369 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 861,000.00 | 225,307.71 |

| ተ.ቁ | የጨረታ ቁጥር | የቦታ ኮድ | ክ/ከተማ | ወረዳ | የቦታው ደረጃ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | የቦታው አገልግሎት | የህንፃ ከፍታ | የቦታው መነሻ ዋጋ | ቅድሚያ ክፍያ በ% | የችሮታ ጊዜ በአመት | የክፍያ ማጠናቀቂያ ጊዜ በአመት | የሊዝ ዘመን በአመት | የአቅም ማሳያ | ሲፒኦ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | ን/ስ/ላ/ክ/ክ/05/18 | LDR-NIF-MIX-00015044 | ን/ስ/ላፍቶ | 14 | 2/2 | 150 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 350,000.00 | 91,588.50 |
| 6 | ን/ስ/ላ/ክ/ክ/06/18 | LDR-NIF-MIX-00015059 | ን/ስ/ላፍቶ | 14 | 2/2 | 175 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 408,333.33 | 106,853.25 |
| 7 | ን/ስ/ላ/ክ/ክ/07/18 | LDR-NIF-MIX-00015060 | ን/ስ/ላፍቶ | 14 | 2/2 | 543 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,267,000.00 | 331,550.37 |
| 8 | ን/ስ/ላ/ክ/ክ/08/18 | LDR-NIF-MIX-00015070 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 2/2 | 387 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 903,000.00 | 236,298.33 |
| 9 | ን/ስ/ላ/ክ/ክ/09/18 | LDR-NIF-MIX-00015133 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 1/3 | 467 | LDMR | max G+12 | 1900.19 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,416,566.67 | 443,694.37 |
| 10 | ን/ስ/ላ/ክ/ክ/10/18 | LDR-NIF-MIX-00015134 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 1/3 | 482 | LDMR | max G+12 | 1900.19 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,462,066.67 | 457,945.79 |
| 11 | ን/ስ/ላ/ክ/ክ/11/18 | LDR-NIF-MIX-00015135 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 1/3 | 500 | LDMR | max G+12 | 1900.19 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,516,666.67 | 475,047.50 |
| 12 | ን/ስ/ላ/ክ/ክ/12/18 | LDR-NIF-MIX-00015136 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 1/3 | 500 | LDMR | max G+12 | 1900.19 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,516,666.67 | 475,047.50 |
| 13 | ን/ስ/ላ/ክ/ክ/13/18 | LDR-NIF-MIX-00015137 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 1/3 | 500 | LDMR | max G+12 | 1900.19 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,516,666.67 | 475,047.50 |
| 14 | ን/ስ/ላ/ክ/ክ/14/18 | LDR-NIF-MIX-00015138 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 1/3 | 500 | LDMR | max G+12 | 1900.19 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,516,666.67 | 475,047.50 |
| 15 | ን/ስ/ላ/ክ/ክ/15/18 | LDR-NIF-MIX-00015139 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 1/3 | 500 | LDMR | max G+12 | 1900.19 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,516,666.67 | 475,047.50 |
| 16 | ን/ስ/ላ/ክ/ክ/16/18 | LDR-NIF-MIX-00015140 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 1/3 | 500 | LDMR | max G+12 | 1900.19 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,516,666.67 | 475,047.50 |
| 17 | ን/ስ/ላ/ክ/ክ/17/18 | LDR-NIF-MIX-00015141 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 1/3 | 500 | LDMR | max G+9 | 1900.19 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 475,047.50 |
| 18 | ን/ስ/ላ/ክ/ክ/18/18 | LDR-NIF-MIX-00015142 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 2/5 | 500 | LDMR | max G+9 | 1027.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 256,960.00 |
| 19 | ን/ስ/ላ/ክ/ክ/19/18 | LDR-NIF-MIX-00015143 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 2/5 | 500 | LDMR | max G+9 | 1027.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 256,960.00 |
| 20 | ን/ስ/ላ/ክ/ክ/20/18 | LDR-NIF-MIX-00015144 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 2/5 | 500 | LDMR | max G+9 | 1027.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 256,960.00 |
| 21 | ን/ስ/ላ/ክ/ክ/21/18 | LDR-NIF-MIX-00015145 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 2/5 | 500 | LDMR | max G+9 | 1027.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 256,960.00 |
| 22 | ን/ስ/ላ/ክ/ክ/22/18 | LDR-NIF-MIX-00015146 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 2/5 | 500 | LDMR | max G+9 | 1027.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 256,960.00 |

## የአዲስ ከተማ ክ/ክተማ 8ኛው ዙር የመሬት ሊዝ ጨረታ የወጡ ቦታዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የጨረታ ቁጥር | የቦታ ኮድ | ክ/ከተማ | ወረዳ | የቦታው ደረጃ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | የቦታው አገልግሎት | የህንፃ ከፍታ | የቦታው መነሻ ዋጋ | ቅድሚያ ክፍያ በ% | የችሮታ ጊዜ በአመት | የክፍያ ማጠናቀቂያ ጊዜ በአመት | የሊዝ ዘመን በአመት | የአቅም ማሳያ | ሲፒኦ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አ/ክ/ክ/01/18 | LDR-ADK-MIX-00014014 | አዲስ ከተማ | 11 | 2/5 | 214 | LDMR | max G+9 | 1027.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 499,333.33 | 109,978.88 |

## የኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ክተማ 8ኛው ዙር የመሬት ሊዝ ጨረታ የወጡ ቦታዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የጨረታ ቁጥር | የቦታ ኮድ | ክ/ከተማ | ወረዳ | የቦታው ደረጃ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | የቦታው አገልግሎት | የህንፃ ከፍታ | የቦታው መነሻ ዋጋ | ቅድሚያ ክፍያ በ% | የችሮታ ጊዜ በአመት | የክፍያ ማጠናቀቂያ ጊዜ በአመት | የሊዝ ዘመን በአመት | የአቅም ማሳያ | ሲፒኦ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/01/18 | LDR-KOL-MIX-00014971 | ኮ/ቀራኒዮ | 11 | 2/2 | 141 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 329,000.00 | 86,093.19 |
| 2 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/02/18 | LDR-KOL-MIX-00014972 | ኮ/ቀራኒዮ | 11 | 2/1 | 266 | LDMR | max G+9 | 1327.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 620,666.67 | 176,542.87 |
| 3 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/03/18 | LDR-KOL-MIX-00014973 | ኮ/ቀራኒዮ | 11 | 2/1 | 227 | LDMR | max G+9 | 1327.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 529,666.67 | 150,658.77 |
| 4 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/04/18 | LDR-KOL-MIX-00014974 | ኮ/ቀራኒዮ | 11 | 2/1 | 292 | LDMR | max G+9 | 1327.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 681,333.33 | 193,798.94 |
| 5 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/05/18 | LDR-KOL-MIX-00014975 | ኮ/ቀራኒዮ | 11 | 2/1 | 283 | LDMR | max G+9 | 1327.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 660,333.33 | 187,825.69 |
| 6 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/06/18 | LDR-KOL-MIX-00014976 | ኮ/ቀራኒዮ | 2 | 2/4 | 137 | LDMR | max G+9 | 1074.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 319,666.67 | 73,595.72 |
| 7 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/07/18 | LDR-KOL-MIX-00014980 | ኮ/ቀራኒዮ | 2 | 3/1 | 291 | LDMR | max G+9 | 994.71 | 40 | 2 | 5 | 60 | 679,000.00 | 144,730.31 |
| 8 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/08/18 | LDR-KOL-MIX-00014981 | ኮ/ቀራኒዮ | 2 | 2/5 | 260 | LDMR | max G+9 | 1027.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 606,666.67 | 133,619.20 |
| 9 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/09/18 | LDR-KOL-MIX-00014982 | ኮ/ቀራኒዮ | 2 | 2/5 | 198 | LDMR | max G+9 | 1027.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 462,000.00 | 101,756.16 |
| 10 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/10/18 | LDR-KOL-MIX-00015013 | ኮ/ቀራኒዮ | 3 | 3/3 | 159 | LDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 371,000.00 | 73,763.28 |
| 11 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/11/18 | LDR-KOL-MIX-00015014 | ኮ/ቀራኒዮ | 3 | 3/3 | 189 | LDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 441,000.00 | 87,680.88 |
| 12 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/12/18 | LDR-KOL-MIX-00015015 | ኮ/ቀራኒዮ | 3 | 3/3 | 161 | LDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 375,666.67 | 74,691.12 |
| 13 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/13/18 | LDR-KOL-MIX-00015016 | ኮ/ቀራኒዮ | 3 | 3/3 | 180 | LDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 420,000.00 | 83,505.60 |
| 14 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/14/18 | LDR-KOL-MIX-00015020 | ኮ/ቀራኒዮ | 3 | 2/3 | 193 | LDMR | max G+9 | 1191.17 | 40 | 2 | 5 | 60 | 450,333.33 | 114,947.91 |
| 15 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/15/18 | LDR-KOL-MIX-00015022 | ኮ/ቀራኒዮ | 3 | 2/3 | 180 | LDMR | max G+9 | 1191.17 | 40 | 2 | 5 | 60 | 420,000.00 | 107,205.30 |
| 16 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/16/18 | LDR-KOL-MIX-00015147 | ኮ/ቀራኒዮ | 7 | 2/1 | 128 | LDMR | max G+9 | 1327.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 298,666.67 | 84,952.96 |
| 17 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/17/18 | LDR-KOL-MIX-00015148 | ኮ/ቀራኒዮ | 7 | 2/3 | 87 | LDMR | max G+9 | 1191.17 | 40 | 2 | 5 | 60 | 203,000.00 | 51,815.90 |
| 18 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/18/18 | LDR-KOL-MIX-00015149 | ኮ/ቀራኒዮ | 7 | 2/3 | 89 | LDMR | max G+9 | 1191.17 | 40 | 2 | 5 | 60 | 207,666.67 | 53,007.07 |
| 19 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/19/18 | LDR-KOL-MIX-00015150 | ኮ/ቀራኒዮ | 7 | 2/3 | 111 | LDMR | max G+9 | 1191.17 | 40 | 2 | 5 | 60 | 259,000.00 | 66,109.94 |
| 20 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/20/18 | LDR-KOL-MIX-00015151 | ኮ/ቀራኒዮ | 7 | 2/3 | 104 | LDMR | max G+9 | 1191.17 | 40 | 2 | 5 | 60 | 242,666.67 | 61,940.84 |
| 21 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/21/18 | LDR-KOL-MIX-00015152 | ኮ/ቀራኒዮ | 7 | 2/3 | 84 | LDMR | max G+9 | 1191.17 | 40 | 2 | 5 | 60 | 196,000.00 | 50,029.14 |
| 22 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/22/18 | LDR-KOL-MIX-00015153 | ኮ/ቀራኒዮ | 7 | 1/5 | 167 | LDMR | max G+9 | 1531.91 | 40 | 2 | 5 | 60 | 389,666.67 | 127,914.49 |
| 23 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/23/18 | LDR-KOL-MIX-00015154 | ኮ/ቀራኒዮ | 7 | 2/5 | 186 | LDMR | max G+9 | 1027.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 434,000.00 | 95,589.12 |
| 24 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/24/18 | LDR-KOL-MIX-00015155 | ኮ/ቀራኒዮ | 3 | 3/5 | 217 | LDMR | max G+9 | 873.74 | 40 | 2 | 5 | 60 | 506,333.33 | 94,800.79 |
| 25 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/25/18 | LDR-KOL-MIX-00015156 | ኮ/ቀራኒዮ | 3 | 3/5 | 226 | LDMR | max G+9 | 873.74 | 40 | 2 | 5 | 60 | 527,333.33 | 98,732.62 |
| 26 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/26/18 | LDR-KOL-MIX-00015157 | ኮ/ቀራኒዮ | 3 | 2/3 | 188 | LDMR | max G+9 | 1191.17 | 40 | 2 | 5 | 60 | 438,666.67 | 111,969.98 |
| 27 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/27/18 | LDR-KOL-MIX-00015158 | ኮ/ቀራኒዮ | 5 | 2/1 | 309 | LDMR | max G+9 | 1327.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 721,000.00 | 205,081.76 |
| 28 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/28/18 | LDR-KOL-MIX-00015159 | ኮ/ቀራኒዮ | 5 | 2/1 | 283 | LDMR | max G+9 | 1327.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 660,333.33 | 187,825.69 |
| 29 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/29/18 | LDR-KOL-MIX-00015160 | ኮ/ቀራኒዮ | 5 | 1/4 | 189 | LDMR | max G+9 | 1552.93 | 40 | 2 | 5 | 60 | 441,000.00 | 146,751.89 |
| 30 | ኮ/ቀ/ክ/ክ/30/18 | LDR-KOL-MIX-00015292 | ኮ/ቀራኒዮ | 3 | 2/5 | 199 | LDMR | max G+9 | 1027.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 464,333.33 | 102,270.08 |

## በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ክተማ 8ኛው ዙር የመሬት ሊዝ ጨረታ የወጡ ቦታዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የጨረታ ቁጥር | የቦታ ኮድ | ክ/ከተማ | ወረዳ | የቦታው ደረጃ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | የቦታው አገልግሎት | የህንፃ ከፍታ | የቦታው መነሻ ዋጋ | ቅድሚያ ክፍያ በ% | የችሮታ ጊዜ በአመት | የክፍያ ማጠናቀቂያ ጊዜ በአመት | የሊዝ ዘመን በአመት | የአቅም ማሳያ | ሲፒኦ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አ/ቃ/ክ/ክ/01/18 | LDR-AKI-MIX-00013939 | አቃቂ | 13 | 2/2 | 429 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,001,000.00 | 261,943.11 |
| 2 | አ/ቃ/ክ/ክ/02/18 | LDR-AKI-MIX-00014245 | አቃቂ | 4 | 2/4 | 322 | LDMR | max G+9 | 1071.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 751,333.33 | 172,493.79 |
| 3 | አ/ቃ/ክ/ክ/03/18 | LDR-AKI-MIX-00014278 | አቃቂ | 8 | 1/5 | 106 | LDMR | max G+9 | 1531.91 | 40 | 2 | 5 | 60 | 247,333.33 | 81,191.23 |
| 4 | አ/ቃ/ክ/ክ/04/18 | LDR-AKI-MIX-00014281 | አቃቂ | 8 | 1/5 | 104 | LDMR | max G+9 | 1531.91 | 40 | 2 | 5 | 60 | 242,666.67 | 79,659.32 |
| 5 | አ/ቃ/ክ/ክ/05/18 | LDR-AKI-MIX-00014283 | አቃቂ | 8 | 1/5 | 104 | LDMR | max G+9 | 1531.91 | 40 | 2 | 5 | 60 | 242,666.67 | 79,659.32 |
| 6 | አ/ቃ/ክ/ክ/06/18 | LDR-AKI-MIX-00014332 | አቃቂ | 13 | 2/3 | 76 | LDMR | max G+9 | 1191.17 | 40 | 2 | 5 | 60 | 177,333.33 | 45,264.46 |
| 7 | አ/ቃ/ክ/ክ/07/18 | LDR-AKI-MIX-00014340 | አቃቂ | 13 | 2/2 | 749 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,747,666.67 | 457,331.91 |
| 8 | አ/ቃ/ክ/ክ/08/18 | LDR-AKI-MIX-00014588 | አቃቂ | 2 | 2/2 | 232 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 541,333.33 | 141,656.88 |
| 9 | አ/ቃ/ክ/ክ/09/18 | LDR-AKI-MIX-00014589 | አቃቂ | 2 | 2/2 | 232 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 541,333.33 | 141,656.88 |
| 10 | አ/ቃ/ክ/ክ/10/18 | LDR-AKI-MIX-00014591 | አቃቂ | 2 | 2/2 | 213 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 497,000.00 | 130,055.67 |
| 11 | አ/ቃ/ክ/ክ/11/18 | LDR-AKI-MIX-00014688 | አቃቂ | 1 | 2/2 | 90 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 210,000.00 | 54,953.10 |
| 12 | አ/ቃ/ክ/ክ/12/18 | LDR-AKI-MIX-00014692 | አቃቂ | 13 | 2/2 | 165 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 385,000.00 | 100,747.35 |
| 13 | አ/ቃ/ክ/ክ/13/18 | LDR-AKI-MIX-00014693 | አቃቂ | 13 | 2/2 | 167 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 389,666.67 | 101,968.53 |
| 14 | አ/ቃ/ክ/ክ/14/18 | LDR-AKI-MIX-00014887 | አቃቂ | 4 | 2/2 | 377 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 879,666.67 | 230,192.43 |
| 15 | አ/ቃ/ክ/ክ/15/18 | LDR-AKI-MIX-00014889 | አቃቂ | 9 | 2/2 | 351 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 819,000.00 | 214,317.09 |
| 16 | አ/ቃ/ክ/ክ/16/18 | LDR-AKI-MIX-00014890 | አቃቂ | 9 | 2/2 | 350 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 816,666.67 | 213,706.50 |
| 17 | አ/ቃ/ክ/ክ/17/18 | LDR-AKI-MIX-00014891 | አቃቂ | 9 | 2/2 | 350 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 816,666.67 | 213,706.50 |
| 18 | አ/ቃ/ክ/ክ/18/18 | LDR-AKI-MIX-00014892 | አቃቂ | 9 | 2/2 | 351 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 819,000.00 | 214,317.09 |
| 19 | አ/ቃ/ክ/ክ/19/18 | LDR-AKI-MIX-00014896 | አቃቂ | 9 | 2/2 | 412 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 961,333.33 | 251,563.08 |
| 20 | አ/ቃ/ክ/ክ/20/18 | LDR-AKI-MIX-00014897 | አቃቂ | 9 | 1/3 | 400 | LDMR | max G+9 | 1900.19 | 40 | 2 | 5 | 60 | 933,333.33 | 380,038.00 |
| 21 | አ/ቃ/ክ/ክ/21/18 | LDR-AKI-MIX-00014898 | አቃቂ | 9 | 1/3 | 397 | LDMR | max G+9 | 1900.19 | 40 | 2 | 5 | 60 | 926,333.33 | 377,187.72 |
| 22 | አ/ቃ/ክ/ክ/22/18 | LDR-AKI-MIX-00014900 | አቃቂ | 9 | 1/3 | 397 | LDMR | max G+9 | 1900.19 | 40 | 2 | 5 | 60 | 926,333.33 | 377,187.72 |
| 23 | አ/ቃ/ክ/ክ/23/18 | LDR-AKI-MIX-00014902 | አቃቂ | 1 | 2/1 | 350 | LDMR | max G+9 | 1327.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 816,666.67 | 232,293.25 |
| 24 | አ/ቃ/ክ/ክ/24/18 | LDR-AKI-MIX-00014916 | አቃቂ | 2 | 2/2 | 221 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 515,666.67 | 134,940.39 |
| 25 | አ/ቃ/ክ/ክ/25/18 | LDR-AKI-MIX-00014919 | አቃቂ | 9 | 2/2 | 404 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 942,666.67 | 246,678.36 |
| 26 | አ/ቃ/ክ/ክ/26/18 | LDR-AKI-MIX-00014922 | አቃቂ | 8 | 3/2 | 239 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 557,666.67 | 114,745.10 |
| 27 | አ/ቃ/ክ/ክ/27/18 | LDR-AKI-MIX-00014927 | አቃቂ | 8 | 3/4 | 992 | LDMR | max G+9 | 904.77 | 40 | 2 | 5 | 60 | 2,314,666.67 | 448,765.92 |
| 28 | አ/ቃ/ክ/ክ/28/18 | LDR-AKI-MIX-00014930 | አቃቂ | 8 | 3/1 | 344 | LDMR | max G+9 | 994.71 | 40 | 2 | 5 | 60 | 802,666.67 | 171,090.12 |
| 29 | አ/ቃ/ክ/ክ/29/18 | LDR-Aki-MIX-00015293 | አቃቂ | 9 | 2/2 | 200 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 466,666.67 | 122,118.00 |
| 30 | አ/ቃ/ክ/ክ/30/18 | LDR-Aki-MIX-00015294 | አቃቂ | 9 | 2/2 | 200 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 466,666.67 | 122,118.00 |
| 31 | አ/ቃ/ክ/ክ/31/18 | LDR-Aki-MIX-00015295 | አቃቂ | 9 | 2/2 | 200 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 466,666.67 | 122,118.00 |
| 32 | አ/ቃ/ክ/ክ/32/18 | LDR-Aki-MIX-00015296 | አቃቂ | 9 | 2/2 | 200 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 466,666.67 | 122,118.00 |
| 33 | አ/ቃ/ክ/ክ/33/18 | LDR-Aki-MIX-00015297 | አቃቂ | 9 | 2/2 | 200 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 466,666.67 | 122,118.00 |
| 34 | አ/ቃ/ክ/ክ/34/18 | LDR-Aki-MIX-00015298 | አቃቂ | 9 | 2/2 | 275 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 641,666.67 | 167,912.25 |
| 35 | አ/ቃ/ክ/ክ/35/18 | LDR-Aki-MIX-00015299 | አቃቂ | 9 | 2/2 | 272 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 634,666.67 | 166,080.48 |
| 36 | አ/ቃ/ክ/ክ/36/18 | LDR-Aki-MIX-00015300 | አቃቂ | 9 | 2/2 | 200 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 466,666.67 | 122,118.00 |
| 37 | አ/ቃ/ክ/ክ/37/18 | LDR-Aki-MIX-00015301 | አቃቂ | 9 | 2/2 | 200 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 466,666.67 | 122,118.00 |
| 38 | አ/ቃ/ክ/ክ/38/18 | LDR-Aki-MIX-00015302 | አቃቂ | 9 | 2/2 | 200 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 466,666.67 | 122,118.00 |
| 39 | አ/ቃ/ክ/ክ/39/18 | LDR-Aki-MIX-00015303 | አቃቂ | 9 | 2/2 | 200 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 466,666.67 | 122,118.00 |
| 40 | አ/ቃ/ክ/ክ/40/18 | LDR-Aki-MIX-00015304 | አቃቂ | 9 | 2/2 | 197 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 459,666.67 | 120,286.23 |
| 41 | አ/ቃ/ክ/ክ/41/18 | LDR-Aki-MIX-00015305 | አቃቂ | 1 | 2/2 | 500 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 305,295.00 |
| 42 | አ/ቃ/ክ/ክ/42/18 | LDR-Aki-MIX-00015306 | አቃቂ | 1 | 2/2 | 400 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 933,333.33 | 244,236.00 |
| 43 | አ/ቃ/ክ/ክ/43/18 | LDR-Aki-MIX-00015307 | አቃቂ | 13 | 2/2 | 490 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,143,333.33 | 299,189.10 |

## በጉለሌ ክ/ክተማ 8ኛው ዙር የመሬት ሊዝ ጨረታ የወጡ ቦታዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የጨረታ ቁጥር | የቦታ ኮድ | ክ/ከተማ | ወረዳ | የቦታው ደረጃ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | የቦታው አገልግሎት | የህንፃ ከፍታ | የቦታው መነሻ ዋጋ | ቅድሚያ ክፍያ በ% | የችሮታ ጊዜ በአመት | የክፍያ ማጠናቀቂያ ጊዜ በአመት | የሊዝ ዘመን በአመት | የአቅም ማሳያ | ሲፒኦ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጉ/ክ/ክ/01/18 | LDR-GUL-MIX-00014655 | ጉለሌ | 7 | 3/3 | 171 | LDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 399,000.00 | 79,330.32 |
| 2 | ጉ/ክ/ክ/02/18 | LDR-GUL-MIX-00014657 | ጉለሌ | 7 | 3/3 | 175 | LDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 408,333.33 | 81,186.00 |
| 3 | ጉ/ክ/ክ/03/18 | LDR-GUL-MIX-00014658 | ጉለሌ | 7 | 3/3 | 176 | MDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 410,666.67 | 81,649.92 |
| 4 | ጉ/ክ/ክ/04/18 | LDR-GUL-MIX-00015187 | ጉለሌ | 7 | 3/3 | 210 | LDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 490,000.00 | 97,423.20 |
| 5 | ጉ/ክ/ክ/05/18 | LDR-GUL-MIX-00015188 | ጉለሌ | 7 | 3/3 | 227 | LDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 529,666.67 | 105,309.84 |
| 6 | ጉ/ክ/ክ/06/18 | LDR-GUL-MIX-00015189 | ጉለሌ | 7 | 3/3 | 236 | LDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 550,666.67 | 109,485.12 |
| 7 | ጉ/ክ/ክ/07/18 | LDR-GUL-MIX-00015190 | ጉለሌ | 7 | 3/3 | 145 | MDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 338,333.33 | 67,268.40 |
| 8 | ጉ/ክ/ክ/07/18 | LDR-GUL-MIX-00015191 | ጉለሌ | 7 | 3/3 | 255 | MDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 595,000.00 | 118,299.60 |
| 9 | ጉ/ክ/ክ/07/18 | LDR-GUL-MIX-00015192 | ጉለሌ | 7 | 3/3 | 253 | MDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 590,333.33 | 117,371.76 |
| 10 | ጉ/ክ/ክ/07/18 | LDR-GUL-MIX-00015193 | ጉለሌ | 7 | 3/3 | 247 | MDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 576,333.33 | 114,588.24 |
| 11 | ጉ/ክ/ክ/07/18 | LDR-GUL-MIX-00015194 | ጉለሌ | 7 | 3/3 | 143 | MDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 333,666.67 | 66,340.56 |
| 12 | ጉ/ክ/ክ/07/18 | LDR-GUL-MIX-00015195 | ጉለሌ | 7 | 3/3 | 144 | MDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 336,000.00 | 66,804.48 |
| 13 | ጉ/ክ/ክ/07/18 | LDR-GUL-MIX-00015196 | ጉለሌ | 7 | 3/3 | 145 | MDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 338,333.33 | 67,268.40 |

| ተ.ቁ | የጨረታ ቁጥር | የቦታ ኮድ | ክ/ከተማ | ወረዳ | የቦታው ደረጃ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | የቦታው አገልግሎት | የህንፃ ከፍታ | የቦታው መነሻ ዋጋ | ቅድሚያ ክፍያ በ% | የችሮታ ጊዜ በአመት | የክፍያ ማጠናቀቂያ ጊዜ በአመት | የሊዝ ዘመን በአመት | የአቅም ማሳያ | ሲፒኦ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 14 | ጉ/ክ/ከ/07/18 | LDR-GUL-MIX-00015197 | ጉለሌ | 7 | 3/3 | 147 | MDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 343,000.00 | 68,196.24 |
| 15 | ጉ/ክ/ከ/07/18 | LDR-GUL-MIX-00015198 | ጉለሌ | 7 | 3/3 | 148 | MDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 345,333.33 | 68,660.16 |
| 16 | ጉ/ክ/ከ/07/18 | LDR-GUL-MIX-00015199 | ጉለሌ | 7 | 3/3 | 237 | MDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 553,000.00 | 109,949.04 |

## በልደታ ክ/ክተማ 8ኛው ዙር የመሬት ሊዝ ጨረታ የወጡ ቦታዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የጨረታ ቁጥር | የቦታ ኮድ | ክ/ከተማ | ወረዳ | የቦታው ደረጃ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | የቦታው አገልግሎት | የህንፃ ከፍታ | የቦታው መነሻ ዋጋ | ቅድሚያ ክፍያ በ% | የችሮታ ጊዜ በአመት | የክፍያ ማጠናቀቂያ ጊዜ በአመት | የሊዝ ዘመን በአመት | የአቅም ማሳያ | ሲፒኦ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ል/ክ/ከ/01/18 | LDR-LID-MIX-00015282 | ልደታ | 8 | 1/2 | 642 | MDMR | max G+12 | 2165.47 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,947,400.00 | 695,115.87 |
| 2 | ል/ክ/ከ/02/18 | LDR-LID-MIX-00015283 | ልደታ | 8 | 1/2 | 500 | MDMR | max G+12 | 2165.47 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,516,666.67 | 541,367.50 |
| 3 | ል/ክ/ከ/03/18 | LDR-LID-MIX-00015284 | ልደታ | 8 | 1/2 | 451 | MDMR | max G+12 | 2165.47 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,368,033.33 | 488,313.49 |
| 4 | ል/ክ/ከ/04/18 | LDR-LID-MIX-00015285 | ልደታ | 8 | 1/2 | 500 | MDMR | max G+12 | 2165.47 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,516,666.67 | 541,367.50 |
| 5 | ል/ክ/ከ/05/18 | LDR-LID-MIX-00015286 | ልደታ | 8 | 1/2 | 542 | MDMR | max G+12 | 2165.47 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,644,066.67 | 586,842.37 |
| 6 | ል/ክ/ከ/06/18 | LDR-LID-MIX-00015287 | ልደታ | 8 | 1/2 | 801 | MDMR | max G+12 | 2165.47 | 40 | 2 | 5 | 60 | 2,429,700.00 | 867,270.74 |
| 7 | ል/ክ/ከ/07/18 | LDR-LID-MIX-00015288 | ልደታ | 8 | 1/2 | 1097 | MDMR | max G+12 | 2165.47 | 40 | 2 | 5 | 60 | 3,327,566.67 | 1,187,760.30 |
| 8 | ል/ክ/ከ/08/18 | LDR-LID-MIX-00015289 | ልደታ | 8 | 1/2 | 586 | MDMR | max G+12 | 2165.47 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,777,533.33 | 634,482.71 |
| 9 | ል/ክ/ከ/09/18 | LDR-LID-MIX-00015290 | ልደታ | 8 | 1/2 | 570 | MDMR | max G+12 | 2165.47 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,729,000.00 | 617,158.95 |
| 10 | ል/ክ/ከ/10/18 | LDR-LID-MIX-00015291 | ልደታ | 8 | 1/2 | 657 | MDMR | max G+12 | 2165.47 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,992,900.00 | 711,356.90 |

## በለሚ ኩራ ክ/ክተማ 8ኛው ዙር የመሬት ሊዝ ጨረታ የወጡ ቦታዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የጨረታ ቁጥር | የቦታ ኮድ | ክ/ከተማ | ወረዳ | የቦታው ደረጃ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | የቦታው አገልግሎት | የህንፃ ከፍታ | የቦታው መነሻ ዋጋ | ቅድሚያ ክፍያ በ% | የችሮታ ጊዜ በአመት | የክፍያ ማጠናቀቂያ ጊዜ በአመት | የሊዝ ዘመን በአመት | የአቅም ማሳያ | ሲፒኦ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ለ/ሚ/ክ/ከ/01/18 | LDR-LIMK-MIX-00014732 | ለሚ ኩራ | 4 | 2/4 | 306 | LDMR | max G+9 | 1074.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 714,000.00 | 164,381.67 |
| 2 | ለ/ሚ/ክ/ከ/02/18 | LDR-LIMK-MIX-00014733 | ለሚ ኩራ | 4 | 2/4 | 217 | LDMR | max G+9 | 1074.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 506,333.33 | 116,571.32 |
| 3 | ለ/ሚ/ክ/ከ/03/18 | LDR-LIMK-MIX-00014776 | ለሚ ኩራ | 4 | 2/4 | 326 | LDMR | max G+9 | 1074.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 760,666.67 | 175,125.57 |
| 4 | ለ/ሚ/ክ/ከ/04/18 | LDR-LIMK-MIX-00014778 | ለሚ ኩራ | 4 | 2/4 | 306 | LDMR | max G+9 | 1074.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 714,000.00 | 164,381.67 |
| 5 | ለ/ሚ/ክ/ከ/05/18 | LDR-LIMK-MIX-00014780 | ለሚ ኩራ | 4 | 2/4 | 256 | LDMR | max G+9 | 1074.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 597,333.33 | 137,521.92 |
| 6 | ለ/ሚ/ክ/ከ/06/18 | LDR-LIMK-MIX-00014784 | ለሚ ኩራ | 4 | 2/4 | 272 | LDMR | max G+9 | 1074.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 634,666.67 | 146,117.04 |
| 7 | ለ/ሚ/ክ/ከ/07/18 | LDR-LIMK-MIX-00014786 | ለሚ ኩራ | 4 | 2/4 | 268 | LDMR | max G+9 | 1074.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 625,333.33 | 143,968.26 |
| 8 | ለ/ሚ/ክ/ከ/08/18 | LDR-LIMK-MIX-00014741 | ለሚ ኩራ | 4 | 2/4 | 300 | LDMR | max G+9 | 1074.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 700,000.00 | 161,158.50 |
| 9 | ለ/ሚ/ክ/ከ/09/18 | LDR-LIMK-MIX-00014742 | ለሚ ኩራ | 4 | 2/4 | 395 | LDMR | max G+9 | 1074.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 921,666.67 | 212,192.03 |
| 10 | ለ/ሚ/ክ/ከ/10/18 | LDR-LIMK-MIX-00014743 | ለሚ ኩራ | 4 | 2/4 | 335 | LDMR | max G+9 | 1074.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 781,666.67 | 179,960.33 |
| 11 | ለ/ሚ/ክ/ከ/11/18 | LDR-LIMK-MIX-00014746 | ለሚ ኩራ | 4 | 2/4 | 313 | LDMR | max G+9 | 1074.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 730,333.33 | 168,142.04 |
| 12 | ለ/ሚ/ክ/ከ/12/18 | LDR-LIMK-MIX-00014771 | ለሚ ኩራ | 4 | 2/4 | 390 | LDMR | max G+9 | 1074.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 910,000.00 | 209,506.05 |
| 13 | ለ/ሚ/ክ/ከ/13/18 | LDR-LIMK-MIX-00014760 | ለሚ ኩራ | 4 | 2/4 | 389 | LDMR | max G+9 | 1074.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 907,666.67 | 208,968.86 |
| 14 | ለ/ሚ/ክ/ከ/14/18 | LDR-LIMK-MIX-00014798 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 200 | LDMR | max G+9 | 904.77 | 40 | 2 | 5 | 60 | 466,666.67 | 90,477.00 |
| 15 | ለ/ሚ/ክ/ከ/15/18 | LDR-LIMK-MIX-00015200 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 350 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 816,666.67 | 168,036.75 |
| 16 | ለ/ሚ/ክ/ከ/16/18 | LDR-LIMK-MIX-00015201 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 367 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 856,333.33 | 176,198.54 |
| 17 | ለ/ሚ/ክ/ከ/17/18 | LDR-LIMK-MIX-00015202 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 350 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 816,666.67 | 168,036.75 |
| 18 | ለ/ሚ/ክ/ከ/18/18 | LDR-LIMK-MIX-00015203 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 375 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 875,000.00 | 180,039.38 |
| 19 | ለ/ሚ/ክ/ከ/19/18 | LDR-LIMK-MIX-00015204 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 350 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 816,666.67 | 168,036.75 |
| 20 | ለ/ሚ/ክ/ከ/20/18 | LDR-LIMK-MIX-00015205 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 384 | LDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 896,000.00 | 178,145.28 |
| 21 | ለ/ሚ/ክ/ከ/21/18 | LDR-LIMK-MIX-00015206 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 350 | LDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 816,666.67 | 162,372.00 |
| 22 | ለ/ሚ/ክ/ከ/22/18 | LDR-LIMK-MIX-00015207 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 385 | LDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 898,333.33 | 178,609.20 |
| 23 | ለ/ሚ/ክ/ከ/23/18 | LDR-LIMK-MIX-00015208 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 350 | LDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 816,666.67 | 162,372.00 |
| 24 | ለ/ሚ/ክ/ከ/24/18 | LDR-LIMK-MIX-00015209 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 389 | LDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 907,666.67 | 180,464.88 |
| 25 | ለ/ሚ/ክ/ከ/25/18 | LDR-LIMK-MIX-00015210 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 350 | LDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 816,666.67 | 162,372.00 |
| 26 | ለ/ሚ/ክ/ከ/26/18 | LDR-LIMK-MIX-00015211 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 399 | LDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 931,000.00 | 185,104.08 |
| 27 | ለ/ሚ/ክ/ከ/27/18 | LDR-LIMK-MIX-00015212 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 350 | LDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 816,666.67 | 162,372.00 |
| 28 | ለ/ሚ/ክ/ከ/28/18 | LDR-LIMK-MIX-00015213 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 407 | LDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 949,666.67 | 188,815.44 |
| 29 | ለ/ሚ/ክ/ከ/29/18 | LDR-LIMK-MIX-00015214 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 350 | LDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 816,666.67 | 162,372.00 |
| 30 | ለ/ሚ/ክ/ከ/30/18 | LDR-LIMK-MIX-00015215 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 415 | LDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 968,333.33 | 192,526.80 |
| 31 | ለ/ሚ/ክ/ከ/31/18 | LDR-LIMK-MIX-00015216 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 350 | LDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 816,666.67 | 162,372.00 |
| 32 | ለ/ሚ/ክ/ከ/32/18 | LDR-LIMK-MIX-00015217 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 423 | LDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 987,000.00 | 196,238.16 |
| 33 | ለ/ሚ/ክ/ከ/33/18 | LDR-LIMK-MIX-00015218 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 519 | LDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,211,000.00 | 240,774.48 |
| 34 | ለ/ሚ/ክ/ከ/34/18 | LDR-LIMK-MIX-00015219 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 543 | LDMR | max G+9 | 927.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,267,000.00 | 251,908.56 |
| 35 | ለ/ሚ/ክ/ከ/35/18 | LDR-LIMK-MIX-00015220 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 240,052.50 |
| 36 | ለ/ሚ/ክ/ከ/36/18 | LDR-LIMK-MIX-00015221 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 240,052.50 |
| 37 | ለ/ሚ/ክ/ከ/37/18 | LDR-LIMK-MIX-00015222 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 240,052.50 |
| 38 | ለ/ሚ/ክ/ከ/38/18 | LDR-LIMK-MIX-00015223 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 240,052.50 |
| 39 | ለ/ሚ/ክ/ከ/39/18 | LDR-LIMK-MIX-00015224 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 240,052.50 |
| 40 | ለ/ሚ/ክ/ከ/40/18 | LDR-LIMK-MIX-00015225 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 431 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,005,666.67 | 206,925.26 |
| 41 | ለ/ሚ/ክ/ከ/41/18 | LDR-LIMK-MIX-00015226 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 430 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,003,333.33 | 206,445.15 |

| ተ.ቁ | የጨረታ ቁጥር | የቦታ ኮድ | ክ/ከተማ | ወረዳ | የቦታው ደረጃ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | የቦታው አገልግሎት | የህንፃ ከፍታ | የቦታው መነሻ ዋጋ | ቅድሚያ ክፍያ በ% | የችሮታ ጊዜ በአመት | የክፍያ ማጠናቀቂያ ጊዜ በአመት | የሊዝ ዘመን በአመት | የአቅም ማሳያ | ሲፒኦ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 42 | ለ/ሚ/ክ/ክ/42/18 | LDR-LIMK-MIX-00015227 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 430 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,003,333.33 | 206,445.15 |
| 43 | ለ/ሚ/ክ/ክ/43/18 | LDR-LIMK-MIX-00015228 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 429 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,001,000.00 | 205,965.05 |
| 44 | ለ/ሚ/ክ/ክ/44/18 | LDR-LIMK-MIX-00015229 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 429 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,001,000.00 | 205,965.05 |
| 45 | ለ/ሚ/ክ/ክ/45/18 | LDR-LIMK-MIX-00015230 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 240,052.50 |
| 46 | ለ/ሚ/ክ/ክ/46/18 | LDR-LIMK-MIX-00015231 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 240,052.50 |
| 47 | ለ/ሚ/ክ/ክ/47/18 | LDR-LIMK-MIX-00015232 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 240,052.50 |
| 48 | ለ/ሚ/ክ/ክ/48/18 | LDR-LIMK-MIX-00015233 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 240,052.50 |
| 49 | ለ/ሚ/ክ/ክ/49/18 | LDR-LIMK-MIX-00015234 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 240,052.50 |
| 50 | ለ/ሚ/ክ/ክ/50/18 | LDR-LIMK-MIX-00015235 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 240,052.50 |
| 51 | ለ/ሚ/ክ/ክ/51/18 | LDR-LIMK-MIX-00015236 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 240,052.50 |
| 52 | ለ/ሚ/ክ/ክ/52/18 | LDR-LIMK-MIX-00015237 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 240,052.50 |
| 53 | ለ/ሚ/ክ/ክ/53/18 | LDR-LIMK-MIX-00015238 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 240,052.50 |
| 54 | ለ/ሚ/ክ/ክ/54/18 | LDR-LIMK-MIX-00015239 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 240,052.50 |
| 55 | ለ/ሚ/ክ/ክ/55/18 | LDR-LIMK-MIX-00015240 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 240,052.50 |
| 56 | ለ/ሚ/ክ/ክ/56/18 | LDR-LIMK-MIX-00015241 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 240,052.50 |
| 57 | ለ/ሚ/ክ/ክ/57/18 | LDR-LIMK-MIX-00015242 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 240,052.50 |
| 58 | ለ/ሚ/ክ/ክ/58/18 | LDR-LIMK-MIX-00015243 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 | LDMR | max G+9 | 960.21 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 240,052.50 |
| 59 | ለ/ሚ/ክ/ክ/59/18 | LDR-LIMK-MIX-00015244 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 577 | LDMR | max G+9 | 904.77 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,346,333.33 | 261,026.15 |
| 60 | ለ/ሚ/ክ/ክ/60/18 | LDR-LIMK-MIX-00015245 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 490 | LDMR | max G+9 | 904.77 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,143,333.33 | 221,668.65 |
| 61 | ለ/ሚ/ክ/ክ/61/18 | LDR-LIMK-MIX-00015246 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 499 | LDMR | max G+9 | 904.77 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,164,333.33 | 225,740.12 |
| 62 | ለ/ሚ/ክ/ክ/62/18 | LDR-LIMK-MIX-00015247 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 490 | LDMR | max G+9 | 904.77 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,143,333.33 | 221,668.65 |
| 63 | ለ/ሚ/ክ/ክ/63/18 | LDR-LIMK-MIX-00015248 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 382 | LDMR | max G+9 | 904.77 | 40 | 2 | 5 | 60 | 891,333.33 | 172,811.07 |
| 64 | ለ/ሚ/ክ/ክ/64/18 | LDR-LIMK-MIX-00015249 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 292 | LDMR | max G+9 | 904.77 | 40 | 2 | 5 | 60 | 681,333.33 | 132,096.42 |
| 65 | ለ/ሚ/ክ/ክ/65/18 | LDR-LIMK-MIX-00015250 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 417 | LDMR | max G+9 | 904.77 | 40 | 2 | 5 | 60 | 973,000.00 | 188,644.55 |
| 66 | ለ/ሚ/ክ/ክ/66/18 | LDR-LIMK-MIX-00015251 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 468 | LDMR | max G+9 | 904.77 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,092,000.00 | 211,716.18 |
| 67 | ለ/ሚ/ክ/ክ/67/18 | LDR-LIMK-MIX-00015252 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 500 | LDMR | max G+9 | 904.77 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,166,666.67 | 226,192.50 |
| 68 | ለ/ሚ/ክ/ክ/68/18 | LDR-LIMK-MIX-00015253 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 636 | LDMR | max G+9 | 904.77 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,484,000.00 | 287,716.86 |
| 69 | ለ/ሚ/ክ/ክ/69/18 | LDR-LIMK-MIX-00015254 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 243 | LDMR | max G+9 | 904.77 | 40 | 2 | 5 | 60 | 567,000.00 | 109,929.56 |
| 70 | ለ/ሚ/ክ/ክ/70/18 | LDR-LIMK-MIX-00015255 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 264 | LDMR | max G+9 | 904.77 | 40 | 2 | 5 | 60 | 616,000.00 | 119,429.64 |
| 71 | ለ/ሚ/ክ/ክ/71/18 | LDR-LIMK-MIX-00015256 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 251 | LDMR | max G+9 | 904.77 | 40 | 2 | 5 | 60 | 585,666.67 | 113,548.64 |
| 72 | ለ/ሚ/ክ/ክ/72/18 | LDR-LIMK-MIX-00015257 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 239 | LDMR | max G+9 | 904.77 | 40 | 2 | 5 | 60 | 557,666.67 | 108,120.02 |
| 73 | ለ/ሚ/ክ/ክ/73/18 | LDR-LIMK-MIX-00015258 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 226 | LDMR | max G+9 | 904.77 | 40 | 2 | 5 | 60 | 527,333.33 | 102,239.01 |
| 74 | ለ/ሚ/ክ/ክ/74/18 | LDR-LIMK-MIX-00015259 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 517 | LDMR | max G+9 | 904.77 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,206,333.33 | 233,883.05 |
| 75 | ለ/ሚ/ክ/ክ/75/18 | LDR-LIMK-MIX-00015260 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 238 | LDMR | max G+9 | 904.77 | 40 | 2 | 5 | 60 | 555,333.33 | 107,667.63 |
| 76 | ለ/ሚ/ክ/ክ/76/18 | LDR-LIMK-MIX-00015261 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 269 | LDMR | max G+9 | 904.77 | 40 | 2 | 5 | 60 | 627,666.67 | 121,691.57 |
| 77 | ለ/ሚ/ክ/ክ/77/18 | LDR-LIMK-MIX-00015262 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 299 | LDMR | max G+9 | 904.77 | 40 | 2 | 5 | 60 | 697,666.67 | 135,263.12 |
| 78 | ለ/ሚ/ክ/ክ/78/18 | LDR-LIMK-MIX-00015263 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 330 | LDMR | max G+9 | 904.77 | 40 | 2 | 5 | 60 | 770,000.00 | 149,287.05 |
| 79 | ለ/ሚ/ክ/ክ/79/18 | LDR-LIMK-MIX-00015264 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 297 | LDMR | max G+9 | 904.77 | 40 | 2 | 5 | 60 | 693,000.00 | 134,358.35 |
| 80 | ለ/ሚ/ክ/ክ/80/18 | LDR-LIMK-MIX-00015265 | ለሚ ኩራ | 10 | 2/5 | 130 | LDMR | max G+9 | 1027.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 303,333.33 | 66,809.60 |
| 81 | ለ/ሚ/ክ/ክ/81/18 | LDR-LIMK-MIX-00015266 | ለሚ ኩራ | 10 | 2/5 | 130 | LDMR | max G+9 | 1027.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 303,333.33 | 66,809.60 |
| 82 | ለ/ሚ/ክ/ክ/82/18 | LDR-LIMK-MIX-00015267 | ለሚ ኩራ | 10 | 2/5 | 130 | LDMR | max G+9 | 1027.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 303,333.33 | 66,809.60 |

## በየካ ክ/ክተማ 8ኛው ዙር የመሬት ሊዝ ጨረታ የወጡ ቦታዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የጨረታ ቁጥር | የቦታ ኮድ | ክ/ከተማ | ወረዳ | የቦታው ደረጃ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ | የቦታው አገልግሎት | የህንፃ ከፍታ | የቦታው መነሻ ዋጋ | ቅድሚያ ክፍያ በ% | የችሮታ ጊዜ በአመት | የክፍያ ማጠናቀቂያ ጊዜ በአመት | የሊዝ ዘመን በአመት | የአቅም ማሳያ | ሲፒኦ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የካ/ክ/ክ/01/18 | LDR-YEKA-MIX-00014647 | የካ | 10 | 1/5 | 281 | LDMR | max G+9 | 1531.91 | 40 | 2 | 5 | 60 | 655,666.67 | 215,233.36 |
| 2 | የካ/ክ/ክ/02/18 | LDR-YEKA-MIX-00015268 | የካ | 1 | 2/5 | 295 | LDMR | max G+9 | 1027.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 688,333.33 | 151,606.40 |
| 3 | የካ/ክ/ክ/03/18 | LDR-YEKA-MIX-00015269 | የካ | 2 | 3/5 | 442 | MDMR | max G+9 | 873.74 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,031,333.33 | 193,096.54 |
| 4 | የካ/ክ/ክ/04/18 | LDR-YEKA-MIX-00015270 | የካ | 2 | 3/5 | 498 | MDMR | max G+9 | 873.74 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,162,000.00 | 217,561.26 |
| 5 | የካ/ክ/ክ/05/18 | LDR-YEKA-MIX-00015271 | የካ | 2 | 3/5 | 385 | MDMR | max G+9 | 873.74 | 40 | 2 | 5 | 60 | 898,333.33 | 168,194.95 |
| 6 | የካ/ክ/ክ/06/18 | LDR-YEKA-MIX-00015272 | የካ | 2 | 3/1 | 300 | LDMR | max G+9 | 994.71 | 40 | 2 | 5 | 60 | 700,000.00 | 149,206.50 |
| 7 | የካ/ክ/ክ/07/18 | LDR-YEKA-MIX-00015273 | የካ | 2 | 3/1 | 270 | LDMR | max G+9 | 994.71 | 40 | 2 | 5 | 60 | 630,000.00 | 134,285.85 |
| 8 | የካ/ክ/ክ/08/18 | LDR-YEKA-MIX-00015274 | የካ | 2 | 2/5 | 251 | LDMR | max G+9 | 1027.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 585,666.67 | 128,993.92 |
| 9 | የካ/ክ/ክ/09/18 | LDR-YEKA-MIX-00015275 | የካ | 2 | 2/5 | 263 | LDMR | max G+9 | 1027.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 613,666.67 | 135,160.96 |
| 10 | የካ/ክ/ክ/10/18 | LDR-YEKA-MIX-00015276 | የካ | 2 | 2/5 | 496 | LDMR | max G+9 | 1027.84 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,157,333.33 | 254,904.32 |
| 11 | የካ/ክ/ክ/11/18 | LDR-YEKA-MIX-00015277 | የካ | 2 | 1/5 | 376 | LDMR | max G+9 | 1531.91 | 40 | 2 | 5 | 60 | 877,333.33 | 287,999.08 |
| 12 | የካ/ክ/ክ/12/18 | LDR-YEKA-MIX-00015278 | የካ | 2 | 2/1 | 165 | LDMR | max G+9 | 1327.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 385,000.00 | 109,509.68 |
| 13 | የካ/ክ/ክ/13/18 | LDR-YEKA-MIX-00015279 | የካ | 2 | 2/2 | 92 | LDMR | max G+9 | 1221.18 | 40 | 2 | 5 | 60 | 214,666.67 | 56,174.28 |
| 14 | የካ/ክ/ክ/14/18 | LDR-YEKA-MIX-00015280 | የካ | 3 | 2/1 | 1219 | LDMR | max G+9 | 1327.39 | 40 | 2 | 5 | 60 | 2,844,333.33 | 809,044.21 |
| 15 | የካ/ክ/ክ/15/18 | LDR-YEKA-MIX-00015281 | የካ | 10 | 1/5 | 455 | LDMR | max G+9 | 1531.91 | 40 | 2 | 5 | 60 | 1,061,666.67 | 348,509.53 |

## ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ

# ይርጋ ምንድን ነው?

መሰረት ፀሐይ (ዐቃቤ ህግ)

የኢትዮጵያ ፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 1845 ይርጋን በአስር ዓመት ቢገድበውም፤ ይርጋ ምን ማለት እንደሆነ ትርጉሙን አላስቀመጠም። በመሆኑም ይርጋ የሚለው ቃል መነሻው "ረጋ" ከሚለው የአማርኛ ቃል ጋር የተያያዘ ሲሆን "ረጋ" የሚለውን ቃል ደራሲ ተሠማ ኃብተ ሚካኤል "ከሡቴ ብርሀን ተሰማ" በተሰኘውና በ2002 ዓ.ም. በድጋሚ ባሳተሙት የአማርኛ መዝገበ ቃላት ላይ "የሰው ሀሳቡ ከመውጣት ከመውረድ፣ በሀሳብ ከመዞር ከመባከን ከመናወጥ ጠጥ (ፀጥ) አለ" በሚል ትርጓሜ ተሠጥቶታል።

ከዚህ በመነሳትም "ይርጋ" የሚለውን ቃል በአንድ ጉዳይ ላይ ክስ የማቅረብ ወይም መብት የመጠየቅ ጉዳይን አስመልክቶ በጉዳዩ ላይ ክስ የሚያቀርብበት ሰው ስለ ጉዳዩ ያለውን ሀሳብ ከመውጣት፣ ከመውረድ፣ በሀሳብ ከመዞርና ከመባከን ከመናወጥ ከረጋ (ፀጥ) ካለ በኋላ ሊከሰስ ወይም ሊጠየቅ እንደማይገባ ያመለክታል በሚል ልንወስደው እንችላለን። በሌሎች ጽሑፎች ላይም ይርጋ ማለት አንድ መብቱ ወይም ጥቅሙ የተነካበት ሰው በሌላ ሰው ላይ ክስ፣ አቤቱታ ወይም የይገባኛል ጥያቄ እንዲያቀርብ በሕግ ተለይቶ የተቀመጠ የክስ (አቤቱታ) ማቅረቢያ ጊዜ ነው፡፡

## የይርጋ አስፈላጊነት/ጠቀሜታው/ እና ጉዳቱ

የይርጋ ፅንሰ ሃሳብ እንዲኖር ያስፈለገበት ሶስት መሠረታዊ ምክንያቶች እንዳሉ በተለያዩ ጽሑፎች ላይ ተመልክቷል። እነርሱም፡-

ሀ) ከሳሽ በተገቢ ትጋትና በቂ ምክንያት መብቱን እንዲጠይቅ ለማስቻል፤

ለ) ተከሳሽ በጣም ዘግይተው የሚመጡ ክሶችን ለመከላከል ማስረጃዎች እንዳያጣ ለማድረግ፤ እና

ሐ) እጅግ ዘግይተው የሚቀርቡ ክሶችና አቤቱታዎች ፍትህ ከማስገኘት ይልቅ በጭካኔ ለማጥቂያ መሳሪያነት ስለሚውሉ፤ ይህንኑ ለመከላከል ስለመሆኑ ይርጋን ስመልክቶ በተፃፉ በርካታ ጽሑፎች ላይ ተመልክቷል። በመሆኑም የይርጋ ፅንሰ ሃሳብ በሕግ ስርዓት ውስጥ መካተቱ ጠቀሜታው ለተከሳሽ ወገን ነው። ምክንያቱም ክስ የማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በኋላ ክስ የቀረበበት ተከሳሽ በኃላፊነት ተጠያቂ ሊሆን አይችልምና ነው፡፡

የይርጋ ፅንሰ ሃሳብ በሕግ ስርዓት ውስጥ መካተቱ ተከሳሹን የሚጠቅመውን ያህል በአንፃሩ የፅንሰ ሃሳቡ መኖር መብት ጠያቂውን ወይም ከሳሹን በእጅጉ የሚጎዳ ነው። በይርጋ ጊዜያት መለያየት፣ ትክክለኛ ተቀባይነት ያገኘ የሕግ ፅንሰ ሀሳብ ሆኗል።



## ክስ ለማቅረብ የሚቀመጡ የይርጋ ጊዜያት

ይርጋን አስመልክቶ በሕግ ውስጥ የሚካተቱ ድንጋጌዎች በዋናነት የሚያመላክቱት ክስ ለማቅረብ ወይም መብት ለመጠየቅ የሚቻልበትን የጊዜ ገደብ ነው፡፡ ክስ ለማቅረብ ወይም መብት ለመጠየቅ እንዲቻል በሕግ የሚቀመጠው የጊዜ ገደብም እንደ ጉዳዩ ክብደት፣ ባሕሪና ሁኔታ የተለያየ ሲሆን፤ ለሁሉም ጉዳዮች የተቀመጠ ተመሣሣይ የክስ ማቅረቢያ ወይም መብት የመጠየቂያ ጊዜ የለም። በመሆኑም ሕግ አውጪው እንደ ጉዳዩ ዓይነት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ክስ ለማቅረብ ወይም መብት ለመጠየቅ እንደሚቻል የተለያዩ የክስ ማቅረቢያ ጊዜያት በሕጎች ውስጥ ተካትተዋል፡፡

የፍትሐ ብሄር ህግ ቁጥር 1845 ስለ ይርጋ እንደሚከተለው ይደነግጋል "በህግ በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በቀር ውሉ እንዲፈጸም ወይም ከመፈጸሙ የተነሳ ስለሚደርስ ጉዳት ወይም ውሉ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት በ10 ዓመት ይርጋ ይቀራል" በውል ህግ ላይ በተጠቀሰው አኳኋን የተደነገገ ቢሆንም፤ በተለያዩ ህጎች የተለያዩ የይርጋ ጊዜዎች ተደንግገዋል ለምሳሌ፡- በውርስ ህግ 1000 "ከሳሽ መብቱንና የውርስ ንብረቶች በተከሳሽ መያዛቸውን ካወቀ ሶስት ዓመት ካለፈ ስለ ወራሽነት ጥያቄ የሚቀርበው ክስ ተቀባይነት ማግኘት አይችልም" በሚል የተደነገገ ሲሆን ከሳሹ በማናቸውም ሁኔታ በዘር የተወረሰ ርስት ካልሆነ በስተቀር ከ15 ዓመት በኋላ በይርጋ እንደሚታገድ ተደንግጓል፡፡

በንብረት ህግ አንድ ሰው የይዞታ መብት ክስ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ካላቀረበ በይርጋ እንደሚታገድ በፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 1149 ንዑስ አንቀጽ (2) ላይ ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም በዚሁ ህግ 1165 "አንድ ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ ነገር የተሰረቀበት ሰው ይህን እቃ በቅን ልቡና ባለሀብት ከሆነው ሰው ላይ የኔ ነው ብሎ ለመጠየቅ ክስ ለማቅረብ ይችላል"፤ "እቃው ከተሰረቀበት አንስቶ በ5 ዓመት ውስጥ ክስ ካላቀረበ የኔ ነው ብሎ ለመጠየቅ ክስ የማቅረብ መብቱን ያጣል" በተመሳሳይ በኢንሹራንስ ህግም ኢንሹራንስ የገባው ሰው ጉዳዩን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ ክስ ካላቀረበ ይርጋ መቃወሚያ እንደሚሆን ይታወቃል፡፡

ከውል ውጭ ኃላፊነት በሚደርስ ጉዳት ላይ በፍ/ህግ ቁጥር 2143 ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ እንደሚከተለው ተደንግጓል" ተበዳዩ ክስ ማቅረብ የሚችለው ካሳ የሚጠይቅበት ጉዳት ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ነው" ተጎጂው ክስ ማቅረብ ያለበት ጉዳት ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ ከፍ ሲል በተጠቀሰው ህግ የይርጋ ጊዜ የሚቆጠረው በፍ/ህግ ቁጥር 1846 እንደሚከተለው ተደንግጓል "የይርጋ ቀን መቁጠር የሚጀምረው ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ወይም ውሉ የሚሰጠው መብት ከተሰራበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡" ስለ ይርጋ ከላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ይርጋ የማይሠራባቸው ሁኔታዎች በፍ/ህግ ቁጥር 1851 ላይ ተደንግጓል፡፡ "ባለ እዳ እዳውን ሲያምን ይልቁንም ወለድ ወይም ከእዳው ላይ በከፊል ሰጥቶ ሲገኝ ወይም መያዢያ ወይም ዋስ የሰጠ እንደሆነ፤ ባለ ገንዘቡ መብቱ እንዲታወቅለት በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ለባለ እዳው አስታውቆ የተገኘ እንደሆነ ነው፡፡" በመሆኑም በገዛ ፈቃዱ እዳውን ያመነ እና ማስያዢያ ያቀረበ ተከሳሽ ክሱ በይርጋ እንዲታገድለት የሚያቀርበው መቃወሚያ እንደ ተተወ ይቆጠራል፡፡ ክፉ ልቦና የሚለው ስለ ይርጋ ከተደነገገው ድንጋጌ ልዩ ሁኔታ ያስቀመጠ ነው፡፡ ይህም ማለት አንድ ተከሳሽ የይርጋ ዘመኑ እንዳይቆጠርበት ከሳሽን በማታለል፣ ሆን ብሎ አድራሻን በመቀየር ወይም በከሳሽ ላይ የመክሰስ መብቱን እንዳይጠቀም ምክንያት በመሆን የይርጋ ጊዜ እንዲያልፍ ያደረገ እንደሆነ የይርጋ መብት እንደሚከለከል በፍ/ህ/ቁ.1845 ላይ የተገለጸ ሲሆን፤ በከሳሽና በተከሳሽ መካከል ቤተሰባዊ ግንኙነት ላይ ይርጋ እንደማይጸና በህጉ ተመላክቷል፡፡

በአጠቃላይ በፍ/ህግ፣ በአሰሪና ሰራተኛ ህግና በሲቪል ሰርቪስ ህጎች የተለያየ የይርጋ ጊዜዎች ተደንግገው ይገኛሉ። ስለሆነም የይርጋ መብት ተጠቃሚ የሆነ ሰው ጉዳዩን በአግባቡ በማቅረብ ለመከራከር ተጠቃሚ መሆን ይቻላል፡፡

## የይርጋ ጽንሰ ሀሳብ በፍ/ህግ እና በወንጀል ህግ

የይርጋ ጽንሰ ሀሳብ በፍትሐብሄር ህግ እና በወንጀል ህግ ተመሳሳይ ቢሆንም ውጤቱ ግን ይለያያል፡፡ ለምሳሌ በወንጀል ህግ ይርጋ በዳኞች የሚቀርብ ሀሳብ ሲሆን፤ በፍ/ህግ ግን በተከሳሽ ወይም በጠበቃው አማካኝነት የሚቀርብ መቃወሚያ ነው፡፡ በመሆኑም ተከሳሹ በይርጋ ክሱ ቀሪ እንዲሆንለት ካላመለከተ በቀር ፍ/ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት ሊያነሳው ስለማይችል ተከሳሽ የይርጋ መቃወሚያ ሳያነሳ ከቀረ በክስ ላይ ያለው ሂደት ቀጥሎ የተከሳሽን መብት ሊገድብ ይችላል፡፡

ከዚህ ባሻገርም በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ይርጋ ቀሪ እንደማይሆን የፍ/ ህጉ አንቀጽ 1855 ያስገነዝባል፡፡ ነገር ግን በይርጋ ተጠቃሚ የሆነው ሰው የሞላዉን ይርጋ ለመተዉ ወይም መብቱን አልጠቀምም ለማለት ይችላል፤ ስለሆነም የውል ህግ የይርጋ ጊዜ ከወንጀል ይርጋ እንደሚለያይና በተለያዩ ህጎች የተለያየ ውጤት እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡ በተለያዩ ህጎች የተለያዩ የይርጋ ጊዜዎች ሰፍረው ይገኛሉ

ከላይ እንደተጠቀሰው የፍ/ህግ እና የወንጀል ይርጋ የተለያዩ ውጤቶች አሏቸው፡፡ በኢትዮጵያ የወንጀል ህግ 1996 እንደተደነገገው የወንጀል ይርጋ ከቁጥር 216 – 229 ተዘርዝሯል፡፡ በመሆኑም በግል አቤቱታ በሚቀርብም ሆነ በሌላ ክስ የይርጋ ዘመን ካለፈ በኋላ ዳኝነት መስጠት እንደማይችል ተመላክቷል፡፡

የወንጀል ጉዳይ በተመለከተ ይርጋ በዓቃቤ ህግም ሆነ በዳኝነት መነሳት እንደሚችል የተደነገገ ሲሆን በፍ/ህግ ግን በተከሳሽ (የይርጋ ተጠቃሚ) ካልተነሳ በስተቀር በዳኝነት አነሳሽነት እንደማይነሳ ይታወቃል፡፡

በልዩ የወንጀል ህጉ የተጠቀሱት የይርጋ ጊዜዎች እንደተጠበቁ ሆነው የተለያዩ የይርጋ ጊዜዎች በወንጀል ህጉ ቁጥር 217 የተለያዩ የይርጋ ጊዜዎች ተመላክተዋል፡፡

ሀ/ የሞት ፍርድ ወይም የእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል ሃያ አምስት ዓመት

ለ/ ከአስር ዓመት በላይ እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት ለሚያስቀጣ ሃያ ዓመት

ሐ/ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አስር ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት ለሚያስቀጣ አስራ አምስት ዓመት

መ/ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል አስር ዓመት

ሠ/ ከአንድ ዓመት በላይ በቀላል እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል አምስት ዓመት

ረ/ እስከ አንድ ዓመት በቀላል እስራት ለሚያስቀጣ ወይም በመቀጮ ብቻ ለሚያስቀጣ ወንጀል ሶስት ዓመት

የወንጀል ይርጋ ከፍ/ህግ የሚለዩት ሁለት ከባድ ወንጀሎች ተፈጽመው ሲገኙ የአንዱ ከባድ ወንጀል የሚያዝ መሆኑና የተለያዩ ወንጀሎች ተፈጽመው ከሆነ ከሁሉም በሚበልጠው ወንጀል የሚያስቀጣው ብቻ የሚፈጸም መሆኑ ነው፡፡

ሌላው የወንጀል ይርጋ በቅጣትና በጥንቃቄ እርምጃ ላይ ተፈጻሚ መሆኑ ነው፡፡ አንድ የተፈረደበት (የጥንቃቄ እርምጃ) የተወሰደበት ሰው የይርጋ ጊዜ ከተቆጠረበት ጀምሮ ቅጣቱ ወይም የጥንቃቄ እርምጃው ተፈጻሚነት አይኖረውም (ቁጥር 223)፡፡

ይርጋ የሚታገድበት ሁኔታዎች እንዳለ በህጉ ተመላክቷል፡፡ በአጠቃላይ ይርጋ ለተከሳሹ ጠቃሚ መሆኑ ይታወቃል። በወንጀል ህግ የፍትህ መጓደል ስለሚያስከትል በዐቃቢ ህግ ወይም በዳኛ ይርጋ ክርክር ሊነሳ ይችላል፡፡ በፍ/ህግ ግን ተከሳሽ ወይም ጠበቃው ካላነሱት በስተቀር በሌላ አካል ስለማይነሳ የተከሰሰው ወገን ይህን መብቱን ካላወቀው እዳውን እንዳመነ ተቆጥሮ ግዴታውን መወጣት እንዳለበት ይታመናል፡፡

# ማሽን አምራቹ ማሽን

**በደረጀ ታደሰ**

በ6 ሰዓት ቻርጅ ለ1 ወር 50 አምፖሎችን የሚያበራ ድምጽ አልባ ጄኔሬተር ስለ ሠራው ኢትዮጵያዊ ወጣት ከሰሞኑ የተሰራጨው መረጃ ብዙዎችን ማስደነቁ አልቀረም፡፡ ይህ ወጣት ፈደሳ ሹማ ይባላል፡፡ ለአዳዲስ ሃሳብ እና ቴክኖሎጂ ፈጠራ የታደለው ወጣቱ ከድምጽ አልባ ጄነሬተሩ በተጨማሪ 47 የሚደርሱ የተለያዩ የፈጠራ ሥራዎችን ዕውን አድርጓል። በሥራዎቹም ከአገር አልፎ በዓለም አቀፍ መድረክ ላይ በመቅረብ እውቅናና ሽልማትን አግኝቷል። ከዚህ ጋር በተያያዘ በ2007 ዓ.ም በቻይና ቲያንጂን ከተማ በተካሄደው ዓለም አቀፍ ውድድር ላይ የኤሌክትሪክ ችግርን የሚፈታ የፈጠራ ሥራ አቅርቦ ከአፍሪካ 1ኛ፣ ከዓለም ደግሞ 9ኛ ደረጃን ይዞ ያጠናቀቀበት ተሳትፎው ይጠቀሳል፡፡

እንደ ወጣት ፈደሳ ሹማ ዓይነት፣ እጅን በአፍ የሚያስጭኑ አዳዲስ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤቶችን ዕውን ማድረግ የቻሉ በርካታ ትንታግ ኢትዮጵያውያን በብዛት አሉ፡፡ ሥራቸው የመገናኛ ብዙሃን ትኩረት ካገኙላቸው ጥቂት ባለ ተሰጥኦዎች ጀምሮ፣ በየትምህርት እና የሙያ ማሰልጠኛ ተቋማቱ፣ የምርምር ማዕከላቱ፣ በግል ቤተ-ሙከራዎች (ወርክሾፖች)፣ በየጓዳ ጎድጓዳው አጃይብ የሚያሰኙ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች የሠሩትን ቤቱ ይቁጠራቸው። ለአካባቢ፣ ለከተማ፣ ለአገር አለፍ ሲልም ለዓለም ውስብስብ ችግር መፍትሄ ሊሰጡ የሚችሉ የታወቁም ሆነ የተደበቁ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች ገሃድ ወጥተው ለውጤት የሚበቁበትን ዕድል ማመቻቸት የዘርፉ ወሳኝ ተግባር ነው፡፡

ከላይ ያነሳነው ሃሳብ መንደርደሪያ በማድረግ፤ የአዳዲስ ቴክኖሎጂ መፍጠሪያ ማዕከላት ከሆኑት የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት መካከል በአዲስ አበባ ተግባረ ዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ተሠርቶ ለአገልግሎት የበቃውን አንድ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤት ለማስቃኘት ወደድን። ቴክኖሎጂው ሲኤንሲ ፕላዝማ ማሽን የሚባል ሲሆን፤ የተለያየ የውፍረት መጠን ያላቸውን ብረቶች በተፈለገው ዓይነት ዲዛይን (ንድፍ) መቁረጥ፣ መብሳት፣ ቅርፅ ማውጣት የሚችል ነው። በኮሌጁ ለተቋቋመው ኢንተርፕራይዝ ውስጣዊ ችግርን ለመፍታት ታስቦ፣ የኮሌጁን አሠልጣኞች ዕውቀትና ክህሎት ተጠቅሞ፣ በአነስተኛ ወጪ ተሠርቶ ለአገልግሎት የበቃው ይህ ማሽን፤ ብዙ የፈጠራ ውጤቶች የሚያጋጥማቸውን “የጋን ውስጥ መብራት” ሆኖ በመጋዘን (ስቶር) መቀመጥን ተሻግሯል፡፡

በአዲስ አበባ ተግባረ ዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የማኑፋክቸሪንግ ክፍል አሰልጣኝ መልኩ አበበ፣ ሲኤንሲ ፕላዝማ ማሽን ፈጠራ ላይ ከተሳተፉ እና ጉልህ ሚና ከተወጡ ተስፈኛ ሙያተኞች አንዱ ነው፡፡ ወጣቱ አሰልጣኝ ከዚህ ቀደም በኮሌጁ ተሠርተው በተዋወቁ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች (ለአብነት፡- የዘይት ማቀነባበሪያ፣ የወርቅ ማጣሪያ፣ የ3ዲ የህትመት ማሽኖች ...) ላይ ሙያዊ አሻራውን አሳርፏል፡፡ አሰልጣኝ እና የፈጠራ ባለሙያው ከጋዜጣችን ጋር በነበረው ቆይታ ስለ አዲሱ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ጥልቅ ሃሳብና አስተያየት አጋርቶናል፡፡

አሰልጣኝ እና የፈጠራ ባለሙያው መልኩ አበበ እንዳስረዳው፤ ሲኤንሲ (CNC – Computer Numerical control) ስሙ እንደሚያመለክተው፡- ማሽኑ ተግባሩን የሚከውነው በኮምፒዩተር በሚሰጠው ኮድ አማካኝነት ነው፡፡ መጀመሪያ ማሽኑ እንዲሠራ የሚፈልገውን ሥራ ዲዛይን በመንደፍ ወደ ኮምፒዩተር የኮድ ቋንቋ ይለወጣል። ኮዶቹን የተቋሙ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ወደሆነው ሲኤንሲ ፕላዝማ ማሽን ይገባል፡፡ በኮምፒውተር ትዕዛዝ ማሽኑ ከስስ ላሜራ ጀምሮ እስከ 20 ሚሊ ሜትር የሚደርስ ውፍረት ያላቸውን ብረቶች በሚፈለገው ዓይነት ዲዛይን ይቆርጣል፣ ይበሳል፣ ቅርፅ ያወጣል፡፡

በ2017 የትምህርት ዘመን የተሠራው ቴክኖሎጂው፤ የፈጠራ ሃሳብ የመጣው ለችግር መፍትሄ ለመስጠት በሚደረግ ጥረት ውስጥ እንደሆነ አሰልጣኝ እና የፈጠራ ባለሙያው መልኩ አስታውሷል። ይህንንም ያብራራው፤ “ከዚህ በፊት በኮሌጁ የተሠሩትን በርካታ የፈጠራ ውጤቶች ለመሥራት በግብዓትነት የሚያገለግሉ ብረቶችን እና ላሜራዎችን በተዘጋጀው ዲዛይን መሰረት ለመቁረጥ ወይም ለመብሳት በውስጥ አቅም የማይቻል ነበር፡፡ ለዚህ መፍትሄ ከተቋም ውጪ ሌሎች ተቋማትን፣ ድርጅቶችን ወይም ግለሰቦችን እገዛ መጠየቅ ግድ ይል ነበር፡፡ ይህ አልሳካ ሲል ደግሞ፤ የተዘጋጀውን የወረቀት ላይ ዲዛይን ብረቱ ላይ በመሳል፣ የብረት መቁረጫ (ግራይንደር) ተጠቅሞ የሚፈልጉትን ቅርፅ ለማውጣት ጥረት ይደረግ ነበር። እነዚህ ጥረቶች በራሳቸው ውጤት ያመጡ ቢሆንም፤ ጥራት፣ ፍጥነት፣ ምርማነት የመሳሰሉትን ወሳኝ የቴክኖሎጂ አላባዊያን ያሟሉ አልነበሩም” በማለት ነው፡፡

“ችግር ብልሃትን ይወልዳል” እንደሚባለው ሁሉ፤ በተግባረ ዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ብረትን በግብዓትነት ተጠቅመው በሚሠሩ ቴክኖሎጂዎች ውጤታማነት እንቅፋት የሆነውን ችግር መፍታት ወሳኝ መሆኑን የተገነዘቡት የተቋሙ አሰልጣኞች እና የአመራር ስብስብ፤ የብረት መቁረጫ፣ መብሻ እና ቅርፅ ማውጫ ማሽን በራስ አቅም በመሥራት ለአገልግሎት ማብቃት ተገቢነት ላይ ስምምነት ደረሱ፡፡ ከዚያም አስፈላጊው የጥናት ሰነድ ተዘጋጅቶ ቴክኖሎጂውን በራስ አቅም ወደ መሥራት ተገባ፡፡ በመጨረሻም አስደናቂው ማሽን ከተሟላ ተግባሩ ጋር ዕውን ሆነ፡፡

በአዲስ አበባ ተግባረ ዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ተሠርቶ ለአገልግሎት የበቃው የሲኤንሲ ፕላዝማ ማሽን፤ የአልጋ ቅርፅ ያለው ሲሆን፤ ስፋቱ 3 ሜትር በ1 ነጥብ 5 ሜትር ነው፡፡ የሚጠቀመው የኤሌክትሪክ ኃይል ሲሆን፤ ብረትን ለመቁረጥ የሚያስችለውን በሙያ ቋንቋ አጠራር ፕላዝማ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው። አጠቃላይ ማሽኑን ለመሥራት 1 ነጥብ 8 ሚሊዮን ብር ወጪ ተደርጎበታል። 2 ነጥብ 8 ሚሊዮን ብር የመሸጫ ዋጋ ተተምኖለታል፡፡ ይህንን ማሽን ከውጭ እናስገባ ቢባል ከ5 ሚሊዮን ብር በላይ ይፈጃል፡፡



ፎቶ- በገነት ወንድሙ

በአዲስ አበባ ተግባረ ዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በተሠራው ሲኤንሲ ፕላዝማ ማሽን ፈጠራ ላይ ከተሳተፉት መካከል የማኑፋክቸሪንግ ክፍል አሰልጣኝ መልኩ አበበ

ቴክኖሎጂው በአዲስ አበባ ተግባረ ዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ውስጥ ወሳኝ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን የጠቆሙት አሰልጣኝ እና የፈጠራ ባለሙያው መልኩ፤ “ከዚህ ቀደም ብረት ነክ የሆኑ ግብዓቶችን ወደ ተለያየ ዓይነት ቅርፅ ለመለወጥ ይታለፍ የነበረውን የመቁረጥ፣ የመብሳት እና ቅርፅ የማውጣት አድካሚ ሥራ አስቀርቷል፡፡ በአንፃሩ በፍጥነት፣ በጥራት፣ ወጪና ጉልበት በሚቆጥብ ሁኔታ ማከናወን ችሏል፡፡ በቀላል አነጋገር ይህ ማሽን ብረትን እንደ ወረቀት እየበሳ፣ እየቆረጠ፣ እየቀረፀ በቀላሉ ወደ ፈለግነው ዓይነት ውጤት መለወጥ እያስቻለን ነው” ብሏል፡፡

አክሎ እንዳብራራው፤ ማሽኑ ለብረታ ብረት እና መሰል የማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች ትልቅ አቅም መፍጠር የሚችል ነው፡፡ ብረትን እና ሌሎች ግብዓቶችን ተጠቅመው የቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤቶችን ዕውን ለማድረግ ፍላጎት ላላቸው ሙያተኞች ትልቅ እገዛ ያደርጋል፡፡ ጌጣ ጌጦችን የሚሠሩ ሙያተኞችንም ችግር በእጅጉ የሚፈታ፣ የሥራ ጥራታቸውን ውጤታማነት ከፍ የሚያደርግ ነው፡፡ አንዳንዶች የሲኤንሲ ፕላዝማ ማሽን ለተለያዩ ቴክኖሎጂ ፈጠራዎች ያለውን አስፈላጊነት ሲገልፁት፤ ‘ማሽንን የሚያመርት ማሽን’ ይሉታል። ለምሳሌ ለግብርና ሥራ የሚያገለግሉ፡- ማረሻ፣ መኮትኮቻ፣ ማጨጃያ፣ መውቂያ የመሳሰሉትን ማሽኖች ለመሥራት ቢፈለግ፤ ለማሽኖቹ የሚያስፈልገውን ብረት በተዘጋጀው ዲዛይን አማካኝነት በፍጥነት፣ በጥራት እና በብዛት በማምረት ማሽኖቹን ለመሥራት ያግዛል፡፡

የሲኤንሲ ፕላዝማ ማሽን ለብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ዕድገት ቁልፍ አቅም ስለመስጠቱ፤ በተግባረ ዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ኢንተርፕራይዝ ውስጥ እያበረከተ ያለውን የምርታማነት እሴት ለውጥ ማሳያ ነው፡፡ በፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የማኑፋክቸሪንግ ክፍል አሰልጣኝ እና የአዲስ አበባ ተግባረ ዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ኢንተርፕራይዝ ሥራ አስኪያጅ የሆኑት ዘሪሁን አየለ፤ በኮሌጁ የውስጥ አቅም የተሠራው እና ወደ ኢንተርፕራይዙ የተሸጋገረው ሲኤንሲ ፕላዝማ ማሽን እያበረከተላቸው ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ስለመሆኑ መስክረዋል፡፡

ከሁለት ዓመት በፊት ሕጋዊ አሠራርን ተከትሎ የተቋቋመው የተግባረ ዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ኢንተርፕራይዝ በዋናነት በእንጨት፣ በብረታ ብረት፣ በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት እንዲሁም በሌሎች የስልጠና ዘርፎች ያሉትን አቅም በመጠቀም ምርቶችን እያመረተ ለገበያ የማቅረብ ዓላማን በመያዝ እየሠራ እንደሚገኝ ያነሱት ሥራ አስኪያጁ፤ በአሁኑ ወቅት በብረታ ብረት እና እንጨት ምርቶች ላይ በተሻለ ሁኔታ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በዚህ ሥራ ውጤታማነት ላይ በኮሌጁ የውስጥ አቅም ተሠርቶ፣ ለኢንተርፕራይዙ በመሸጋገር ለአገልግሎት የበቃው የሲኤንሲ ፕላዝማ ማሽን ከፍተኛ ጠቀሜታ እየሰጣቸው መሆኑን ተናግረዋል፡፡

እንደ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጁ ኢንተርፕራይዝ ሥራ አስኪያጅ ዘሪሁን ገለጻ፤ የሲኤንሲ ፕላዝማ ማሽን ለተለያዩ የብረት ሥራዎች አጋዥ የሆነ ቴክኖሎጂ ነው፡፡ ከዚህ በፊት ትላልቅ መጠን ያላቸውን ብረቶች ለመቁረጥ፣ ለመብሳት፣ ቅርፅ ለመስጠት በጣም አስቸጋሪ ነበር። ይህንን ችግር ለመፍታት በግራይንደር በመቁረጥ እና በመበየድ ለመሥራት ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጂ ሥራው ከፍጥነት፣ ከጥራት፣ ከምርታማነት እና ከውበት አንፃር የሚጠበቀውን ያክል አልነበረም፡፡ አሁን ላይ ይህ ማሽን በኮሌጁ አቅም ተሠርቶ ለኢንተርፕራይዙ በመሸጋገሩ ቀደም ሲል ይታይ የነበረውን ችግር በከፍተኛ ሁኔታ ተቀርፏል፡፡ በቴክኖሎጂው በርካታ ምርቶችን ማምረት ተችሏል፡፡ ለአብነት በኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን ቅጥር ግቢ ውስጥ የተገጠሙት ዘመናዊና ጠንካራ ከብረት የተሠሩ የቆሻሻ ማስወገጃዎች በብዛት፣ ጥራትና ውበት ባለው መልኩ የተሠሩትን ቴክኖሎጂውን በመጠቀም መሆኑን ማንሳት ይቻላል፡፡

የሲኤንሲ ፕላዝማ ማሽን (ቴክኖሎጂ) እንዲሸጋገርላቸው ለአዲስ አበባ ተግባረዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ጥያቄ ካቀረቡ ኢንተርፕራይዞች መካከል የአቢሲኒያ ፍሌክሲብል ሜታል ኢንጂነሪንግ አንዱ ነው፡፡

የድርጅቱ የቦርድ ሰብሳቢ አቶ ተሾመ ተረፈ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት ማብራሪያ፤ ተቋሙ ከውጭ የሚገቡ የቴክኖሎጂ ምርቶችን በአገር ውስጥ ለማምረት ጥረት እያደረገ ነው፡፡ በሥራው ውጤታማ ለመሆን በቴክኖሎጂ ፈጠራና ልማት ላይ ትኩረት አድርገው ከሚንቀሳቀሱ የትምህርትና የምርምር ተቋማት ጋር በቅርበት እየሰራ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ተቋማት መካከል የአዲስ አበባ ተግባረዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ አንዱ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በኮሌጁ የተሠራውንና ለበርካታ ማሽኖች መሥሪያ አቅም የሚፈጥረውን የሲኤንሲ ፕላዝማ ማሽን (ቴክኖሎጂ) ሽግግር ለማድረግ የሁለትዮሽ ስምምነት ተደርሷል ብለዋል።

“ማሽኑ እንዲሸጋገርልን ፍላጎት የፈጠረብን ለምንሠራው ሥራ በጣም አስፈላጊ የሆነ፣ ከውጪ አገር ቢገባ ከፍተኛ ወጪ የሚያስወጣ፣ በእኛ ቢመረት ለሌሎች መሰል ኢንዱስትሪዎች አቅም የሚፈጥር በመሆኑ ነው” ያሉት አቶ ተሾመ፤ ከኮሌጁ ጋር የሰነድ ውል ስምምነት ማድረጋቸውን አስረድተዋል፡፡

በከተማ አስተዳደር እና በፌደራል ደረጃ በተዘጋጁ በቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ሳምንት ላይ ለዕይታ በመቅረብ ሽልማቶችን እና ማበረታቻዎችን ያገኘው የሲኤንሲ ፕላዝማ ማሽን በመዲናዋ የሚገኙ በብረታ ብረት ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች እንዲሠራላቸው ለአዲስ አበባ ተግባራ ዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ጥያቄ እያቀረቡ እንደሚገኙ ካነጋገርናቸው አሰልጣኝና አመራሮች ማወቅ እና ከላይ የተጠቀሰውን ድርጅት በአስረጂነት መጥቀስ ይቻላል። እንዲህ ዓይነቱ ቴክኖሎጂዎች ወደ አገልግሎት የመግባት ሁኔታ፤ ለበለጠ ሥራ የሚያነሳሳ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ በኮሌጁ የሚሠሩ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤቶች በብዙ መመዘኛ ሲታዩ ከጊዜ ወደ ጊዜ በመሻሻል ሂደት ላይ መሆናቸው ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል። ይህንን ውጤታማነት አጠናክረው በያዝነው የ2018 የትምህርት ዘመን በሚሠሩ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤቶች ለማሳየት በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛሉ፡፡

# መንገድ... ከገጽ 1 የዞረ



ፎቶ -በገነት ወንድሙ

በኮልፌ ሁለገብ የገበያ ማዕከል ግብይት ሲከናወን

ለማሳደግ ታልሞ የተገነቡ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ማዕከላት መካከል ኮልፌ ሁለገብ የገበያ ማዕከል አንዱ ነው፡፡

አዲስ ልሳን ጋዜጣ ቅዳሜ ጥቅምት 15 ቀን 2018 ዓ.ም "የተደበቀው የማዕከሉ አገልግሎት" በሚል ርዕስ ከቤተል ወደ ማዕከሉ የሚወስደው የመንገድ መሰረተ ልማት ባለመጠናቀቁ ምክንያት ትራንስፖርት ወደ ማዕከሉ እንደማይገባና ለግብይት ሂደቱም ማነቆ ሆኖ እንደነበር መዘገቡ ይታወሳል፡፡ በዚህ የተነሳ ነጋዴዎች ሱቃቸውን ዘግተው እስከመውጣት መድረሳቸውን በወቅቱ መገለጹ ይታወሳል፡፡

የመንገድ መሰረተ ልማቱ ችግሩ ምን ያህል እንደተፈታ እና የግብይት ሁኔታው ምን እንደሚመስል በድጋሚ ቅኝት ያደረገው የጋዜጣው ዝግጅት ክፍል መንገዱ ተጠናቅቆ ስራ መጀመሩንና የትራንስፖርት አገልግሎትም ወደ ማዕከሉ መግባት መቻሉን ተመልክቷል። የመሰረተ ልማቱ መከናወን ማዕከሉ እየሰጠ ያለው የግብይት አገልግሎት እንዲሳለጥ ከማድረግ አንጻር ያለውን አበርክቶ ሸማቾችንና ነጋዴዎችን አነጋግሯል፡፡

ወጣት ልኡል ታያቸውን ያገኘነው በማዕከሉ ሽንኩርት፣ ካሮት እንዲሁም ጎመን ሲሸምት ነው፡፡ "በየጊዜው እየመጣሁ የምፈልገውን ነገር ለቤተሰቦቼ እየገዛሁ እወስዳለሁ፡፡ የሚቀርቡት የፍጆታ ምርቶች ጥራት ያላቸውና ትኩስ ናቸው፤ ዋጋውም ቢሆን ውጭ ላይ ከሚገዛው ቅናሽ አለው፤ ይህንን እድል በሚፈለገው ልክ ለመጠቀም አስቸግሮን የቆየው ከቤተል ወደ ማዕከሉ የሚወስደው መንገድ የትራንስፖርት አገልግሎት አለመኖር ነበር፡፡ ሁሉንም ነገር ገዝቼ መሄድ እፈልግና ትራንስፖርት አለመኖሩን ሳስብ እቸገር ነበር" ሲል የሚያስታውሰው ወጣት ልኡል፤ በአሁኑ ወቅት መንገዱ ተስተካክሎ አገልግሎት እየሰጠ እንደሆነ፣ እሱም አቅሙ የሚፈቅደውን ያህል መግዛቱንና በዚህም ደስተኛ መሆኑን አብራርቷል፡፡

ሌላኛዋ በማዕከሉ ግብይት ሲያደርጉ ያገኘናቸው ወይዘሮ ትዕግስት ነጋሽ ናቸው፡፡ ማዕከሉ ስራ ከጀመረ ጀምሮ የሚፈልጉትን ነገር ሸምተው እንደሚሄዱም ነግረውናል፡፡ ከዚህ በፊት ከማዕከሉ ሸምተው ወደ ቤታቸው ለመመለስ የትራንስፖርት ችግር ይገጥማቸው እንደነበር የሚናገሩት ወይዘሮ ትዕግስት፣ "በአሁኑ ወቅት ችግሩ ተቀርፎልናል፡፡ መንገዱ ተሰርቶ ባጃጆች እየገቡ ነው፡፡ በማዕከሉ የሚሸጡ አትክልት፣ ፍራፍሬ እንዲሁም ዘይትን ጨምሮ ውጭ ላይ ከሚሸጠው ቅናሽ አለው፡፡ ዘይት ባለ አምስት ሊትር በ1ሺህ 600 ብር ገዝቻለሁ፡፡ ውጭ ላይ ግን 1800 ብር እና ከዚያ በላይ ነው፡፡ ይህንን በቅናሽ የገዛሁትን ዘይትም ሆነ ሽንኩርት ይዤ በባጃጅ ተሳፍሬ ለመሄድ እየተዘጋጀሁ ነው፡፡ ይህ ለነዋሪው ማህበረሰብ ትልቅ እድል ነው፡፡ በተለይ ደግሞ እንደ እኔ አቅመ ደካማና ተሸክሞ መሄድ ለማይችል መንገዱ ተሰርቶ ትራንስፖርት መግባቱ ጠቅሞናል" ሲሉ ደስታቸውን ገልፀዋል፡፡

"የኮልፌ ሁለገብ የገበያ ማዕከል የነበረበት የመንገድ ችግር ተቀርፏል፡፡ ከዚህ በፊት የገዛነውን እቃ ወደ ቤታችን ይዘን መመለስ ስለማንችል በአካባቢያችን ከሚገኙ ሱቆች በውድ እንገዛ ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን ተሳፍረን መጥተን የምንሸምትበት እድል ተመቻችቷል" ሲሉም ያክላሉ፡፡

በማዕከሉ አትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ላይ የተሰማሩት አቶ ጤናዬ ዘርጋ በበኩላቸው፣ "የመንገድ መሰረተ ልማቱ ባልተሟላበት ወቅት ትራንስፖርት ስላልነበረ ኪሳራ ይፈጠር ነበር፡፡ ያመጣነውን ምርት በወቅቱ ለመሸጥ እንቸገር ነበር፡፡ ብዙ ጊዜም እየተበላሸ ደፍቻለሁ" ሲሉ ትውስታቸውን ነግረውናል፡፡

"በአሁኑ ወቅት ብዙ ሸማቾች ወደ ማዕከሉ ይመጣሉ፡፡ እኔም አትክልቱም ይሁን ፍራፍሬው 'ይበላሻል' የሚል ስጋት የለብኝም፡፡ የገዥዎች ቁጥር ሲጨምርም ውጤታማ እንሆናለን፡፡ ዋጋችንም ቢሆን በተቀመጠልን የዋጋ ተመን ነው የምንሸጠው፡፡ ይህም ውጭ ላይ ከሚሸጠው ከ15 እስከ 20 በመቶ ቅናሽ አለው" ሲሉም አክለዋል፡፡

> ማዕከሉ አገልግሎቱን በሚፈለገው ልክ እንዲሰጥ ባነሮችን የመስቀል፣ የማዕከሉን አቅጣጫ የሚያሳይ ታፔላ የመለጠፍ፣ ባዛሮችን የማዘጋጀት እንዲሁም በማዕከሉ የሚቀርቡ ምርቶችን የሚያሳይ ትልቅ ስክሪን ግቢ ውስጥ የማስገባት ስራ ተሰርቷል

"ከዚህ በፊት ከማዕከሉ ወደ ቤተል አስፓልት የሚያስወጣው የመንገድ መሰረተ ልማት ለትራንስፖርት ምቹ አልነበረም፡፡ በዚህም ገበያው ተቀዛቅዞ ቆይቷል፡፡ ሱቃችንንም እስከመዝጋት ደርሰን ነበር፡፡ ሸማቾች ትራንስፖርት ወዳለበት ቦታ ነበር የሚሄዱት፡፡ በዚህም ደንበኞችን አሳጥቶን ቆይቷል። በስራችንም ውጤታማ እንዳንሆን አድርጎን ነበር" የሚሉት ሌላኛው አስተያየት ሰጪ አቶ ሙሉጌታ ጨቡዴ፣ "በአሁኑ ወቅት መንገዱ ተስተካክሎ የትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጠ ነው። ሱቃችንንም ከፍተን እየሸጥን ነው። ሸማቾችም ወደ ማዕከሉ እየመጡ እየሸመቱ ይገኛሉ፡፡ ይህ መሆኑ ሸማቹም እኛም ተጠቃሚዎች ሆነናል" ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ሌላኛዋ የዘይትና አተር ክክ ምርትን ለህብረተሰቡ በማቅረብ ስራ ላይ የተሰማሩት ወይዘሮ ማህደር አስታወሰም የአቶ ሙሉጌታን ሃሳብ ያጠናክራሉ።፡ "የመንገዱ መሰራት ማህበረሰቡ ወደ ማዕከሉ በመምጣት የፈለገውን እንዲሸምት አድርጎታል፡፡ ይህ ሲሆን እኛም ተጠቃሚ እንሆናለን፡፡ ሱቅ ላይ ከሚሸጠው አንፃር ከ200 ብር ያላነሰ ቅናሽ እየሸጥኩ እገኛለሁ" ሲሉ ገልፀው፤ ይህን እድል ማህበረሰቡ ሊጠቀምበት እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

አቶ መሃመድ አሚን የኮልፌ ሁለገብ የገበያ ማዕከል ስራ አስኪያጅ ናቸው። የገበያ ማዕከሉ የኑሮ ውድነቱን ማቃለልን እና የዋጋ ንረቱን ማረጋጋትን ዓላማ አድርጎ ከፍተኛ ወጭ ወጥቶበት ማህበረሰቡን ለማገልገል የተገነባ ነው፡፡ የሰብል ምርቶችን ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች እንዲሁም አትክልትና ፍራፍሬዎች ከጋርመንት በማምጣት የግብይት እንቅስቃሴው እየተከናወነ ይገኛል፡፡

ሆኖም ከዚህ በፊት በመንገድ መሰረት ልማት መጓደል ምክንያት የገበያ መቀዛቀዝ ችግር ነበር፡፡ ሸማቾች ሸምተው ትራንስፖርት ስለማይገባ እቃቸውን ለማጓጓዝ እንቅፋት ሆኖ ቆይቷል። በአሁኑ ወቅት መንገዱ ተስተካክሎ በቅርቡ የትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ ይህ መሆኑ ማዕከሉ በሚፈለገው ልክ አገልግሎት እንዲሰጥ ያደርገዋል፡፡ ሸማቹም፣ ነጋዴውም ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

ማዕከሉ የተቋቋመበት ዋና ዓላማ፤ ውጭ ላይ ካለው ገበያ በቀነሰ ዋጋ በመሸጥ ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ማድረግና ገበያውን ማረጋጋት ነው፡፡ ቅናሹም ከ15 እስከ 20 በመቶ ነው ያሉት ስራ አስኪያጁ፤ ይህንንም ለማስቀጠል በየቀኑ የፍጆታ እቃዎቹ በተለጠፈላቸው ዋጋ መሸጣቸውን እንዲሁም ጥራታቸውን ለማረጋገጥ የክትትልና ቁጥጥር ስራዎች ይሰራሉ ብለዋል፡፡

ሸማቹ ማህበረሰብ ትኩስ ምርቶችን ውጭ ላይ ከሚሸጠው ዋጋ ቅናሽ በሆነ መንገድ እንዲሸምትና ተጠቃሚ እንዲሆን ማዕከሉ አገልግሎቱን በሚፈለገው ልክ እንዲሰጥ ባነሮችን የመስቀል፣ የማዕከሉን አቅጣጫ የሚያሳይ ታፔላ የመለጠፍ፣ ባዛሮችን የማዘጋጀት እንዲሁም በማዕከሉ የሚቀርቡ ምርቶችን የሚያሳይ ትልቅ ስክሪን ግቢ ውስጥ የማስገባት ስራ ተሰርቷል፡፡

ማህበረሰቡም ከሩቅ ቦታዎች ሳይቀር በመምጣት የፍጆታ ምርቶችን ሸምቶ በመሄዱ ረገድ ጥሩ ውጤት እየመጣ ነው፡፡ ወደፊት ደግሞ የትራንስፖርት አማራጩ እየሰፋ ሲሄድ የተሻለ ግብይት ይኖራል ተብሎ እንደሚታሰብ የሚናገሩት ስራ አስኪያጁ፤ ማህበረሰቡም በማዕከሉ መጥቶ እንዲሸምት ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# የመዲናዋ የጥበብ መሰናዶዎች

**በጊዜው አማረ**

በመዲናችን አዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል። ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል መርሃ ግብሮች መቅረባቸውን ይቀጥላሉ። ከእነዚህ መካከል የመጽሐፍ ምርቃት፣ የንባብ ውይይት፣ የሥዕል አውደ ርዕይ እና የቴአትር መርሃ ግብር ይገኙበታል። ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል የተወሰኑትን እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

## መጽሐፍት

"አንድ አካል ሁለት አምሳል" የተሰኘ መጽሐፍ ለንባብ በቃ፡፡ ደራሲው አዲስአለም አስቻለው ሲሆን፤ መጽሐፉ ልብ ወለድ ዘውግ ያለው የድርሰት ስራ መሆኑ ተሰምቷል፡፡ አዲስአለም ከዚህ በፊት "ንግስት ዘውዲቱ" የተሰኘ ታሪካዊ ተውኔት መጽሐፍ ለአንባቢያን ማድረሱ ይታወቃል፡፡

በሌላ መረጃ በዛሬው እለት በደራሲ መስፍን ወንድወሰን "ሽሙኔ" መጽሐፍ ላይ ዳሰሳና ውይይት ይደረጋል፡፡ ይህ ውይይት በRotary Ethiopia Peace Center እና በብሔራዊ ቤተ-መጻሕፍትና ቤተ መዛግብት አገልግሎት በትብብር የሚካሄደው ወርኃዊ መርሐ ግብር አካል ነው፡፡ ውይይቱ ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት እስከ 6:30 ሰዓት በብሔራዊ ቤተ-መጻሕፍትና ቤተ መዛግብት አገልግሎት (ወመዘክር) ይካሄዳል፡፡ ይህ መርሐ ግብር ሥነ-ጽሑፍ ለሰላም ግንባታ ያለውን የማይተካ ሚና የሚያሳይ ልዩ ዝግጅት መሆኑንም አዘጋጆቹ ገልጸዋል፡፡




ፎቶ- ከገፀ ድር

በከተማችን ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

በተጨማሪም "የጨረቃ ብርሃን" ግለ-ታሪክ መጽሐፍ ለንባብ በቅቷል፡፡ መጽሐፉን ያዘጋጁት አድህኖም ምትኩ እና ዮሐንስ አዝመራው ሲሆኑ፤ የወይዘሮ ብርሃኔ አስፋውን ታሪክና አበርክቶ የያዘ ነው፡፡ ባለታሪኳ ወይዘሮ ብርሃኔ አስፋው ከ80 በላይ የዓለም ሀገራት በማቅናት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲወገዱ ለ60 ዓመታት ትግል አድርገዋል፡፡ ከዚህም ባለፈ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዓለም አቀፍ የህፃናት መብት ስምምነት እንዲፀድቅ የበኩላቸውን ሚና የተጫወቱ ናቸው። በአፍሪካ ህብረት የማፑቶ ፕሮቶኮል ውስጥ ጎጂ ልማዶችን የሚከለክሉ አንቀፆች እንዲካተቱ ታላቅ ተጋድሎ እንዳደረጉ የተወዳጅ ሚዲያ ዘገባ ያሳያል፡፡

## የውይይት መርሃ ግብር

"ሰው እና ጉዞ" በሚል ርእስ ልዩ የፓናል ውይይት በዛሬው እለት ይካሄዳል፡፡ በዚህ መርሃ ግብር ውይይት ሃሳብ የሚያቀርቡት ደራሲና ተርጓሚ ዶክተር ጌታቸው ተድላ፣ ተጓዡ ጋዜጠኛና ደራሲ ሄኖክ ስዩም፣ ደራሲ ፍቃዱ አየልኝ እንዲሁም ደራሲ እና ተመራማሪ ዮርዳኖስ አልማዝ ሰይፉ ሲሆኑ ውይይቱ በደራሲ ይታገሱ ጌትነት መሪነት ይካሄዳል፡፡ መርሃግብሩ 4 ኪሎ ኢክላስ ሕንጻ፣ ከ8:00 ሰዓት ጀምሮ ይካሄዳል፡፡

## ሙዚቃ

የድምፃዊ ታሪኩ ጋንካሲ አዲስ ነጠላ ሙዚቃ ተለቀቀ፡፡ "ቦቦ" የተሰኘው ይህ ሙዚቃ በትናንትናው እለት ማታ በናሆም ሬከርድስ አማካኝነት ለአድማጭ ተመልካች ይፋ ሆኗል፡፡ ድምጻዊ ታሪኩ ከዚህ ቀደም ጦና ጋጋሶ፣ ያኔ እና ዲሽታ ጊና የተሰኙ የሙዚቃ ስራዎችን ለህዝብ አድርሷል፡፡

## የቴአትር መርሃ ግብር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ። በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ቅዳሜ ሁለት ቴአትሮች ማለትም 8፡30 ሰዓት ላይ 12ቱ እንግዶች እንዲሁም 11፡30 ሰዓት ባሎችና ሚስቶች ለእይታ ይበቃል። እሁድ በ8፡30 ሰዓት ንጉሥ አርማህ ቴአትር፣ እንዲሁም እምዬ ብረቷ የተሰኘው ቴአትር ደግሞ በ11፡30 ሰዓት ላይ ይታያሉ፡፡ በሀገር ፍቅር ደግሞ "የመጨረሻው ፍርድ" ቴአትር እሁድ 11:30 ሰዓት ይታያል፡፡

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

በስተግራ የሚገኙ ሶስት ቁጥሮች ድምርን፣ በስተቀኝ ከሚገኙ ሶስት ቁጥሮችን ድምር ላይ ሲቀነስ ውጤቱ የመሃለኛውን ቁጥር ይሆናል፡፡ ማለትም በመጀመሪያው ክብ የሚገኘው (6+15+19)-(7+11+10) = 12 ይሆናል፡፡ የሁለተኛው ደግሞ (17+19+2)-(14+16+2)=6 ነው፡፡ በዚህ ስሌት መሰረት መጨረሻ (11+7+5)-(3+8+2)=10 ነው፡፡ ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛ ቁጥር **8** ነው፡፡




## የዛሬው የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት እትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# የበዓላቱ ተጨማሪ ድምቀቶች

**“የገና በዓልን ከመዝናኛ ስፍራዎች በአንዱ የማክበር እቅድ አለኝ”**

**ወጣት ኤልያስ ተስፋ**

**በጊዜው አማረ**



ፎቶ-ከፋይል

ለመዝናኛነት ተመራጭ እየሆኑ ከመጡት መካከል ፋውንቴን ተጠቃሽ ነው

እሰይ መጣልን አውዳመት

እንደሰት

የክት ልብስሽን ልበሽ እናታለም

ዛሬኮ አውዳመት ነው ሌላ ስራ የለም... ትላለች ድምጻዊት አምሳል ምትኬ አውዳመት በተሰኘው ሙዚቃዋ፡፡

ይህ ሙዚቃ የሚያስተላልፈው አንድ መልዕክት አለ፤ ይህም የሰው ልጅ ሕይወት ከሥራ፣ ከትምህርት፣ ከቤተሰብ ኃላፊነትና ከማኅበራዊ ግዴታ ጋር የተቆራኘ መሆኑን። በዓላት ከእነዚህ የዕለት ከዕለት ኃላፊነቶች እና ስራዎች ጫና ለመላቀቅ፣ አዕምሮን ለማደስ እና አካልን ለማሳረፍ የሚያስችል ወሳኝ ዕድል ይፈጥራሉ። በተጨማሪም በዓላት ጤናማና ፍሬያማ ሕይወት ለመምራት፣ የእምነት ግዴታን ለመፈጸም የሚያስችሉ መሠረታዊ ነገሮች ናቸው።

ኃይማኖታዊና ባህላዊ በዓላት የአንድን ማህበረሰብ ማንነትና ትውስታ የሚጠብቁ፣ በየጊዜው የሚመጡ እንዲሁም የሚናፈቁ ናቸው። በአብዛኛው የዓለማችን ክፍል፣ በዓላት ከዕለት ተዕለት ኑሮ ወጣ ብሎ በጋራ የሚከበሩ ልዩ ጊዜን እና የተዝናኖት እድልን የሚጨምሩ ናቸው። እነዚህ ጊዜያት ልዩ የመዝናኛ አማራጭን በመፍጠር ረገድ ተወዳዳሪ አይገኝላቸውም።

በዓላት የሚፈጥሯቸው የመዝናኛ አማራጮች እንደየበዓሉ ዓይነት ይለያያሉ። ለምሳሌ፡- የጥምቀት በዓል በኢትዮጵያ በዝማሬ የሚከበር መንፈሳዊ በዓል ሲሆን፣ የገና በዓል ደግሞ በቤተሰብ መካከል የስጦታ ልውውጥ የሚታይበት፣ በቤት ውስጥ የሚከበር ነው። በዓሉ ሩቅና ቅርብ ያሉ ዘመድ አዝማዶችን፣ ጎረቤትና ወዳጆች የሚሰባሰቡበት ድልድይም ነው።

በዓል ሲመጣ ከሩቅ ከተሞችና ከውጭ ሀገር የሚመጡ የቤተሰብ አባላት መኖሪያ ቤቶችን በደስታ ይሞሉታል። አዛውንቶች የልጅ ልጆቻቸውን ሲያዩ፣ ትውልዶች የጋራ ትውስታን ሲፈጥሩ፣ የቤተሰብ ፍቅርና ትስስር ይጨምራል። ሳቅና ጨዋታ ይደራል፡፡ በበርካታ ሀገራትና ከተሞች ደግሞ የገና በዓልን በተለይ ከሰዓት ከቤት ወጣ ብሎ በመዝናኛ ቦታዎች ማክበር የተለመደ ነው፡፡

ለመሆኑ የአዲስ አበባ እህት ከተሞች የገና በዓልን እንዴት ያከብሩታል፡፡ በዓሉን ከቤት ወጣ በማለትና በመዝናኛ ስፍራዎች የማክበር ባህላቸው ምን ይመስላል። በአዲስ አበባ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በበዓላት ዕለት በተለይ ከሰዓት በመዝናኛ እና በመናፈሻ ቦታዎች የማክበር ልምድ ምን ይመስላል የሚለውን በዚህ ጽሑፍ ለመዳሰስ እንሞክራለን፡፡

ከኮሪደር ልማቱ በፊት በአዲስ አበባ ውስጥ ለመዝናኛነት ሲታሰብ አብዛኛው አማራጮች የተወሰነ ክፍያ የሚጠይቁ ሆቴሎች፣ ካፌዎች ወይም ጥቂት የታጠሩ ፓርኮች ነበሩ። ይህ ደግሞ ዝቅተኛ ገቢ ያለውን ማህበረሰብ ከዘመናዊ መዝናኛዎች ያገለለ ነበር።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በተለይም በአዲስ አበባ የከተማ እድገት፣ ለውጥ እና መዝናኛ አማራጮች መስፋፋት ጋር ተያይዞ በዓላትን ከሰዓት በኋላ ከቤት ወጥቶ በመዝናኛና በመናፈሻ ስፍራዎች የማሳለፍ ልምድ እየተለመደ መጥቷል። የቀድሞው በቤት ብቻ የመታጠር ባህል እየተቀየረ አዲሶቹ የመዝናኛ አማራጮች (እንደ አንድነት እና እንጦጦ ፓርኮች፣ ወዳጅነት አደባባይ፣ የዓድዋ ድል መታሰቢያ) በዓል አድማቂ መድረኮች እየሆኑ ነው። ቤተሰቦችና ወጣቶች ቀኑን ሙሉ በቤት ውስጥ ከዋሉ በኋላ ከሰዓት ገደማ በመናፈሻዎች በመገኘት አየሩን በመቀበል፣ ፎቶ በመነሳት፣ በመጫወቻ ስፍራዎች ጊዜ በማሳለፍ እና ከጓደኞቻቸው ጋር በመገናኘት በዓሉን ሲያከብሩ መመልከት እየተለመደ መጥቷል፡፡

ይህ አዝማሚያ የከተማዋን ፈጣን ለውጥ ከማሳየቱም በላይ፣ የከተሜነት (urbanization) ተጽዕኖ በበዓል አከባበር ባህል ላይ የሚያመጣውን ለውጥ ያሳያል። ወጣቱ ትውልድም ሆነ፣ እናት እና አባት ህጻናት ልጆቻቸውን በመያዝ በበዓል ቀን ከሰዓት በኋላ በመዝናኛ ስፍራዎች የመዝናናት ልምድና ፍላጎት እየጨመረ መምጣቱንም መረዳት ይቻላል።

ወይዘሮ መሰረት ተካልኝ የአዲስ አበባ ነዋሪ እና የሶስት ልጆች እናት ናቸው። ወይዘሮ መሰረት ለረጅም ዓመታት የገናን በዓል የሚያከብሩት በተለመደው የቤት ውስጥ ድባብ ነበር። ጠዋት ቤተ ክርስቲያን መሳለም፣ ቀጥሎም ቤት ገብቶ ማዕድ ማዘጋጀት፣ ከዘመድ አዝማድ ጋር መቋደስ... ይህ የማይለወጥ የሕይወታቸው አካል ነበር።

“ለእኔ በዓል ማለት ቤት ውስጥ ተሰባስቦ ሲጨዋወቱ፣ ሲበሉና ሲጠጡ መዋል ነበር” ይላሉ ወይዘሮ መሰረት ትናንትን ሲያስታውሱ። ነገር ግን ልጆቼ እያደጉ ሲመጡና ከተማዋም ስትቀየር፣ ከቤት ወጣ ብለን ማክበር ጀመርን። ለአብነትም ባለፈው ዓመት ከሰዓት የዓድዋ ድል መታሰቢያ ከልጆቼ ጋር ሄጄ ነበር፡፡ በርካታ ሰው ነበር የነበረው። በፏውንቴኑ የሚዝናና እንዲሁም ፎቶ የሚነሳ በርካታ ሰው ነበር፡፡ እኛም ደስ የሚል ጊዜ ነው ያሳለፍነው ይላሉ፡፡

ወጣት ኤልያስ ተስፋ አዲስ አበባ መኖር ከጀመረ 10 ዓመታት በላይ አስቆጥሯል፡፡ እርሱም በዓላትን ከቤት ውጭ ከሚያከብሩ ሰዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ኤልያስ፣ “ከቤተሰብ ርቄ መኖር ከጀመርኩ ብዙ ዓመታት እየሆነኝ ነው። የመጀመሪያዎቹን ዓመታት በጣም ነበር የምቸገረው፡፡ ምክንያቱም ብዙ የምሄድበት ቦታ አልነበረም፡፡ አሁን ግን በዓልን በመዝናናት ለማሳለፍ በርካታ አማራጮች አሉ፡፡ ለምሳሌ ከሁለት ዓመት በፊት ከጓደኞቼ ጋር እንጦጦ ሄደን ነበር፡፡ አምናም የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሄጄ ነበር፡፡ ይህ የመዝናኛ ስፍራ በዓልን በቤት ውስጥ ከማሳለፍ በተጨማሪ ሌላኛው አማራጭ ሆኖኛል” በማለት ልምዱን ያጋራል፡፡

በእርግጥ በአብዛኛው የአደጉ ሀገራትም በዓልን ከቤት ወጣ ብሎ በፓርኮችና በሚገኙ ቦታዎች በመዝናናት ማክበር የተለመደ ነው፡፡ በአብዛኛዎቹ የአውሮፓና አሜሪካ ከተሞች (ለምሳሌ የአዲስ አበባ እህት ከተማ በሆነችው ዋሽንግተን ዲ.ሲ.) የገና በዓልን ከቤተሰብ ጋር፣ ስጦታ መለዋወጥ፣ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት አምልኮ ይከበራል፡፡ በተጨማሪም በዓሉን ምክንያት በማድረግ ትልልቅ የመብራት ጌጦች፣ የገና ገበያዎች እና የልዩ ዝግጅቶች የሚካሄዱ ሲሆን፣ ሰዎች በዓሉን ለማድመቅ ወደ ውጪ ወጥተው እነዚህን ዝግጅቶች የመጎብኘት እና በፓርኮች የመዝናናት ጠንካራ ባህል አላቸው።

ሌላኛዋ የአዲስ አበባ እህት ከተማ በሆነችው የሩዋንዳዋ ኪጋሊም የገና በዓልን በእርድ፣ ቤተሰብ በመጠየቅ ይከበራል፡፡ ከሰዓት ደግሞ ቤተሰቦች፣ ጓደኞችም ሆነ በግል በውብ የመዝናኛ ስፍራዎች እና ፓርኮች የገና በዓልን ማክበር የተለመደ ነው፡፡

በሀገራችን የገና በዓል ሲመጣ ቀድሞ ወደ አዕምሯችን የሚመጣው የቄጤማው መዓዛ፣ የዶሮ ወጥ ሽታ እና የቤተሰብ ጨዋታ እና ጥየቃ ነው። አዲስ አበባ ያለው ገጽታም በሀገር ደረጃ ካለው የተለየ አይደለም፡፡ ነገር ግን በጊዜ ሂደት የአዲስ አበባ ገጽታ ሲቀየር፣ የበዓል አከባበር ልምድም አብሮ እየተቀየረ ይገኛል። ከእነዚህ ለውጦች መሃል የከተማዋን አዳዲስ የመዝናኛ ስፍራዎች ከቤተሰብ ጋር መጎብኘት አንዱና ዋነኛው እየሆነ መጥቷል፡፡

አዲስ አበባ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ውብ እና ማራኪ ገጽታ እየተላበሰች ትገኛለች። የዚህ ለውጥ ዋነኛ ሞተር ደግሞ የኮሪደር ልማት ፕሮጀክት ነው። ይህ ፕሮጀክት የመሠረተ ልማት ግንባታ ብቻ ሳይሆን የከተማዋን ነዋሪዎች የአኗኗር ዘይቤ፣ የማህበራዊ ግንኙነት ባህል እና የመዝናኛ ምርጫዎችን የቀየረ ትልቅ እድል ሆኗል። በተለይም እንደ ገና፣ ኢሬቻ፣ ጥምቀት እና ፋሲካ ባሉ ታላላቅ በዓላት ወቅት፣ እነዚህ የኮሪደር መንገዶችና የመዝናኛ ቦታዎች ነዋሪዎች ከቤታቸው ወጣ ብለው በነጻነት የሚዝናኑባቸው፣ ፎቶ የሚነሱባቸው እና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ የሚያደርጉባቸው ቀዳሚ ስፍራዎች ሆነዋል።

በአጠቃላይ የገና እና ጥምቀት በዓላትን ጨምሮ ሌሎች በዓላትን ከቤት እና ከቤተ-እምነት ባለፈም በአዲስ አበባ የመዝናኛ ስፍራዎች በመዝናናት ማክበር እየተለመደ መጥቷል፡፡ የአዲስ አበባ የኮሪደር ልማት ፕሮጀክት ከተማዋን ለነዋሪዎቿ ምቹ እና ማራኪ አድርጓታል። እነዚህ ስፍራዎች በተለይም በበዓላት ወቅት የደስታ እና የመዝናኛ ምንጭ በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ። ነዋሪዎች ከቤት ወጣ ብለው ንጹህ አየር እየተነፈሱ፣ ፎቶ እየተነሱና በእግር እየተጓዙ የሚያሳልፉት ጊዜ የአዕምሮ እረፍት ከመስጠቱም በላይ ለከተማዋ አዲስ ህይወት ዘርቷል። ለበዓላት ደግሞ ተጨማሪ ድምቀትን አጎናጽፏል፡፡ ወጣት ኤልያስ ተስፋ፣ “ዘንድሮውም ከሰዓት በኋላ አዲስ ከተሰሩ የመዝናኛ ስፍራዎች በአንዱ እየተዝናናሁ የገና በዓልን የማክበር እቅድ አለኝ” ሲል ሃሳቡን አጋርቷል፡፡

ኢኮኖሚ

# በራስ አቅም የሚተገበር የሥራ ላይ ልምምድ

- በዓለም ባንክ ትብብር ጭምር ሲከናወን የቆየውን የሥራ ላይ ልምምድ በራስ እቅም ለማስቀጠል ከተማ አስተዳደሩ ከ145 ሚሊዮን ብር በላይ በጀት መድቧል
- በመርሃ ግብሩ 3 ሺህ ወጣቶች ቋሚ የሥራ ዕድል ተጠቃሚ ይሆናሉ
- በተመረጡ 20 ወረዳዎች ላይ ከሕዳር 1 ቀን 2018 ዓ.ም ጀምሮ በመተግበር ላይ ነው

**በደረጀ ታደሰ**

"ሥራ ለሠሪው፤ እሾህ ላጣሪው" ይባላል፡፡ ሥራ፤ የሰው ልጅ በሕይወት ዘመኑ ኑሮን መቋቋሚያ ምርኩዝ ነው። ሥራ ያስከብራል፡፡ ሥራ ያኖራል፡፡ ሥራ ያጠነክራል፡፡ ሥራ ከጥገኝነት ነፃ ያወጣል። ብዙ ጥቅምን የሚያስገኘው ሥራ፣ የሚጠበቀውን ውጤት እንዲያመጣ ሠራተኛን ይፈልጋል። የሥራ ብዛትን በዓይነትም በስፋትም መፍጠር የሚችሉ ፀጋዎች የቱንም ያክል ቢትረፈረፉ፤ ሥራና ሠራተኛን ማገናኘት ካልተቻለ ውጤቱ "ላም አለኝ በሰማይ ወተቷን የማላይ" መሆኑ አይቀርም፡፡

ኢትዮጵያ ወጣቶቿ ሙሉ ጊዜያቸውን፣ ዕውቀታቸውን፣ ክህሎታቸውንና ያላቸውን ጥሪት በሥራ ላይ እንዲያውሉላት ትፈልጋለች፡፡ ፍላጎቱ የሀገር ብቻ ሳይሆን የወጣቱ፤ በተለይም ሥራ አጥ የሆነው የህብረተሰብ ክፍል ጭምር ነው፡፡ የሥራ ፍላጎቱ ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ "ለዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር" በሀገራዊ ቁልፍ አጀንዳነት ተይዞ ለተፈፃሚነቱ በርካታ ጥረቶች መደረግ ከጀመሩ ዓመታት ተቆጥረዋል። እንደ ሀገር ለሥራ ዕድል መፍጠሪያነት የሚያግዙ ፀጋዎችን በጥናት በመለየት ዜጎች እንዲሰማሩባቸው ተደርጓል፤ ተግባሩም ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ እየተተገበሩ ካሉ በርካታ የሥራ ዕድል መፍጠሪያ አማራጮች መካከል፡- ብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር ይጠቀሳል፡፡

ብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር ትኩረቱን በወጣቶች ላይ በማድረግ፣ ሥራ ለሌላቸው ወጣቶች የሥራ ላይ ስልጠና በመስጠት ቋሚ የሥራ ዕድል የሚያገኙበትን ሁኔታ የሚያመቻች ነው፡፡ ይህ መርሃ ግብር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደረጃ ከ2014 በጀት ዓመት ጀምሮ ሲተገበር መቆየቱ ይታወሳል፡፡ ስለ መርሃ ግብሩ አጀማመር እና ስላስገኘው ውጤት ማብራሪያ የሰጡን በአዲስ አበባ ሥራና ክህሎት ቢሮ የሥራ ስምሪት አገልግሎት ዳይሬክተር አቶ ሰብሀዲን ሱልጣን እንዳብራሩት፤ በ2014 በጀት ዓመት የጀመረው መርሃ ግብሩ በኢትዮጵያ መንግስት እና በዓለም ባንክ ትብብር 49 ሺህ ወጣቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ ሲሠራ ቆይቷል፡፡ የመርሃ ግብሩ የመጨረሻው ምዕራፍ የሆነው ብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ ጥቅምት 30 ቀን 2018 ዓ.ም. በይፋ ተጠናቅቋል። በመጨረሻው ምዕራፍ ላይ 15 ሺህ ወጣቶች ተሳትፈዋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥም



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

በመንግስት በጀት እየተተገበረ ባለው ብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ ተሳታፊ ወጣቶች

9 ሺህ 615ቱ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ወጣቶች ሲሆኑ፣ ቀሪዎቹ ተጠቃሚዎች የውጭ ሀገር ዜጎች ሆነው በስደት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡

የመርሃ ግብሩ መጨረሻ በሆነው የሦስተኛ ዙር የብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር ከተሳተፉ እና የስድስት ወራት ቆይታቸውን በአግባቡ ያጠናቀቁ ከስምንት ሺህ በላይ ወጣት የመዲናዋ ነዋሪዎች፤ በአሁኑ ወቅት በተለያዩ ተቋማት እና ድርጅቶች ቋሚ የሥራ ዕድል እንደተፈጠረላቸው እንዲሁም በግላቸው ወይም በመደራጀት የራሳቸውን ሥራ ፈጥረው እየተንቀሳቀሱ ያሉ ብዙዎች ስለመሆናቸው አቶ ሰብሀዲን አስረድተዋል፡፡

የዳይሬክተሩን ሃሳብ በመርሃ ግብሩ ተጠቃሚ የሆኑ ወጣቶችም ያረጋግጣሉ፡፡ ወጣት አየናቸው ሽብሩ እና ወይዘሮ ብርቱካን ተቻለ በሮሰን ጨርቃ ጨርቅ አምራች እና የህትመት ስራ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት ተቀጥረው በመሥራት ላይ ይገኛሉ። እነዚህ ሁለት ሥራ አጥ የነበሩ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በድርጅቱ ቋሚ የሥራ ዕድል እንዲያገኙ ድልድይ የሆናቸው ብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር ስለመሆኑ አልሸሸጉም። በመርሃ ግብሩ ከመታቀፋቸው አስቀድሞ የነበራቸው ሕይወት በውጣ ውረድ የተሞላ፣ ያቋረጡትን ትምህርት ለመቀጠል እንዲሁም ሠርተው ለመለወጥ የሚችሉበት መንገድ ጠፍቷቸው በቤተሰብ ጥገኝነት እንዲቆዩ የተገደዱበት፣ ለጭንቀት እና ለመብሰልሰል የተዳረጉበት እንደነበር ሩቅ ካልሆነው የትዝታ ማህደራቸው አስቃኝተውናል፡፡

ወጣት አየናቸው እና ወይዘሮ ብርቱካን በአሁኑ ወቅት በሮሰን ጨርቃ ጨርቅ አምራች እና የህትመት ስራ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት ብቁ ሙያተኛ ሆነው፣ በቋሚ ሠራተኛነት ተቀጥረው ገቢ ማግኘት ከጀመሩ ወራትን አስቆጥረዋል። በአራዳ ክፍለ ከተማ ውስጥ በሚገኝና 354 ካሬ ላይ ባረፈ የማምረቻ ሼድ ውስጥ ነው ሥራውን እያከናወነ የሚገኘው የስፖርት ትጥቅ አምራች ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ፍቅሬ ታፈሰ፤ በድርጅታቸው ከሚሠሩ 56 ባለሙያዎች መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት፤ በብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር አማካኝነት ለስድስት ወር የሥራ ላይ ልምምድ ሲያደርጉ የቆዩ መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡

በተመሳሳይ፤ በግርማ፣ ሕይወትና ጓደኞቻቸው የእንጨት እና ብረታ ብረት ሥራ ድርጅት ውስጥ ለስድስት ወራት የቆየውን የብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ በማጠናቀቅ በቋሚነት የሥራ ዕድልን ማግኘት የቻሉት ወጣቶችም የመርሃ ግብሩን ውጤታማነት በተጨባጭ የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡ ወጣት አብርሃም ተስፋዬ እና ወጣት ዮሀንስ ጌትነት በዚህ ድርጅት ውስጥ፤ በዓለም ባንክ እና በኢትዮጵያ መንግስት የጋራ ትብብር ሲተገበር በቆየው የመጨረሻው ምዕራፍ የብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ ተሳታፊዎች መካከል የመሆን ዕድልን አግኝተው ተጠቅመዋል፡፡ በቆይታቸውም ጥሩ ሙያዊ ብቃትን፣ የሥራ ስነ ምግባርን፣ ከቤት ውጪ ያለውን የሕይወት ልምድ በማግኘት የተሟላ የሥራ ሰው ስብዕናን የሚገነባ እርሾ መያዛቸውን መስክረዋል። በቋሚነት ከሚያገኙት ደምወዝ ባሻገር በትርፍ ሰዓታቸው በሚሠሩት ሥራ ተጨማሪ ገቢ የሚያገኙበት ሁኔታ መፈጠሩንም አንስተዋል፡፡

ከስምንት ሺህ በላይ የሚሆኑ ወጣቶችን ከጠባቂነት በማላቀቅ ሠራተኛ እና አምራች በማድረግ የማይተካ ሚናን የተጫወተው፣ በዓለም ባንክ እና በኢትዮጵያ መንግስት ትብብር ሲተገበር የቆየው የብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር ጥቅምት 30 ቀን 2018 ዓ.ም. በይፋ ተጠናቅቋል፡፡ የመርሃ ግብሩ መጠናቀቅ ተስፋ ሰጪ ጅምሩን እንዳያቀጭጨው የከተማ አስተዳደሩ ቁርጠኛ አቋምን በመያዝ በራስ አቅም የሚቀጥልበትን አሠራር ዘርግቶ ወደ ተግባር ገብቷል፡፡ ከአምስት ዓመቱ አፈጻጸም ልምድና ተሞክሮ በመቅሰም፣ የመዲናዋን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የሥራ ላይ ልምምድ እያከናወነ ይገኛል፡፡ በራስ አቅም ስለሚተገበረው የሥራ ዕድል መፍጠሪያ መርሃ ግብር አስመልክቶ አቶ ሰብሀዲን ሱልጣን ለአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል አብራርተዋል፡፡

እንደ አቶ ሰብሀዲን ገለፃ፤ በመንግሥት የሚተገበረው ብቃት የሥራ ላይ ልምምድ እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተመረጡ 20 ወረዳዎች ላይ ከሕዳር 2018 ዓ.ም. ጀምሮ በመተግበር ላይ ነው፡፡ በራስ አቅም የሚከናወነውን ብቃት የሥራ ላይ ልምምድ ለማስፈፀም በከተማ አስተዳደር ደረጃ ከ145 ሚሊዮን ብር በላይ በጀት ተመድቦለት ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡ በዚህ መርሃ ግብር 3 ሺህ ወጣቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ ከሕዳር 1 ቀን 2018 ዓ.ም. ጀምሮ እየተሠራ ይገኛል፡፡ እነዚህ ወጣቶች ዕድሜያቸው ከ18 እስከ 34 የሚገኝ፣ የትምህርት ዝግጅታቸው ከ12ኛ ክፍል በታች የሆነ፣ ሥራ የሌላቸው ወይም የሚሠሩትን ሥራ በተለያየ ምክንያት አቋርጠው ቤታቸው የተቀመጡ ሲሆኑ፤ ከመርሃ ግብሩ ተጠቃሚዎች መካከል የሴቶች ድርሻ 60 ከመቶ የሚይዝ ይሆናል፡፡

"በብቃት የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር የሚሳተፉ ወጣቶች በዋናነት ሙያዊ ክህሎትና ዕውቀት ሊያገኙባቸው ወደሚችሉ ተቋማት ወይም ድርጅቶች ልምምድ ያደርጋሉ፡፡ እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶቹን ተቀብለው የሥራ ላይ ልምምድ እንዲያደርጉ ዕድል የሚሰጡ 1 ሺህ የሚሆኑ ተቋማት ወይም ድርጅቶች ተለይተዋል፡፡ እነዚህ ድርጅቶች ብቃት የሥራ ላይ ልምምድን ተግባራዊ ማድረግ የሚችሉ መሆናቸው ተቋማዊ በሆነ አሠራር ልየታ እና ማረጋገጫ የተሰጣቸው ናቸው" ያሉት የሥራ ስምሪት አገልግሎት ዳይሬክተሩ፤ ወጣቶቹም ወደ ድርጅቶቹ የሚሄዱት በፍላጎታቸው መሰረት መሆኑን በመጥቀስ ድርጅቶቹን ከመቀላቀላቸው በፊት ለ12 ቀናት የሚቆይ የሕይወት ክህሎት እና የሥራ ማፈላለግ ስልጠና እንደሚሰጣቸው አስረድተዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም፤ ለሥራ ላይ ልምምድ በሚሄዱባቸው ድርጅቶች ላይ ማሳየት ስለሚገባቸው የሥራ ላይ የስነ ምግባር ስልጠና ተሰጥቷቸው፣ ወደ ድርጅቶቹ ለመግባት የሚያስችላቸውን ቅድመ ሁኔታ ሲያሟሉ ከድርጅቶቹ ጋር ውል ፈፅመው የሥራ ላይ ልምምዳቸውን እንደሚጀምሩ ጠቁመው፤ "በድርጅቶቹ እና የሥራ ላይ ልምምድ በሚያደርጉ ወጣቶች መካከል የሚፈጸመው ውል ለስድስት ወራት ይቆያል፡፡ ወጣቶቹ የድርጅቱን የሥራ ባህል በማክበር፣ የሠራተኛ ስነ ምግባርን ተፈፃሚ በማድረግ የሥራ ላይ ልምምዱን ባልተቆራረጠ ሁኔታ መፈጸም ይጠበቅባቸዋል፡፡

ወደ ገጽ 22 ዞሯል

# ልጆች፤ ስለ ገና ጨዋታ ምን ያህል ታውቃላችሁ?

**በፋንታነሽ ተፈራ**



ግራፊክስ ከፋይል
የገና ጨዋታ ከፊል ገፅታ

ልጆች "አሲና በል አሲና ገናዬ...! እየተባለ የሚገጠመው መቼ እንደሆነ ታውቃላችሁ? ለገና በዓል እንደምትሉ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ እንኳን ለበዓሉ በሰላም አደረሳችሁ! እያልኩ ስለገና ጨዋታ ምንነት፣ ጨዋታውን ስንጫወት ስለምንጠቀማቸው ቁሳቁሶች እንዲሁም በጨዋታው ላይ ስለሚገጠሙ ግጥሞች ለእናንተ ለልጆች ማብራሪያ እንዲሰጡልን አንድ እንግዳ ጋብዘናል፡፡

መስፍን ከበደ እባላለሁ፡፡ በአዲስ አበባ የባህል ስፖርት ፌዴሬሽን ስራ አስፈፃሚ እና የቴክኒክ ኮሚቴ ሰብሳቢ ነኝ፡፡ የገና በዓል እረኞች የኢየሱስ ክርስቶስ ልደትን ምክንያት በማድረግ የገና ጨዋታን ከታህሳስ ጀምሮ እስከ ጥር ከዚያም እስከ ክረምቱ መግቢያ ይጫወቱት እንደነበር የቀድሞ አባቶች ይናገራሉ። ጨዋታው የሚካሄደውም አርሶ አደሮች ሰብላቸውን ከሰበሰቡ በኋላ ለጥ ባለ ሜዳ ላይ ነው፡፡

ልጆች የገና ባህላዊ ጨዋታ የሚካሄደው በሁለት ቡድኖች መካከል ነው፡፡ ተጫዋቾች ወደ ሜዳ የሚገቡት "አሲና በል አሲና ገናዬ..." በማለት በአንዱ ቡድን 10፣ በሌላው ቡድን 10 በመሆን ነው፡፡ ቡድኖቹ የየራሳቸው በረኛ ወይም ጠባቂ አላቸው፡፡ ጨዋታው አንድ ዋና፣ ሁለት የመስመር እና አንድ የነጥብ መዝጋቢ ዳኞች አሉት፡፡ በጨዋታው ወቅት ልክ እንደ እግር ኳስ የራሱ የማዕዘን ምት እንዲሁም የቅጣት ምት የሚሉ የጨዋታ ህጎች አሉት፡፡

ልጆች የገናን ጨዋታ ስንጫወት ከምንገለገልባቸው ቁሶች ሩር ወይም ጥንግ አንዱ ነው፡፡ ይህ ቁስ በገጠሩ የማህበረሰብ ክፍል ከጠፍር ወይም ከጉቶ ተጠርቦ የሚሰራ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት ደግሞ ከፕላስቲክ እንደ ኳስ መስራትም ይቻላል፡፡ ሌላኛው ደግሞ ሩሯን የምንመታበት ዱላ ነው፡፡ ዱላው ጫፉ ላይ ጠመም ያለ ቅርፅ ያለው ሲሆን፤ ይህም ሩሯን እንዳስፈለገ ለመምታትና ወደ ሌላ ቦታ እንዳትሄድ ለመመለስ የሚረዳ መሳሪያ ነው፡፡

ልጆች ኳስ ስትጫወቱ ጎል እንዳለ ሁሉ የገና ጨዋታም ሩሯ እንዳትሾልክ የሚያደርግ ከሸራ ወይም ከማዳበሪያ እንደመረብ የተሰራ ጎል አለው፡፡ 60 ደቂቃ የጨዋታ ጊዜ ያለው ሲሆን፤ አቻ ስትሆኑ አንድ፣ አሸናፊ ከሆነ ደግሞ ሶስት ነጥብ ያገኛል፡፡ ይህም ማለት አሸናፊና ተሸናፊም አለው ማለት ነው፡፡

ልጆች የገና ጨዋታ ባህላችንን ለማስተዋወቅና ኢትዮጵያን ለመግለፅ ተጫዋቾች እግረ ጠባብ እና ራሳቸው ላይ ሻሽ አስረው ነው የሚጫወቱት፡፡ የዱሮ አባቶች ሲጫወቱ ለመጫወት ፍላጎት ያለው ትልቅ ትንሽ፣ አሰሪም ሰራተኛ ሳይል ሁሉም እኩል ይጫወት ነበር፡፡ ይህንን ምሳሌ በማድረግም "በገና ጨዋታ የለም ሎሌ ጌታ፣ በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ" እየተባለ ግጥሞች ይገጠማሉ፡፡ ይህ ማለት በዚህ ጨዋታ ትልቅ ትንሽ ሳይባል አንዱ በአንዱ ላይ ጉዳት እንኳን ቢያደርስ ቅጣትም ሆነ ቂም አይያዝም ማለት ነው፡፡

እናንተም ልጆች ከገና ጨዋታም ውጭ ቢሆን ከጓደኞቻችሁ ጋር ስትጫወቱ አንዱ አንዱን ቢጎዳው ወይም በኳስ ቢመታው ሳትኮራረፉ፣ ቂም ሳትይዙ ተግባብታችሁ በፍቅር መጫወት አለባችሁ፡፡

ልጆች የገና ጨዋታ ለመጫወት ወደ ሜዳ ሲገባ ተቃራኒ ቡድኖች ዱላቸውን አጣምረው ወይም የኤክስ ምልክት ሰርተው ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሚያሳየው አንድነትን፣ ሰላምን፣ ፍቅር፣ እንዲሁም ስፖርት የሰላም መድረክ መሆኑን ለመግለፅ ነው፡፡

የገና ጨዋታን አያቶቻችን እና አባቶቻችን ሲጫወቱት የነበረ አሁንም ያለ በመሆኑ እናንተም የሀገራችሁን ባህልና ወግ ለማወቅ መጫወት አለባችሁ፡፡ እናንተ የፈረንጆቹን ጨዋታ አስበልጣችሁ እንድታዩና እንድትወዱት ያደረጋችሁ እነሱ የራሳቸውን ወግና ባህል ስለሚያስጠብቁ ነው፡፡ ስለዚህ የራሳችሁን ወግና ባህል በማወቅ መኩራት እና በተግባርም ማሳየት አለባችሁ፡፡

ልጆች በገና ጨዋታ፣ በትግል፣ በገበጣ፣ በፈረስ ጉግስ እንዲሁም ቀስትና በመሳሰሉት ባህላዊ ጨዋታዎች በመወዳደር ስፖርቶቹን ወደ ኦሎምፒክ ማስገባትና ኢትዮጵያን ማስጠራት ትችላላችሁ፡፡ ባህልና ወጋችሁን የምትወዱ መሆን አለባችሁ፡፡ መልካም የገና በዓል ይሁንላችሁ፡፡ ሰላም ሁኑ ልጆች፡፡

## 10 ልዩነቶችን ፈልጉ





## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ላይጠቅማት ሸክሙ ባሳት**

**መልስ፡- ሐ. የፍየል ጅራት**

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ሲቀመጥ ረጅም ፤ ሲቆም አጭር**

**ሀ. ውሻ**
**ለ. ሰው**
**ሐ. ግመል**

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ።**

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ

# “በአጥር የተዘጉ መንገዶችን የማስከፈት ስራው ተጠናክሮ ይቀጥላል”

## የመንገድ ሀብት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ኢንጂኒዬር መሀመድአወል ሰይድ

በሳምሶን ዮሐንስ (ከመንገዶች ባለሥልጣን)

የከተማዋን የመንገድ ሽፋንና ተደራሽነት ለማሳደግ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን የሚያከናውነው የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን፤ በመሠረተ ልማቶቹ ላይ የሚፈፀሙ ህገ ወጥ ድርጊቶችን ለመከላከል የተለያዩ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡ በቅርቡም በአጥር የታጠሩ የውስጥ ለውስጥ መንገዶችን የማስከፈትና ለታለመላቸው ዓላማ እንዲውሉ የማድረግ ስራ በማከናወን ላይ ነው፡፡ በዚህ ዙሪያ በባለስልጣኑ የመንገድ ሀብት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ኢንጂኒዬር መሀመድአወል ሰይድ አነጋግረናል፡፡

ያቀረብንላቸው ጥያቄ እና የሰጡት ምላሽ



ፎቶ- ከፋል

የመንገድ ሀብት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ኢንጅነር መሀመድአወል ሰይድ

ፎቶ ከፋይል

በህገወጥ መንገድ ከፈረሱ መንገደች በጥቂቱ

**ባለስልጣኑ የታጠሩ የውስጥ ለውስጥ መንገዶችን የማስከፈት እንቅስቃሴ አሁን ላይ ማካሄድ የፈለገበትን ምክንያት ቢጠቅሱልን?**

**ኢንጂኒዬነር መሀመድአወል፡-** በከተማዋ መዋቅራዊ ፕላን መሠረት፤ በተለያየ ደረጃ የተከፈቱ መንገዶች ዋነኛ ዓላማ የትራፊክ እንቅስቃሴውን በማስተናገድ ደህንነቱ የተጠበቀ የመንገድ አገልግሎት እንዲኖር ማስቻል መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከዚህ አንፃር በየአካባቢው የሚገኙ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ከፍተኛ ድርሻ አላቸው፡፡ ይሁን እንጂ በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች፤ ከተከፈቱበት አገልግሎት በተቃራኒ በግለሰቦች ታጥረው መዘጋታቸው በየአካባቢው የትራፊክ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ አሳድሯል፡፡ በመሆኑም ባለስልጣን መስሪያቤታችን በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በመንገድ ሀብታችን ላይ የሚፈጸሙ ህገ ወጥ ድርጊቶችን ለማስቆም እርምጃ መውሰድ ጀምሯል፡፡ የተዘጉ መንገዶችን የማስከፈት እንቅስቃሴ አቅደንና ተዘጋጅተን በተያዘው በጀት ዓመት ዋና ዋና መንገዶችን ከጠገንን በኋላ የውስጥ ለውስጥ መንገዶችን እንጠግናለን የሚል ዕቅድ ይዘን ቆይተናል፡፡ የምንጠግናቸው መንገዶች ደግሞ ተጠግነው የግለሰቦች መጠቀሚያ መሆን የለባቸውም፤ መንገዶቹ ከግለሰቦች መጠቀሚያነት ወደ ህዝብ መጠቀሚያነት መሸጋገር አለባቸው የሚል ዕምነት ስላለንና መንገዶቹ ከመጠገናቸው በፊት የታጠሩ አጥሮች መፍረስ ስላለባቸው ነው ወደ ማፍረስ የገባነው፡፡

**የመንገዶቹ መዘጋት የሚያስከትሉት ጉዳት እስከምን ድረስ ነበር?**

> “በአጥር የተዘጉ የውስጥ ለውስጥ መንገዶችን ለትራፊክ ክፍት ለማድረግ በሚወሰደው እርምጃ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በንቃት ሊሳተፍ ይገባል”

**ኢንጂኒዬር መሀመድአወል፡-** የውስጥ ለውስጥ መንገዶቹ መዘጋት በዋና ዋና መንገዶች ላይ የትራፊክ ጫና ከመፍጠሩ ባሻገር መሰረተ ልማቱ ለጉዳት እንዲዳረግ የሚያደርግ ነው፡፡ በሌላ በኩል እነዚህ መንገዶች ለትራፊክ ክፍት ባለመሆናቸው እሳት እና ሌሎች ድንገተኛ አደጋዎች በሚፈጠሩ ጊዜ አስፈላጊውን ዕርዳታ ለማድረግ አዳጋች የሚሆንበት ሁኔታ ይፈጥራሉ፡፡ ሰዎች በሚታመሙ ጊዜ በወቅቱ ወደ ህክምና ለማድረስ የማይቻልበት ሁኔታ የሚፈጠርበትም ጊዜ አለ፡፡

**ወደ ማፍረስ እርምጃ ከመገባቱ በፊት የተደረጉ ቅድመ ዝግጅቶች ምን ይመስላሉ?**

**ኢንጂኒዬር መሀመድአወል፡-** ወደ እርምጃ ከመገባቱ በፊት የውስጥ ለውስጥ መንገዶችን ያጠሩ አካላት አጥሮቹን እንዲያፈርሱ ቀነ ገደብ አስቀምጠናል፡፡ መድረኮችን በማዘጋጀት ጭምር ውይይት አካሂደናል፡፡ የተቀመጠው ቀነ ገደብ ሲያልቅ ነው ወደ ማፍረስ የገባነው፡፡ በዚህም በመዲናዋ አራቱም አቅጣጫዎች በህገ ወጥ መንገድ የታጠሩ አጥሮችን የማፍረስ መንገዶች ለታለመላቸው ዓላማ እንዲውሉ የማድረግ ሥራ እየሰራን ነው፡፡

**በተወሰደው እርምጃ የተገኘው ውጤት ምን ይመስላል?**

**ኢንጂኒዬነር መሀመድአወል፡-** የተዘጉ መንገዶችን የማፍረስ እንቅስቃሴ በሁሉም ክፍለ ከተሞች በስፋት ቀጥሏል። በዚህም በግለሰቦችና በተለያዩ አካላት ታጥረው የነበሩ በርካታ የውስጥ ለውስጥ መንገዶችን በማስከፈት ለአገልግሎት ክፍት ማድረግ ችለናል፡፡ መንገድ የሚገነባው በአካባቢው ለሚኖር ህብረተሰብ ብቻ አይደለም፡፡ መንገድ የሁሉም ነው፡፡ መንገድ የምንገነባው ህዝብ እንዲጠቀምበት ነው፡፡ ከህዝቡ እየመጣ ያለው ግብረ መልስም የህዝቡን ፍትሀዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተወሰደው እርምጃ ትክክለኛ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

**መንገዶቹን በማስከፈት ሂደት የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ምን ይመስላል ?**

**ኢንጂኒዬር መሀመድአወል፡-** ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ በየዓመቱ በከፍተኛ በጀት የመንገድ ግንባታና ጥገና ስራዎችን እያከናወነ ቢሆንም በሀብቱ ላይ የሚፈፀመው ህገ-ወጥ ድርጊት ግን አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል፡፡ በተጨማሪም በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች የተገነቡ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች በአጥር ተዘግተው ለህብረተሰቡ አገልግሎት እንዳይሰጡ ተደርጓል፡፡ ድርጊቱ የህብረተሰቡን በመንገድ መሰረተ ልማት የመጠቀም መብትን የሚጋፋና ለትራፊክ ፍሰት መስተጓጎል መንስኤ እየሆነ እንደሚገኝ ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር መግባባት ላይ ከተደረሰ በኋላ ነው ወደ እርምጃ የገባነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት፤ ከፖሊስ፣ ከሰላምና ጸጥታ፣ ከደንብ ማስከበርና ከሁሉም ክፍለ ከተሞች ጋር ተናብበን እየሰራን ነው፡፡ በአጥር የተዘጉ የውስጥ ለውስጥ መንገዶችን ለትራፊክ ክፍት ለማድረግ በሚወሰደው እርምጃ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በንቃት ሊሳተፍ ይገባል የሚል ዕምነት አለን፡፡

**የህብረተሰቡ ምላሽ ምን ይመስላል?**

**ኢንጂኒዬር መሀመድአወል፡-** ከህብረተሰቡ እያገኘን ያለው ምላሽ ጥሩ ነው፡፡ ዘግይታችኋል የሚል ምላሽ እየሰጠን ነው፡፡ እንዲያውም እኛ በራስ ሀይል የታጠሩ መንገዶችን ማፍረስ ስንጀምር የእኛን እንቅስቃሴ ተከትሎ በአንዳንድ አካባቢዎች ማህበረሰቡ በራሱ የታጠሩ መንገዶችን ማፍረስ የጀመረበት ሁኔታ ነው ያለው ፡፡

**የመንገዶቹ መከፈት በከተማዋ የትራፊክ እንቅስቃሴ ላይ የሚያመጣው ለውጥ እንዴት ይታያል?**

**ኢንጂኒዬር መሀመድአወል፡-** የውስጥ ለውስጥ መንገዶች በመዘጋታቸው ተሽከርካሪዎች ወደ ዋና ዋና መንገዶች የሚመጡበት ሁኔታ ነበር፡፡ አቋራጭ መንገዶችን በመጠቀም በፍጥነት ወደ አሰበበት ቦታ ለመድረስ ያስችላል፡፡ በዋና ዋና መንገዶች ላይ የሚከማቸው ተሽከርካሪም ወደ ውስጥ ለውስጥ መንገዶች የሚበተንበት ሁኔታ የሚፈጠር በመሆኑ በተለያዩ አካባቢዎች የሚፈጠር የትራፊክ መጨናነቅን ያስቀራል የሚል እምነት አለን፡፡

**መንገዶቹን የማስከፈት እንቅስቃሴ ቀጣይነቱን በተመለከተ ምን አስተያየት አለዎት?**

**ኢንጂኒዬር መሀመድአወል፡-** እነዚህ የታጠሩ መንገዶች መፍረስ አለባቸው የሚል ግልጽ አቅጣጫ አስቀምጠን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መግባባት ላይ ከደረስን በኋላ ነው ወደ ተግባር የገባነው፡፡ ስለዚህ የታጠሩ መንገዶችን የማስከፈት እርምጃው ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ ስለ እርምጃው ቀጣይነት አንዳንዶች ጥርጣሬ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ምክንያቱም በጠራራ ፀሀይ ነው መንገዶቹ በግለሰቦች ሲታጠሩ የነበሩት። ስለዚህ ስጋታቸውን መግለፃቸው ተገቢ ነው፡፡ አሁን ግን እርምጃ መውሰድ ጀምረናል፤ እኛ እያፈረስን በጎን መንገድ እናጥራለን የሚባል ነገር ከዚህ በኋላ አይሰራም ደንብ አስከባሪ አከላትም ይሄን የመከታተልና መቆጣጠር ኃላፊነት አለባቸው፡፡ በእኛ በኩል በየትኛውም ወረዳና ክፍለ ከተማ የታጠረ የውስጥ ለውስጥ መንገድ አለመኖሩ እስከሚረጋገጥ ድረስ የጀመርነውን ሥራ አጠናክረን እንቀጥላለን ፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የከተማ ግብርና ትሩፋት

- የከተማ ግብርና በአዲስ አበባ በበዓላት ሰሞን የሚያጋጥም የምርት አቅርቦት እጥረት ችግር እንዲቀንስ ማስቻሉ ተመላክቷል

**በይግለጡ ጓዴ**

አቶ በግዱ አልታዬ በየካ ክፍለ ከተማ የወረዳ 11 ነዋሪ ሲሆኑ፣ በዶሮ እርባታ ስራ ይተዳደራሉ፡፡ ስራውን ከጀመሩ ረጅም ጊዜ እንዳስቆጠሩ ገልጸው፣ በአሁኑ ጊዜ 2 ሺህ እንቁላል ጣይ እና 1 ሺህ የስጋ በአጠቃላይ 3 ሺህ ዶሮዎች እንዳሏቸው ተናግረዋል፡፡

ለገና በዓል ክፍለ ከተማው በሚያዘጋጀው ባዛር ላይ 1 ሺህ ዶሮዎች እና 5 ሺህ እንቁላል በማቅረብ የተሻለ ገቢ እንዳገኙም ገልፀውልናል፡፡

ነዋሪዎች ባላቸው አነስተኛ ቦታ ላይ ዶሮ በማርባት በእንቁላል እና በዶሮ ስጋ ተጠቃሚ መሆን እንደሚችሉ አቶ በግዱ ይናገራሉ፡፡ አንድ የስጋ ዶሮ እስከ 1 ሺህ ብር ድረስ፣ እንቁላል ደግሞ ክፍለ ከተማው በሚያስቀምጠው የዋጋ ተመን መሰረት እንደሚሸጡ ይገልጻሉ፡፡

የዶሮ መኖ፣ የጫጩት እና የለማ እንቁላል ግብዓት አቅርቦት በስፋት ማግኘት ከተቻለ የዶሮ እርባታ ውጤታማ የሚያደርግ ዘርፍ መሆኑን አቶ በግዱ ይናገራሉ፡፡

በተመሳሳይ ወይዘሮ ገነት ያደቴ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 በዶሮ እርባታ ክላስተር ተደራጅተው እየሰሩ የሚገኙ ነዋሪ ናቸው፡፡ የዶሮ እርባታ ስራ መስራት ከጀመሩ 2 ዓመት እንደሞላቸው በማስታወስ፣ አሁን 350 እንቁላል ጣይ ዶሮዎች እንዳሏቸው ገልፀዋል፡፡

ለገና በዓል እንቁላል እና ዶሮዎችን ወደ ገበያ በማቅረብ የምርት አቅርቦትን ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የድርሻቸውን ለማበርከት መዘጋጀታቸውን የተናገሩት ወይዘሮ ገነት፣ በቤተሰብ ደረጃ ባለ ትንሽ ቦታ ዶሮ በማርባት ከራስ ፍጆታ አልፎ ለሽያጭ በማቅረብ ገበያን ማረጋጋት እንደሚቻል ጠቁመዋል፡፡

በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 በተለምዶ ቀጨኔ ተብሎ የሚጠራ አካባቢ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ወይንሸት ሰብስቤ የወተት ላሞችን ማርባት ከ30 ዓመት በፊት እንደጀመሩ ጠቁመው፣ ስራውን በተደራጀ መንገድ መስራት የጀመሩት ግን ከሁለት ዓመት በፊት በተጀመረው የሌማት ትሩፋት ፕሮግራም አማካኝነት መሆኑን ይናገራሉ፡፡

ወይዘሮ ወይንሸት አሁን 30 የወተት ላሞች እንዳሏቸው ገልፀው፣ በግላቸው ተጠቃሚ ከመሆን አልፈው ለሶስት ወጣቶችም የስራ እድል መፍጠራቸውን ተናግረዋል፡፡

በከተማ ደረጃ ዘርፉን በተደራጀ እና በዘመናዊ መንገድ በመስራታቸው እውቅና ማግኘታቸውን ወይዘሮ ወይንሸት ጠቁመው፣ በአንድ ቀን እስከ 150 ሊትር የወተት ምርት ያገኛሉ፡፡ በዚህም በቀን እስከ 15 ሺህ ብር ገቢ ያገኛሉ፡፡

በየካ ክፍለ ከተማ የወረዳ 11 የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ሻንበል ዳባ ዋካ፣ በወረዳው በከተማ ግብርና በቤተሰብ ደረጃ በእንስሳት እና በእጽዋት ልማት ዘርፍ የተደራጁ ተጠቃሚዎችን የመደገፍና የመከታተል ስራዎች እየተሰራ እንደሚገኝ ጠቅሰው፣ ይህም የተሻለ ውጤት እንዲገኝ ማስቻሉን ገልፀዋል፡፡

የከተማ ግብርና በበዓል ወቀት የምርት አቅርቦት እጥረት እንዳይኖር በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው የጠቆሙት ሻምበል ዳባ፣ ለመጪው የገና በዓል የምርት አቅርቦት እጥረት እንዳይፈጠር በከተማ ግብርና ስራ የደለቡ በሬዎች፣ በጎች፣ የስጋ ዶሮዎች፣ እንቁላል፣ ቂቤ እና አይብ በብዛት ወደ ገበያ ለማቅረብ በቂ ዝግጅት መደረጉን አስታውቀዋል፡፡

በግለሰብ እና በተቋማት ደረጃ የተለያዩ የከተማ ግብርና ስራዎች እየተሰሩ ሲሆን፣ በእንስሳት ዘርፍ የወተት ላሞች እንዲሁም እንስሳትን በማድለብ ረገድ አበረታች ውጤት ተገኝቷል፡፡ የእንቁላል እና የስጋ ዶሮዎች በማርባት ረገድም እንዲሁ ያሉት ሻምበል ዳባ፣ በወረዳው በየቀኑ ከ10 እስከ 15 ሺህ እንቁላል ለእሁድ ገበያ ይቀርባል። ከዚህ በተጨማሪ ለግብርና ውጤቶች መሸጫነት በተሰሩ ሱቆች እና በተቋማት የከተማ ግብርና ምርቶች በስፋት እየቀረቡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

እንደ ሻንበል ዳባ ገለጻ፣ በተቋማት እና በግለሰብ ደረጃ 20 የደለቡ በሬዎች፣ 60 በጎች፣ በክላስተር ደረጃ የረቡ 20 ሺህ የስጋ ዶሮዎች እና 85 ሺህ እንቁላል ለገና በዓል በተዘጋጁ ባዛሮች ይቀርባል፡፡

በጉለሌ ክፍለ ከተማ የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ጽህፈት ቤት የእንስሳት ሃብት ልማት ቡድን መሪ አቶ ሞገስ አባይነህ የከተማ ግብርና በበዓል ወቅት የምርት አቅርቦት እጥረት እንዳይኖር በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

በክፍለ ከተማው ለገና በዓል የተለያዩ የከተማ ግብርና ውጤቶች እንደሚቀርቡ አስታውቀዋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥም 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን እንቁላል፣ 10 ሺህ 800 ኪሎ ግራም የዶሮ ስጋ፣ 9 ሺህ 500 ሊትር ወተት፣ 20 ሺህ ኪሎ ግራም የእንስሳት ስጋ፣ 9 ሺህ 800 ኪሎ ግራም የማር፣ 15 ነጥብ 5 ኩንታል ቲማቲም፣ 26 ነጥብ 5 ኩንታል ቀይ ሽንኩርት እንደሚቀርብ ገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ በክፍለ ከተማው ከግቢና ከጓሮ አትክልት 274 ነጥብ 5 ኩንታል ምርት ወደ ገበያ ይቀርባል፡፡ እነዚህ ምርቶች በክፍለ ከተማው እና በወረዳዎች በተዘጋጁ ባዛሮች ለሸማቾች እንደሚቀርቡ አቶ ሞገስ አስታውቀዋል፡፡

የከተማ ግብርና በከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚደረግ ወሳኝ ጥረት ነው፡፡ ይህ ዘርፍ በውስን ቦታ ላይ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሚከናወን ሲሆን፣ የእንስሳት፣ የዶሮ፣ የዓሳ እርባታ፣ ንብ ማነብ፣ ወተትና የወተት ተዋፅኦ ምርትን፣ ፍራፍሬ፣ የጓሮ አትክልት ማምረት እና የተመረቱ ምርቶችን ማቀነባበርንም እንደሚያካትት እሙን ነው፡፡ ይህም በተለይ በበዓላት ሰሞን የሚያጋጥም የምርት አቅርቦት እጥረት ችግር እንዲቀንስ አስችሏል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በከተማ ግብርና የሚያገኙትን ምርት ለቤት ፍጆታ ከማዋል ባሻገር ለገበያ በማቅረብ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ማግኘት ከጀመሩ ሰነባብተዋል፡፡ የግብርና ምርትና ምርታማነት በመጠንና በጥራት በማሳደግ ኢኮኖሚን በማሻሻል በከተማና በከተማ ዙሪያ የሚኖረው የህብረተሰብ ክፍል የምግብ ዋስትና እንዲሻሻል እያደረገ ያለ ዘርፍም ነው፡፡

የከተማ ግብርና በተለይ "ከእርሻ ወደ ማዕድ" ያለውን ጉዞ በማሳጠር፣ ነዋሪዎች የፈለጉትን ምርት በፈለጉት ሰዓት በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ የሚያስችል ዘላቂ መፍትሔ እንደሆነ በብዙ ተፅፏል። አትክልቶች፣ ፍራፍሬዎች፣ እንቁላል፣ ዶሮ፣ ዓሳ፣ ወተት፣ አይብ፣ ቅቤ፣ እርጎ፣ የሰብል እና ጥራጥሬ ምርቶችን በጥራት፣ በብዛትና በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ ያለው ሚና ከፍተኛ እየሆነ መጥቷል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ወንድወሰን አካሌ የከተማ ግብርና በበዓል ወቅት የምርት አቅርቦት እጥረት እንዳይኖር በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ እንደሚገኝ ይገልጻሉ፡፡

እንደ አቶ ወንድወሰን ገለጻ፣ የከተማ ግብርና በሶስት ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጎ እየሰራ ይገኛል፤ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ የከተማ ግብርና ምርትና ምርታማነት ማሳደግ፣ አርሶ አደሮች ከከተማዋ ልማት ጋር አብረው እንዲለሙ ማድረግ፣ ደህንነቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ የከተማ ግብርና ምርትና ግብዓት አቅርቦት ለማህበረሰቡ ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡

በበዓል ወቅት የምርት አቅርቦት ላይ ትኩረት በማድረግ ሸማቹ ማህበረሰብ ከአምራቹ ላይ ምርት ማግኘት እንዲችል ሰፊ ስራ እየተሰራ መሆኑን ያወሱት አቶ ወንድወሰን፣ ምርቱም በተመጣጣኝ ዋጋ በእሁድ ገበያ፣ በባዛሮች እና በየክፍለ ከተሞች በተዘጋጁ የግብርና ምርቶች መሸጫ የገበያ ማዕከላት ላይ በብዛት እየቀረበ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የእንስሳት ልማት እና ልህቀት ማዕከል የሚያመርታቸውን ምርቶችም በማዕከሉ በተዘጋጁ የመሸጫ ሱቆች እና በሁሉም ክፍለ ከተሞች በተዘጋጁ የመሸጫ ሱቆች ይቀርባሉ፤ የገና በዓልን ምክንያት በማድረግ እንቁላል፣ ወተት፣ ቅቤ፣ አይብና የደለቡ ከብቶች እየቀረቡ ነው ብለዋል፡፡

ይህም የከተማ ግብርና በዋናነት ገበያውን በማረጋጋት ሸማቹ ማህበረሰብ በተመጣጣኝ ዋጋ ምርት ማግኘት እንዲችሉ አስችሏል ያሉት አቶ ወንድወሰን፣ በተጨማሪም ተጠቃሚዎች ንጹህ እና ጥራቱ የተጠበቀ ምርት እንዲያገኙ አግዟል ሲሉ አክለዋል፡፡

በጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ላይ የተሰማሩ ግለሰቦችም ከራሳቸው ፍጆታ የተረፈውን ምርት ለገበያ በማቅረብ ላይ ይገኛሉ ያሉት አቶ ወንድወሰን፣ ተቋማትም የምርት ማዕከል እየሆኑ መጥተዋል፡፡ ያመረቱትን የከተማ ግብርና ምርት ለሰራተኞቻቸው ከማቅረብ በተጨማሪ ለማህበረሰቡ በመሸጥ ራሳቸውን ይደጉማሉ፡፡

አቶ ወንድወሰን ኮሚሽኑ በበዓላት ወቅት የምርት አቅርቦት መከታተል ብቻ ሳይሆን ደህንነቱ፣ ጤንነቱ እና ንጽህናው የተጠበቀ ምርት ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ የቁጥጥር ስራ እየሰራ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡ በማስፋፊያ ክፍለ ከተሞች ላይ ሽንኩርትና ሌሎች የጓሮ አትክልቶች በስፋት እየተመረተ ሲሆን፣ የተመረተው ምርትም በቅዳሜና እሁድ ገበያ ላይ ለተጠቃሚው ማህበረሰብ ተደራሽ እንዲሆን እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የእንስሳት ሃብት ልማት ዘርፍ ዳይሬክተር ደጀኔ ጌታቸው (ዶ/ር)፣ በከተማ ግብርና ሰፊ ስራ እየተሰራ መሆኑን በመጠቆም፤ በበዓል ወቅት የምርት አቅርቦት እጥረት እንዳይኖር በማድረግ ረገድ የተጫወተው ሚና ከፍተኛ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

እንደ ደጀኔ (ዶ/ር) ገለጻ፣ በከተማ ግብርና ስራ የተገኘ 10 ነጥብ 8 ሚሊዮን እንቁላል፣ ከ450 ሺህ እስከ 500 ሺህ ዶሮዎች፣ 3 ነጥብ 3 ሚሊዮን ሊትር ወተት፣ 1 ነጥብ 2 ሚሊዮን ኪሎ ግራም ስጋ፣ 95 ሺህ በጎች እና 88 ሺህ ፍየሎች ለገና በዓል ገበያ ቀርበዋል፡፡



ፎቶ- ከፋይል
የገና በዓልን ምክንያት በማድረግ በአዲስ አበባ ለገበያ ከቀረቡ የከተማ ግብርና ምርቶች በጥቂቱ

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# ብዝሃ ሕይወትን እየታደገ ያለው ልማት

- በአዲስ አበባ ስነ ምህዳሩን ያገናዘበ የወንዝ ዳርቻ ልማት መከናወኑ ተጠቁሟል

**በለይላ መሀመድ**

አዲስ አበባ ከ76 በላይ ወንዞች አሏት። እነዚህ ወንዞች ለነዋሪዎች የመጠጥ ውሃን ጨምሮ የተለያዩ አገልግሎቶች ሲሰጡ የቆዩ፣ የብዙዎች ታሪክና ትዝታ የተከተበባቸው ናቸው:: “ማን ይናገር የነበረ፤ ማን ያርዳ የቀበረ” እንደሚባለው ወንዞቹ በጥንት ጊዜ ይዞታቸው ምን ይመስል ነበር? ለምን አገልግሎት ይውሉስ ነበር? የሚለውን ነዋሪዎችን ጠይቀናል::

“የቀበናን ወንዝ ጠጥቼ ነው ያደግኩት” ይላሉ ትውልዳቸውና እድገታቸው በአዲስ አበባ ከተማ ቀበና አካባቢ እንደሆነ የሚናገሩት ወይዘሮ ምንዳ በቀለ:: በወቅቱ እንደ አሁኑ የቧንቧ ውሃ ስላልነበረ ከወንዙ በእንስራ ለመጠጥ እቀዳ ነበር:: አካባቢው ጽድት ያለና ውሀውም ኩልል ያለ ከመሆኑም በላይ ሲጠጣም ይጣፍጥ ነበር:: ደስ እያለን ነበር የምንጠጣው:: በአካባቢውም እንደአሁኑ ብዙ ሰው አይኖርም ነበር። ውሃው ከመጠጥ ባለፈም ለተለያዩ አገልግሎቶች ይውል ነበር:: ማህበረሰቡ ልብሱን የሚያጥበው በዚሁ ወንዝ ነበር:: ልጆችም ይዋኙበት እንደነበር ገልጸዋል::

ወንዙ ዙሪያውን በባህር ዛፍና ሌሎች ትላልቅ እጽዋት የተሸፈነና ጫካ ስለነበር እንደ ዝንጀሮ፣ ጦጣ ያሉ የዱር እንስሳት በብዛት ይኖሩበት ነበር:: ጫካው ስለሚያስፈራ እንዲሁ ዝም ብሎ ለብቻ የሚገባበት አልነበረም:: ጫካው በቡድን ካልሆነ ለብቻ ያስፈራ ነበር:: የማገዶ እንጨት ለቤተሰቦቻችን የምንለቅምበትም በዚሁ በቀበና ወንዝ ዙሪያ ነበር:: ለችቦ እንጨት የምናመጣው እንዲሁ::

ወይዘሮ ምንዳ እንደሚገልፁት፣ በሂደት አዲስ አበባ እያደገችና መኖሪያ ቤቶች በስፋት እየተሰሩ ሲሄዱ፣ ከቤቶቹና ከተለያዩ ፋብሪካዎች ወደ ወንዙ ፍሳሽ ቆሻሻዎች መለቀቅም ተጀመረ:: የተለያዩ ነገሮች ወደ ወንዙ መጣል ተጀመረ:: አይናችን እያየ ወንዙ መቆሸሽና መጥቆር ብሎም መበከል ጀመረ:: በዙሪያው ያለው ደን ተመናመነ፤ እጽዋቱ ደረቁ:: እንኳን ውሀ መቅዳትና እንጨት መልቀም ይቅርና በአካባቢው ለማለፍ እንኳን አስቸጋሪ እየሆነ መጣ::

“የድሮው እና የአሁኑን ስመለከት ይከፋኛል:: ያን የመሰለ ንጹህና ለምለም ስፍራ ቆሽሾ ሳየው ውስጤ ያዝን ነበር። አሁን እየተከናወነ ያለው የወንዝ ዳርቻ ልማት ብክለቱን በማስወገድ ወደቀደመው ገጽታቸው ይመልሳቸዋል ብየ አስባለሁ” ብለዋል፤ ወይዘሮ ምንዳ::

አቶ ተገኑ መገርሳም በተመሳሳይ አዲስ አበባ ከተማ ለቡ አካባቢ ተወልደው ማደጋቸውን ይናገራሉ:: እሳቸውም የአዲስ አበባ ከተማ ወንዞች የቀደመ ገጽታ ምን እንደሚመስሉ ሲገልጹ፤ “እኔና ጓደኞቼ ውሏችን ወንዝ ዳር ነበር። ወንዞቹና የወንዞቹ ዳርቻ ውበትና ምቾት ነበራቸው:: እኔ ተወልጄ ባደግኩበት


ፎቶ- ከፋይል
የአዲስ አበባ የወንዝ ዳርቻ ልማት ከፊል ገፅታ

ለቡ አካባቢ ላፍቶን ይዞ ጀሞን ተከትሎ ይፈስስ የነበረው የሰዲቃ ወንዝ እንጠጣው፤ ልብስም እናጥብበት ነበር። በወንዙ ዙሪያ የነበሩ እጽዋት ማንም ሳይተክላቸው በራሳቸው የበቀሉ ሀገር በቀል ዛፎች ነበሩ:: በጫካው ውስጥ ጦጣ፣ ዝንጀሮ፣ ጥንቸል፣ ሚዳቋ፣ ሰስ የመሳሰሉ የዱር እንስሳት ይኖሩበት ነበር:: ወንዙን ተከትሎ የሚበቅል ‘አለልቱ’ የሚባል የጥርስ መፋቂያ እንጨት በመቁረጥ ጥርሳችንን እንፍቅ የነበረውን ትዝታ ሳስታውሰው ልቤ በሀሴት ይሞላል:: እናቶቻችን ማገዶ የሚለቅሙትም እዚሁ ወንዝ ዳር ከነበረው ጫካ ነበር:: ከብቶቻችንን እናጠጣበትም ነበር:: ከተማዋ ውስጥ በነበሩት ወንዞች እየተንቀሳቀስን እንዋኝ፣ እንጠጣውም ነበር::

ቀስ በቀስ ህገ ወጥ ቤቶች በመገንባታቸው አካባቢው የነበረው ደን እየተመናመነ መጣ:: ውሃውም በአካባቢው በሰፈረው ህዝብ እየተበከለ፣ ሙቀት እየጨመረ መጣ:: የዝናብ ወቅቶች እየተዘበራረቁ ነው:: ድሮ ወንዝና ወንዝ ዳር ጊዜን ማሳለፍ ያስደስት ነበር:: በጊዜ ሂደት ግን እንኳን መዋል ለማለፍ ያስጠላል:: የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ወንዞችን ወደቀደመ መልካቸው እየቀየራቸው ስለሆነ ተስፋ ሰጪ ሆኖ አይቻዋለሁ” ብለዋል::

የወንዝ ዳርቻዎች መልማት የብዝሀ ህይወት እንዲያገግም የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው ያሉት በአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የስርአተ ምህዳርና ብዝሀ ህይወት ተመራማሪ እና በወንዝ ዳርቻ ልማት ውስጥ ከእንጦጦ እስከ ፒኮክ ያለው የወንዝ ዳርቻ ልማት አስተባባሪ ወይዘሮ እስከዳር አልታየን አነጋግረናቸዋል:: እንደ እሳቸው ገለጻ፤ በቅድሚያ ብዝሀ ህይወት ማለት እንስሳትን፣ እጽዋትን፣ በዓይን የማይታዩ ደቂቅ አካላት (ማይክሮ ኦርጋኒዝም) ጨምሮ ህይወት ያላቸውን ፍጥረታት ሁሉ አጠቃልሎ የሚይዝ ነው:: የወንዞች መልማት ለብዝሀ ህይወት ሀብቶች ማገገምና በህይወት ለመኖር ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው:: ምክንያቱም ወንዞች የእነዚህ በርካታ ህይወት ያላቸው ነገሮች መኖሪያ ወይንም መተላለፊያ ናቸው::

የተፈጥሮ ወንዞች የራሳቸው መገለጫዎች አላቸው:: ዓመቱን ሙሉ መፍሰስ፣ በአካባቢው በርካታ እጽዋት መገኘት፣ ያልተበከለ ውሃና አፈር እንዲሁም በውሃው ውስጥ እንስሳትና ነፍሳት መኖር ናቸው የሚሉት ተመራማሪዋ፣ ወንዞቹ ከተበከሉ ወዲህ ግን እነዚህ ህይወት ያላቸው ፍጥረታት ሁሉ ጠፍተዋል:: ወንዝ ዳርቻዎቹ ላይ የነበሩት እጽዋት መጥፋት ደግሞ አዕዋፋት እንዳይኖሩ አድርጓቸዋል። ብክለቱ ያደረሰው ተጽዕኖ በእነዚህ ህይወት ባላቸው ነገሮች መጥፋት ይገለፃል::

ለዘመናት ተረስተው የቆዩት ወንዞች የተጎሳቆለውን ገፅታቸውን ለመቀየር፣ ከብክለት በመታደግ ወደ ቀደመ ይዞታቸው ለመመለስ በአዲስ አበባ ከተማ ስነ ምህዳሩን ያገናዘበ የወንዝ ዳርቻ ልማት ተካሂዷል:: በዚህም የሚጠበቁ ዋና ዋና ጥቅሞች አሉ:: ከእነዚህ መካከል ዋናው የውሃ ጥራትን ማሻሻል ነው። ለዚህ ጤናማ የወንዝ ዳርቻ ልማት እንደ ማጣሪያ ሆኖ ያገለግላል:: በወንዝ ዳርቻ የሚለሙ እጽዋት ብዙ ጠቀሜታ አላቸው። የሚለሙ እጽዋት ወደ ወንዝ የሚለቀቁ መርዛማ ኬሚካሎችን እንዳይገቡ ይታደጋሉ:: የውሃው ንጹህ መሆን በውሃ ውስጥ ለሚኖሩ እንደ አሳ፣ እንቁራሪት ላሉ ህይወት ያላቸው ነገሮች በህይወት ለመኖር ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥርላቸው ተመራማሪዋ ያነሳሉ።

ሁለተኛው ጠቀሜታ የአፈር መሸርሸርን ይከላከላል:: ሶስተኛው የአየር ንብረት እንዳይዛባ ያደርጋሉ:: እንደ ካርቦንዳይኦክሳይድ አይነት አማቂ ጋዞች ወደ ከባቢ አየር እንዳይለቀቁ ያደርጋሉ። ከተሞች 70 በመቶ ለሚሆነው የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ናቸው። ባላቸው ትራንስፖርት፣ የሀይል አጠቃቀም፣ የኢንዱስትሪ አጠቃቀም ለአማቂ ጋዝ ልቀት ዋነኛ ምንጮች ናቸው:: ይህ የወንዝ ዳርቻ ልማትም የአየር ንብረት መዛባትን ይቋቋማል:: በወንዝ ዳርቻ የሚለሙ እጽዋት አማቂ ጋዞቹን መምጠጥ ይችላሉ:: በተለይም ሀገር በቀል እጽዋት በተፈጥሯቸው አማቂ ጋዞችን የመምጠጥ ሀይላቸው ከፍተኛ ነው:: ወንዝ ዳርቻ ሲባል 70 ሜትር ወንዙን ተከትሎ በሁለቱም በኩል የሚካሄደው ልማት ሲሆን በዚህ በ70 ሜትር ስፋት ላይ እጽዋት በተለይም ሀገር በቀል እጽዋት ሲተከሉ ካርቦንን በመምጠጥ የአየር ንብረት ለውጥን በመቋቋም ረገድ ሁነኛ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ::

በተጨማሪም ወንዝና የወንዝ ዳርቻዎች እንደ ስነ ህይወታዊ መተላለፊያ (Biological corridor) ሆነው ያገለግላሉ:: ወንዞች መልክዓ ምድሮችን የሚያገናኙ አረንጓዴ ድልድዮች ናቸው ይላሉ ተመራማሪዋ:: ወንዞች ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት አሉ:: የወንዝ ዳርቻ ልማቱ እነዚህ ውሃ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት በሰላም እንዲንቀሳቀሱና እንዲራቡ ምቹ ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል። ይህም በውሃ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት ዝርያ እንዳይመናመኑ ያደርጋል። እንዲሁም ሌሎች ጥቃቅን ነፍሳት በህይወት እንዲኖሩ ለማድረግ ጠቃሚ ናቸው::

የአንዱ መኖር ለሌላው መኖር ወሳኝነት እንዳለው ለመገንዘብ የሚከተለውን በአስረጅነት ማንሳት በቂ ነው:: ትላትሎች ለመኖር እርጥበት ይፈልጋሉ። የትላትሎች መኖር ለአፈር ለምነት ጠቃሚ ናቸው:: የአፈር ለምነት ደግሞ ለእጽዋት፤ የእጽዋት መኖር ደግሞ ለአዕዋፋትና ለሰው ልጆች ጠቃሚ ናቸው:: ተመጋጋቢ ናቸው:: ማንኛውም አካባቢው ላይ መኖር ያለበት ህይወት ያለው ነገር መኖር፤ ጤናማ ውሃ እና አፈር መኖሩን ያሳያል::

ከእንጦጦ እስከ ፒኮክ የሚሸፍነውን የወንዝ ዳርቻ ልማት የሚያስተባብሩት ተመራማሪዋ እንደሚገልፁት፤ በወንዝ ዳርቻ ላይ ሰፍረው ለወንዙ መበከል ምክንያት የሆኑ ነዋሪዎች መነሳትና የወንዝ ብክለትን የሚከላከል ደንብ 180/2017 መውጣቱ ወንዞች ከለሙ በኋላ ንፁህና ተፈጥሯዊ ይዞታቸውን ይዘው እንዲቀጥሉ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። በአሁኑ ወቅት ወንዞቹ ምንም አይነት ሽታ የላቸውም:: ውሃው ጽድት ብሎ እየታየ ነው:: ሌላው እንጦጦ የላይኛው ተፋሰስ እንደመሆኑ መጠን እንደከዚህ ቀደሙ ከላይ ተንደርድሮ የሚመጣ ጎርፍ አሁን የለም። በዚህም የአፈር መሸርሸር አይፈጠርም። የአፈር መሸርሸር ከሌለ መቅረት ያለበት ውሃ እዛው ሰርጎ ይቀራል። ይህም ምንጮች እንዲጎለብቱ፣ የከርሰ ምድር ውሃ እንዲጨምር ያደርጋል:: ዓመቱን ሙሉ የሚፈሱ ወንዞች ይኖራሉ:: የጠፉ አዕዋፋትና በውሃ ውስጥ የሚኖሩ እንደ ትናንሽ አዞዎች፣ አሳዎችና እንቁራሪት ዓይነቶች ይመለሳሉ::

ተመራማሪዋ እንደሚያስረዱት፤ የወንዝና ወንዝ ዳርቻ ልማቱ ከብዝሀ ህይወት ማገገምና መመለስ ባለፈም ለመዝናኛነት እየዋለ ነው:: ካፍቴሪያዎች፣ አንፊ ቴአትሮች፣ ምቹ የሳይክል መንገድ አላቸው:: በዚህም ከስነ ምህዳራዊ ጠቀሜታ ባለፈ የሰዎችን ማህበራዊ መስተጋብር ጨምሯል:: ትኩረቱ የወንዞቹን ብክለት አቁሞ ወደ ተፈጥሯዊ ይዞቱ እንዲመለስ ማድረግ ቢሆንም ይህንን ተከትሎ የተለያዩ ጠቀሜታዎች እየሰጠ፣ የሀገርን ገጽታም እየቀየረ ይገኛል:: ቀደም ባለው ጊዜ አዲስ አበባ ወንዟ ሲባል ሰው አፍንጫውን ይዞ ያልፍባቸው የነበረው ታሪክ ተቀይሮ አሁን ባለው ደረጃ ጸድቶና ለመዝናኛነት ሲውል መታየቱ ከኢትዮጵያም አልፎ ተርፎ ለአፍሪካ ኩራት ነው::

ስነ ምህዳር ሲጠበቅ እርስ በእርስ የተሰናሰለው ብዝሀ ህይወት ያገግማል፤ ይመለሳል:: ብዝሀ ህይወት ሲመለስ ደግሞ ጠቅለል ባለ ሁኔታ የሰው ልጅ ምግብ፣ ንጹህ አየር እና መድኃኒት ያገኛል። እነዚህን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች ለማግኘት ሁሉም ለስነ ምህዳር መጠበቅ የድርሻውን መወጣት እንዳለበት ተመራማሪዋ መክረዋል::

# የአንጋፋው ሙዚየም ፍካት

**“ሙዚየሙን ሁለት ሶስት ጊዜ እየዞርኩ አየሁት፤ ያየሁት ነገር በጣም አስደንቆኛል”**

**ከሳዑዲ አረቢያ የመጣው ወጣት ኢብራሂም ጋታኔ**

**በፋንታነሽ ተፈራ**





ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

የታደሰው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሙዚየም በውጭ ሀገራት ዜጎች ሲጎበኝ

ወይዘሮ ሂሩት ነጋሽ ይባላሉ። በኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም ቅርሶችን ሲጎበኙ ነው ያገኘናቸው። “ማንኛውም ሰው ገብቶ መጎብኘት እንደሚችል አላውቅም ነበር፡፡ አድራሻውን በዩቲዩብ ስመለከት ታሪኬን ለማወቅ ልጆቼን ይዤ ለጉብኝት መጣሁ” ይላሉ፡፡

“የሚታየው ነገር ቀልብን ይስባል፤ የእንግዳ ተቀባዮቹ ትህትናም ይማርካል። ውጭውን ሳየው አዲስ አበባ ሳይሆን ውጭ ሀገር ያለሁ ነው የመሰለኝ፡፡ ወደ ውስጥ ስንገባ ደግሞ ተማሪ ሆኜ የማደንቃትን ሉሲን በአይኔ አየኋት። የእንስሳት ቅሪተ አካል ጥንታዊ መመገቢያና መጠጫ ቁሳቁሶች፣ ስእሎችና ሌሎችንም ጎብኝቻለሁ፡፡ ቅርሶቹ በዚህ መንገድ መቀመጣቸው የኢትዮጵያን ገናና ታሪክና ምድረ ቀደምትነት በአግባቡ ለማሳየት ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ነው” ሲሉም አክለዋል፡፡

“አሜሪካ ሀገር በሄድኩበት አጋጣሚ በዚያ የሚገኘውን የተፈጥሮ ሙዚየም አይቻለሁ፤ ከዚህ በፊት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየምን ስላየሁት እንዲህ ቢሆን ብዬ ተመኝቼ ነበር፡፡ አሁን ስጎበኘው ግን የበለጠ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ብዙ ቅርሶች የያዘም ነው፡፡ ታሪካችን ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአለምም የሚተርፍ ነው፡፡ በዚህ መልክ ተደራጅቶ በአግባቡ በእንክብካቤ መያዙ ታሪክን ህያው እንዲሆን የሚያደርግ ነው፡፡ ለሌሎች አካላትም በኩራት ያየሁትን እንድናገር ያደርገኛል” ሲሉ የልባቸው መሻት እውን እንደሆነ አብራርተዋል፡፡

ሌላኛው በሙዚየሙ ከሁለት ጓደኞቹ ጋር በመሆን ሲጎበኝ ያገኘነው ከሳዑዲ አረቢያ የመጣው ወጣት ኢብራሂም ጋታኔ ነው፡፡ “ሙዚየሙን ስጎበኝ የመጀመሪዬ ነው፡፡ ሁለት ሶስት ጊዜ እየዞርኩ አየሁት፤ ያየሁት ነገር በጣም አስደንቆኛል” ሲል የተመለከተው ነገር የፈጠረበትን ስሜት ገልጿል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም ግቢው ሳቢ፣ ለጎብኚዎችም ምቹ መሆኑንም አክሏል፡፡

ወይዘሮ እዥዋማከ አግቦ ሌላኛዋ ከናይጀሪያ የመጡ ቱሪስት ናቸው። ሙዚየሙን ሲጎበኙ የመጀመሪያቸው መሆኑንም ነግረውናል፡፡ “በሙዚየሙ የሰው ዘር ቅሪተ አካል የሆነችው ሉሲን አይቻለሁ፡፡ በፊት የነበሩትን የኢትዮጵያ ነገስታት ታሪክን ተመልክቻለሁ። የተለያዩ ታሪክ ያላቸው አልባሳትም አሉ። እነዚህንም በመጎብኘቴ ደስ ብሎኛል። የሙዚየሙ ግቢም አረንጓዴ ነው፡፡ ብዙ ታሪክ አላችሁ፡፡ ሌላ ጊዜም መጥቼ እጎበኛለሁ፡፡” ሲሉም በሙዚየሙ የነበራቸውን የጉብኝት ቆይታ እንደወደዱት ሀሳባቸውን አጋርተዋል፡፡

የዝግጅት ክፍላችንም ባደረገው ቅኝት፣ ታሪክን ከውበት ጋር አጣምሮ የያዘው ሙዚየም ከውጭ ሲገቡ አበቦቹ እይታን ከመሳብ አልፈው መአዛቸው ከሩቅ የሚጣራ፣ መሬቱን አረንጓዴ ያደረገው ለምለም ሳር፣ የደከመው የሚያርፍባቸው ወንበሮች፣ መኪና ማቆሚያ ምቹና ሰፊ ቦታ፣ ከሩቅ አይንን ሰቅዞ የሚይዘው ፋውንቴን እንዲሁም የህንፃው ቀለም የጎብኚዎችን ቀልብ ለመያዝ ትልቅ አቅም እንደሆኑት መረዳት ችሏል፡፡ “ደጅአፏን አይተህ ከቤቷ ግባ…” እንዲል የሀገራችን ብሂል የውጭው ውበት የውስጡን ለማየት ጉጉትን የሚያጭር ሆኖ አግኝቶታል።

ወደ ውስጥ ሲገባም ቅርሶቹ ደረጃውን ጠብቆ በታደሰው ቦታ በየፈርጃቸው ህያውነታቸውን ለማመስከር ለጎብኚዎች ምቹ ሆነው ተቀምጠዋል፡፡ በተለየ ሁኔታ የውጭ ጎብኚዎች እጃቸውን አፋቸው ላይ ጭነው በትኩረት ሲመለከቷቸው መታዘብ ችሏል፡፡

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም የትምህርት ዴስክ ኃላፊ አቶ ንጉሱ መኮንን ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት ማብራሪያ፤ “ሙዚየሙ እንዲታደስ የተደረገበት ዋነኛ ምክንያት፤ በርካታ ዓመታትን ያገለገለ በመሆኑ፣ የሙዚየሙን ውስጣዊና ውጫዊ ክፍል ደረጃውን በማሻሻል ለጎብኚዎች ምቹ ለማድረግ እንዲሁም ኢትዮጵያ ያላትን ብዝሃ ቅርስ ለማስተዋወቅ እድል ለመፍጠር ነው” ብለዋል፡፡

በአካባቢው የተከናወነው የኮሪደር ልማትም ሆነ የውስጡ እድሳት ለሙዚየሙ የገጽታ ፍካት ትልቅ አስተዋፅኦ እንዳለው የሚናገሩት አቶ ንጉሱ፣ ከዚህ በፊት ከነበረው በተሻለ መንገድ በግቢው ለአካል ጉዳተኞች፣ ለህፃናት እንዲሁም አረጋዊያን ማረፊያ ወንበሮች ተሰርተዋል፡፡ ለአይን የሚስብ አረንጓዴ ልማትና ፋውንቴን ያለው መሆኑ አጠቃላይ የግቢውን ገፅታ የተዋበ እንዲሆን እንዳደረገውም አክለዋል።

“በየትኛውም ዓለም ያሉ ብሔራዊ ሙዚየሞች የሚጠቀሙትን የኤግዚቢሽን አደረጃጀት ቴክኖሎጂን ተጠቅመን ማደስ መቻላችን በፊት ከነበረው የሙዚየሙ ገፅታ ላይ ውበት እንዲጨምር አድርጓል። ቅርሶቹ በጽሑፍ እንዲሁም በስዕላዊ መረጃ በግልፅ መቀመጣቸው ጎብኚዎቹ ታሪኩ ገብቷቸው እንዲጎበኙ እና ደስተኛ እንዲሆኑ የሚያደርግ ነው” ሲሉ ተናግረዋል፡፡

እንደ አቶ ንጉሱ ገለጻ፣ የታሪክና የአርኪዮሎጂ ስብስብ ክፍሉ እንዲሁም የቅድመ ሰው ዘር አመጣጥ እና የእንስሳት ቅሪተ አካል የሚታይበት ክፍል ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ታድሶ ተጠናቅቋል፡፡ ቀሪዎቹን የብሔር፣ ብሔረሰቦች ባህል፣ አኗኗር፣ ታሪክ እንዲሁም የሥነ ጥበብ ውጤቶች የሚታዩበት ሁለት ክፍሎች ከታደሱት ጋር በተናበበ መልኩ በሂደት ይታደሳሉ፡፡ እነዚህ ክፍሎች ታድሰው ለአገልግሎት ሲበቁ ሙዚየሙ ከበፊቱ በተሻለ መልኩ ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ጎብኚዎች እንዲሁም ተመራማሪዎች ጭምር የሚጠቅም ነው፡፡

ሙዚየሙ በቅርስ ስብስቡ ታዋቂ የሆኑ፣ ሉሲን፣ ሰላምንና አርዲን የመሳሰሉ ሀገራችን በሰው ዘር አመጣጥ ያላትን ቦታ የሚያሳዩ፣ በታሪክ፣ በባህልም ሆነ በስነ ጥበብ ኢትዮጵያን የሚያስጠሩ ቅርሶችን የያዘ፣ እድሳቱም ይህንን የበለጠ በሚያጎላ መልኩ የተከናወነ ነው፡፡

“የከተማ መልማትና መዘመን ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች አሉት” የሚሉት የትምህርት ዴክስ ኃላፊው፤ ለገፅታ ግንባታ፣ ለኢኮኖሚ ምንጭነት እንዲሁም ለማህበረሰቡ የሚሰጠው እርካታ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በተለይ ደግሞ ከአየር ማረፊያ እስከ እንጦጦ ፓርክ ድረስ ያለው መንገድ የሙዚየም ኮሪደር ተብሎ ስለሚጠራ ጎብኚዎች ከአየር ማረፊያ ጀምሮ ጎብኝተው እስከሚመለሱ ድረስ በተመቻቸው መንገድ ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲያገኙ ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡ ይህ የጎብኚዎችን የቆይታ ጊዜ ይጨምራል፤ ገቢ ያስገኛል፤ የሃገሪቱንም ሃብት መጠቀም ያስችላል ነው ያሉት፡፡

ቱሪስቶች በሚያገኙት አገልግሎት ልክ ነው ገንዘባቸውን የሚያወጡት ያሉት አቶ ንጉሱ፤ ኮሪደር ልማቱም ሆነ ከሱ ጋር ተያይዞ የታደሱና ለአገልግሎት ምቹ የሆኑ አካባቢዎች መፈጠራቸው ለብሔራዊ ሙዚየሙ ትልቅ እድል ፈጥሮለታል፡፡

የመጣው ጎብኚ እርካታ አግኝቶ፣ ጥሩ ነገር በአዕምሮው ይዞ እንዲመለስ ማድረግ ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ መሆኑን የገለጹት አቶ ንጉሱ፣ ይህም በሂደት ለመጪው እድላችን መደላድል እንደሚሆን አብራርተዋል፡፡

ወርሃ ታህሳስና ጥር የውጭ ሀገር ጎብኚዎች ኢትዮጵያን ለመጎብኘት የሚያቅዱበት እንደሆነ የዘርፉ ምሁራን ሲናገሩ ይደመጣል፡፡ ቱሪዝሙን የበለጠ አጎልብቶ የኢኮኖሚ አቅምን በማሳደግ ረገድ አወንታዊ ሚና የሚጫወት ገቢን ለማግኘት እንደ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም ነባሮችን መዳረሻዎች ማልማት፣ አዳዲሶችን ማስፋፋትና መሰረተ ልማቶቻቸውን የተመቸ ማድረግ ይገባል። ለዚህ ደግሞ እየተሰራ ያለውን ስራ አጠናክሮ ማስቀጠል ያስፈልጋል እንላለን፡፡

## ከበዓላት... ከገጽ 5 የዞረ

መደበኛና ማህበራዊ ሚዲያዎችን፣ ገፅ ለገፅ በሚኖሩ መድረኮችን በመጠቀም ስለበጎነት ለማህበረሰቡ ግንዛቤ በመፍጠር እየተሰራ ይገኛል፡፡ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት በመሳተፍ የተሻለ እንቅስቃሴ ለሚያደርጉ ግለሰቦችና ድርጅቶች እውቅና በመስጠት የበለጠ እንዲሰሩ የማነሳሳትና ሌሎች ትምህርት ወስደው እንዲሳተፉ በማድረግ በጎነት ባህል እንዲሆን እየተሰራ እንደሚገኝ ወይዘሮ አስራት ጠቁመዋል፡፡

ከዚህ ባሻገር ቀደም ብሎ የፀደቀውና ባለፈው ዓመት ተግባራዊ መሆን የጀመረው የበጎ ፈቃድ አገልግሎትና የማህበራዊ ኃላፊነት አሰራር ደንብ ቁጥር 161/2016ን በተጠናከረ ሁኔታ ወደ ስራ ለማስገባት፣ ዜጎች በግልና በተደራጀ መንገድ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንዲሳተፉና ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ለማስቻል በደንቡ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ እየተሰራ እንደሚገኝ አብራርተዋል፡፡

### ባህል እንዲሆን ምን መሰራት ይኖርበታል?

በበዓል ሰሞን የሚደረጉ የማዕድ ማጋራትና መሰል ስጦታዎች ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው የሚሉት የሶሻል አንትሮፖሎጂ ተመራማሪው ገብሬ ይንቲሶ (ፐ/ር)፣ የስጦታና መሰል የበጎነት ስራዎች ባህል እንዲሆኑ የቀደመውን ባህላችንን ወደኋላ ዞር ብሎ መፈተሽ እንደሚገባ ያነሳሉ፡፡ በተለይ በብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ዘንድ ስጦታ የሚሰጠው 'በበዓል ሰሞን ብቻ ነው? ወይስ በሌላው ቀንም ይደረጋል' የሚለውን መለስ ብለን ብናይ ብዙ ጠቃሚ ትምህርቶችን እናገኛለን። ለምሳሌ በአሪ ብሔረሰብ በበዓል ወቅት ከሚደረገው በተጨማሪ በሌሎች መደበኛ ቀናትም በጎ ማድረግ የተለመደ ነው፡፡ አንድ ሰው መሬት ኖሮት መሬቱን የሚያርስበት በሬ ከሌለው የበሬ ጉልበት በነፃ ይሰጣል። መሬትና ዘርም ይሰጣል፡፡

ስጦታ በበዓል ቀን ብቻ የምናደርገው ሊሆን አይገባም፡፡ በበዓል ወቅት ከሚደረገው የማዕድ ማጋራትና ሌሎች ስጦታዎች በተጨማሪ ባህላችንም ውስጥ ስላለ፤ በሌላውም ቀን፣ አቅም ለሚያንሳቸው ወገኖች ድጋፍ ማድረግና ራሳቸውን የሚችሉበትን ሁኔታ ለመፍጠር መስራት ይገባል። በዚህ ረገድ ከታች ጀምሮ ልጆች ጥሩ ስብእና ተላብሰው እንዲያድጉ ማስተማር ይገባል፡፡ ስለ መልካምነት፣ ቸርነት፣ ልግስና፣ ትብብር ማስተማር ያስፈልጋል።ይህን ማድረግ ሲያድጉ በጎ ማድረግን እየተላበሱ፣ መደጋገፍና መተባበርን ባህል እያደረጉት እንዲሄዱ ያደርጋል፡፡ በማህበረሰብ መካከል ያለው ትብብርና ትስስርም ይጠናከራል፡፡ በማህበረሰብ ዘንድ ያሉትን ነባር እሴቶች በማጠናከር ስጦታ ወሳኝ የመረዳዳት ባህል ሆኖ እንዲቀጥል ለማድረግ መስራት እንደሚገባ የሶሻል አንትሮፖሎጂ ተመራማሪው አስገንዝበዋል፡፡

## በራስ ... ከገጽ 16 የዞረ

ድርጅቶቹም ለሥራ ላይ ተለማማጆች ዕውቀትና ክህሎት ሊያስጨብጥ በሚችል አግባብ ምቹ የሥራ ቦታ፣ የሥራ መሣሪያን፣ ግብዓትን በማሟላት ወጣቶቹን የበቁ ሙያተኞች የማድረግ ኃላፊነትን መወጣት ይገባቸዋል፡፡ ይህ የሥራ ላይ ተለማማጅ ወጣቶች እና የድርጅቶች ግንኙነት በአጠቃላይ ለስድስት ወራት የሚቆይ ሲሆን፤ እንደ መደበኛው የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት በቀን ለስምንት ሰዓታት፣ በሣምንት ለአምስት ቀናት፣ በወር ለሀያ ሁለት ቀናት ተፈጻሚ ይሆናል" በማለት አብራርተዋል።

በብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር የታቀፉ ወጣቶች የሚለማመዱባቸው ድርጅቶች በተለያዩ የሥራ ዘርፎች የተሰማሩ ሲሆን ከዘርፎቹ መካከልም፡- የአምራች (ማንፋክቸሪንግ)፣ የግንባታ (ኮንስትራክሽን)፣ የአገልግሎት (ሰርቪስ)፣ የንግድ እንዲሁም የከተማ ግብርና ዘርፎች በዋናነት ይጠቀሳሉ። በእነዚህ ድርጅቶች ለስድስት ወራት በሚቆየው ብቃት የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር ላይ ለሚሳተፉ 3 ሺህ ወጣቶች፤ ለትራንስፖርት አገልግሎት ወጪ የሚሆን ገንዘብ በቀን 149 ብር በማሰብ መንግስት ለእያንዳንዳቸው በየወሩ ክፍያ የሚፈፅም መሆኑን ከሥራና ክህሎት ቢሮ ያገኘነው መረጃ ይጠቁማል።

አቶ ሰብሃዲን በሰጡት ማብራሪያ እንዳስታወሱት፤ ከዚህ ቀደም በከተማ አስተዳደር ደረጃ ከዓለም ባንክ በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በተተገበረው ብቃት የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር ሂደት ውስጥ በርካታ ልምድና ተሞክሮዎች ተገኝተዋል። ለምሳሌ፤ ድርጅቶች የሚቀርቡላቸው የብቃት የሥራ ላይ ተለማማጅ ወጣቶች በሥራ ላይ ያላቸውን ሙያዊ ብቃት እና ውጤታማነት በማየት የተለያየ የማበረታቻ ተጠቃሚ ያደርጓቸዋል። ተጨባጭ ክህሎትና ዕውቀት እየያዙ በዚህ ሂደት ውስጥ ማለፋቸው አብዛኛው በሚባል ደረጃ በአራት ወር ውስጥ ብቁ ሠራተኛ ሆነው ከድርጅቶች ጋር በቋሚነት ለመሥራት የሚያስችል ውል እስከ መፈራረም ይደርሳሉ፡፡ በአራት ወራት ቆይታቸው ብቻ በወር እስከ 10 ሺህ ብር ገቢ ማግኘት የቻሉ ብዙዎች ናቸው፡፡ ወርሃዊ ደምወዝ ከ30 ሺህ ብር በላይ በሚያስገኝ ሥራ ላይ ተቀጥረው የሚሠሩም አሉ፡፡

በራስ አቅም ተግባራዊ መደረግ በጀመረው የብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር ላይ ስለሚከናወኑ መሰረታዊ ተግባራት በተመለከተ አቶ ሰብሀዲን ሲያብራሩ፤ "ወጣቶቹ በመርሃ ግብሩ ታቅፈው ለስድስት ወራት በሥራ ላይ ልምምድ ቆይታ ሲያደርጉ፤ ሙያን ብቻ አይደለም የሚቀስሙት፡፡ የሥራ ስነ ምግባርን በተግባር ይለማመዳሉ፡፡ የእርስ በእርስ የአቻ የሥራ ላይ ውይይት ቢያንስ በየወሩ ያደርጋሉ፡፡ የአቻ ለአቻ ውይይት እና ምክክሩ በእነዚህ ድርጅቶች ውስጥ ባሉ የሥራ ላይ ተለማማጅ ወጣቶች ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ በተለያየ ድርጅት ውስጥ ያሉ ወጣቶች በጋራ ተገናኝተው ልምድና ተሞክሯቸውን እንዲለዋወጡ ይደረጋል፡፡

ወጣቶቹ የስድስት ወራት የሥራ ላይ ልምምድን በብቃት አጠናቅቀው ሲመረቁ ለቀጣይ ሥራቸው ማስረጃ ሆኖ የሚያገለግላቸው ሦስት ዓይነት የምስክር ወረቀት (ሰርተፊኬት) ይሰጣቸዋል። የመጀመሪያው የምስክር ወረቀት የሕይወት ክህሎት ስልጠና መውሰዳቸውን የሚያረጋግጥ ሲሆን፤ ሁለተኛው መሠረታዊ የኮምፒዩተር ስልጠና መውሰዳቸውን የሚገልፅ ነው። ዋናውና ሦስተኛው ደግሞ የሥራ ላይ ልምምድ ያደረጉበት ተቋም ወይም ድርጅት የሚሰጣቸው የስድስት ወር የሥራ ላይ ልምድ(experience) ነው። በዕውቀት፣ በክህሎት፣ በሥራ ስነ ምግባር፣ በአስተሳሰብ ለውጥ ያሳዩት እነዚህ ወጣቶች በመጨረሻ የተቀበሏቸውን የምስክር ወረቀቶች ይዘው ልምምድ ባደረጉበት ድርጅት መቀጠር፣ ሌላ ድርጅት ፈልገው ተወዳድረው መግባት፣ በግላቸው ወይም በመደራጀት የራሳቸውን ሥራ መጀመር ይችላሉ" ብለዋል፡፡

# ማስታወቂያ

## በአዲስ አበባ ከተማ የሲኒማ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት የኪራይ ጨረታ ማስታወቂያ

የአዲስ አበባ ከተማ ሲኒማ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት በልደታ ክ/ከተማ፣ በወረዳ 7፣ ሰንጋተራ አካባቢ አዲስ ሲኒማ ማዕከል ለልዩ ልዩ አገልግሎት መዋል የሚችሉ ክፍት ቦታዎችን ለኪራይ አገልግሎት አዘጋጅቷል።

በኪራይ አገልግሎት መጫረት ለሚፈልጉ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ነጥቦች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡

1. የተጫራቾችን ማንነትን መግለጽ የሚችል መረጃ ለማቅረብ ፈቃደኛ መሆን ይገባቸዋል፣
2. ተጫራቶች የድርጅቱን አሠራርና የውል አግባብ መርህን ለመፈፀም መስማማት የሚችሉ መሆን አለባቸው፣
3. ተጫራቾች ይህ የኪራይ ጨረታ ማስታወቂያ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ በአዲስ ሲኒማ ማዕከል ህንፃ 7ኛ ወለል ላይ በመገኘት የማይመለስ ብር 500(አምስት መቶ ብር) በመክፈል የዋጋ ማቅረቢያ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
4. ተጫራቾች መከራየት ለሚፈልጉት ቦታ /ክፍል/ የ1 ካሬ ሜትር ወይም ጠቅላላ ዋጋ በዋጋ ማቅረቢያ ሰነድ መሰረት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
5. ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ብር 20,000 (ሃያ ሺህ ብር) ለሲኒማ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት የታዘዘ ሲፒኦ) ከጨረታ ሰነዱ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡
6. ተጫራቾች ይህ የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን አንስቶ እስከ 1 ሳምንት በስራ ቀናት ውስጥ መግዛት ይችላሉ፡፡
7. ለኪራይ ጫረታ የቀረቡ ልዩ ልዩ ቦታዎችን በተመለከተ በጨረታ የሽያጭ ሰነድ ውስጥ በዝርዝር ተመላክቷል፣
8. መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ለተጨማሪ መረጃ አዲስ ሲኒማ ማዕከል ሰንጋተራ ዮቤክ ህንፃ 40/60 ኮንዶሚኒየም አጠገብ ይገኛል። በስልክ ቁጥር ላይ 0986687882 በመደወል መጠየቅ ይቻላል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሲኒማ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት**

---

አደይ አበባ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በቀን 22/4/2018 ዓ.ም የካርታ ቁጥር ለ/ኩራ/2/52/2/65436/026819/00 የሴሪ ቁጥር 1646114 የተሰጠበት ቀን 10/10/2015 ዓ.ም ወረዳ 02 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በእኛ ተቋም የተሰጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡
ይሁንና ከላይ የተጠቀሰው ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የጠፋ ስለሆነ ካርታውን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ20 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቀን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ አዘጋጅተን የምንሰጥ ስለሆነ ሀላፊነት የምንወስድ ይሆናል፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

እጅጋየሁ አለሙ ቼኬ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ካርታ ቁጥር ጂ.አይ.ኤስ.ቦሌ01/363/156-7494/00 ሴሪ ቁጥር 126690 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸው ምክንያት አግኝቸዋለው የሚል አካል ማስታወቅያው ከወጣበት ቀን እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ/ሰርተፍኬት/ እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 01 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000090103285 ሴሪ ቁጥር R 090665 የሆነው በአቶ አየነው ሁነኛው አለሙ ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት /ካርታ/ የጠፋባቸው መሆኑን ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ90 (ዘጠና) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ቦ/አያ/108/1948/01 ሴሪ ቁጥር 005062 በወ/ሮ መሠረት ስሜ ከበደ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የኮንደሚንየም እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

በወ/ሮ ጤናዬ መኩሪያ አሸንጌ ስም የተመዘገበ ይዞታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 የይዞታ ካርታ ቁጥር ኮ/ቀ/የማ/ን/መ/390/20670/01 ሴሪ ቁጥር 062042 የጠፋባቸው መሆኑን በ16/04/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ቦሌ15/3/9/109559/00 ሴሪ ቁጥር 0687077 ሜቲ ሁንዴ ሆርዶፋ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቤት እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በዳንኤል ለማ ሁምኔሳ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከ/ወረዳ 06 የሚገኘው የይዞታ/የቤቱ/ ልዩ መለያ /ካርታ/ ቁጥር AA000080600167200421 ሴሪ ቁጥር 052926 በጽ/ቤታችን በስማቸው የተመዘገበ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት/ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝታችሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ፀጋዬ ብሩ ዘለለው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 01 የካርታ ቁጥር ቦሌ1/22/4/5/1796/250683/01 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት /ካርታ/ እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በያሲን ኡመር ሁሴን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከ/ወረዳ 14 የሚገኘው የይዞታ/የቤቱ/ ልዩ መለያ /ካርታ/ ቁጥር AA00008011959l ሴሪ ቁጥር 0224987 በጽ/ቤታችን በስማቸው የተመዘገበ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት /ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝታችሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

የአቶ ሰባህ አብደላ ኑርጌታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 06 የካርታ ቁጥር ለ/ኩ/3/9/3/17/142320/00 የሆነው ሰርተፍኬት ተመዝግቦ የሚገኘው በቤት ባለቤትነት ካርታ በሴሪ ቁጥር 1659819 ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግንቼዋለሁ የሚል ግለሰብም ይሆን ሌላ አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረበ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት /ካርታ/ ተዘጋጅቶ እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የለሚ ኩራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በፍሊንትስቶን ኢንጂነሪንግ አክ/ማህ ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ቦሌ9/51/7/11/40310/116226/01 የሴሪ ቁጥር 1491916 የተሰጠበት ቀን 24/02/2012 የቤቱ ስፋት በሰነድ 103.28 ሜ.ካ በሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በእኛ ተቋም የተሰጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ይሁንና በፍሊንትስቶን ኢንጂነሪንግ አክ/ማህ ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ቦሌ9/51/7/11/40310/116226/01 የሴሪ ቁጥር 1491916 የተሰጠበት ቀን 24/02/2012 የቤቱ ስፋት በሰነድ 103.28 ሜ.ካ በሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ከእጃቸው የጠፋ ስለሆነ ቤቶን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ማህደሩን የምናደራጅ እና ሀላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የለሚ ኩራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ኤም ኤፍ ኤ አስመጪና ላኪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000060402807 ሴሪ ቁጥር L 0122589 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ የመሬት ይዞታ የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በቂርቆስ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 20 ቀበሌ 40 በአዲሱ ወረዳ 04 የቤት ቁጥር 019 በካርታ ቁጥር 33277 በአቶ ደምስስ ዬርዳኖስ ስም የሚገኘው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ካለ በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማት አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ይዞ እንዲቀርብ እየጠየቅን ይዤዋለሁ የሚል ከሌለ በምትኩ ሌላ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቂርቆስ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት**

---

በሻለቃ ተስፋዬ አለሙ ወልደተንሳይ ስም የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000080101863100319 የሆነው የካርታ ሴሪ ቁጥር C 089138 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 01 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋ በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ተለዋጭ ሰርተፊኬት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ አሊ ይማም ኢብሬ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 02 የሚገኘው የይዞታ የይዞታ መለያ ቁጥር AA00008020361l በሴሪ ቁጥሩ 0124972 በስማቸው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ወ/ሮ/ወ/ት ሀይሉ ተካ በየካ ክ/ከተማ በቀድሞ ወረዳ 12 ቀበሌ 11 ወይም አዲሱ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር 1155 የካርታ ቁጥር የካ/209317/10 ሴሪ ቁጥር 048737 ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለው የሚል ካለ እስከ 20 ቀን ድረስ አዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ግን በምትኩ ሌላ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የየካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቶ መሀሪ ብርሀነ አምባዬ ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ቦሌ8/20/1/4/10170/24231/01 የሴሪ ቁጥር 1466615 የተሰጠበት ቀን 16/5/2011 የቤቱ ስፋት በሰነድ 51 ሜ.ካ በሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በእኛ ተቋም የተሰጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ይሁንና በአቶ መሀሪ ብርሀነ አምባዬ ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ቦሌ8/20/1/4/10170/24231/01 የሴሪ ቁጥር 1466615 የተሰጠበት ቀን 16/5/2011 የቤቱ ስፋት በሰነድ 51 ሜ.ካ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ከእጃቸው የጠፋ ስለሆነ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የምናዘጋጅ እና ሀላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ /ወ/ሮ/ሪት ፀሀይ አበራ ደመናው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000061207285820109 ሴሪ ቁጥር C 277542 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በወ/ሮ ወርቅነሽ ተፈራ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 ክልል ውስጥ የሚገኝ ይዞታ ካርታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 01135 ሴሪ ቁጥር 0645627 የይዞታ ስፋት 404 ካ.ሜ የሆነ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን ከፖሊስ ማስመዝገባቸውን በቁጥር ወ/መ/10/13264/18 በቀን 20/04/18 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በተገለፀልን መሰረት ወጪውን ግለሰቡ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅላቸው እየገለጽን በማንኛውም ምክንያት የጠፋው ካርታ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ እስከ 30 ተከታታይ የስራ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ካላቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በክብሮም አምለሶም ተስፋልደት እና ኢማና መሐመድኑር አለዲን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 05 የሚገኘው በይዞታ ካርታ ቁጥር AA000080504491 በሴሪ ቁጥሩ 0171964 በስማቸው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# የባህል ስፖርቶች አስታዋሽ እያገኙ ይሆን?

**በሳህሉ ብርሃኑ**



ፎቶ- ከገፀ ድር

ባህላዊ ስፖርቶችን የበለጠ በማልማት፣ በማሳደግና በማስተዋወቅ በዓለም አቀፍ መድረኮችም ጭምር የሚዘወተሩ እንዲሆኑ ማስቻል ይገባል

ማህበረሰቡ እንደየአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ የአካል ብቃቱን የሚያዳብርባቸው፣ የተዳከመ አዕምሮውን የሚያፍታታባቸው፣ የዛለ አካሉን የሚያነቃቃባቸው፣ በትርፍ ጊዜው እና በበዓላት ቀን ማኅበራዊ ግንኙነቱን የሚያጠናክርባቸው ሀገር በቀል እውቀቶች ውጤት የሆኑ የባህል ስፖርቶች አሉት። እንደ ገና፣ የጥምቀትና መሰል በዓላት ደግሞ ከኃይማኖታዊ ይዘታቸው ባሻገር የማህበራዊ ትስስር መገለጫ የሆኑት ባህላዊ ስፖርታዊ ሁነቶች ጎላ ብለው የሚታዩባቸው ናቸው።

የባህል ስፖርቶችና ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲተዋወቁ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ በተለይም የገና ጨዋታ እና የፈረስ ጉግስ በከተማዋ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ቦታ አላቸው። ሆኖም ስፖርቶቹ በየዓመቱ በወጥነት ይካሄዳሉ ወይ? ባህላዊ ስፖርቶቹን ዘወትራዊ ለማድረግ ምን አይነት ስራዎች ሊሰሩ ይገባል? የሚሉና መሰል ጥያቄዎች በስፖርት ቤተሰቡ የሚነሱ ናቸው።

በዘመናዊው የፈረስ ጉግስ ላይ አተኩሮ የሚሰራው የኢትዮጵያ ፈረስ ስፖርት ማህበር ፅህፈት ቤት ኃለፊ አቶ ዘሪሁን ቢያድግልኝ ከዚህ ቀደም ለዝግጅ ክፍላችን በሰጡት አስተያየት ባህላዊ ስፖርቶች እንደ ዕድሜያቸው ማደግ ያልቻሉበትን ምክንያት አስረድተዋል፡፡ በቂ ውድድሮች ያለመኖር፣ የባለሙያ እጥረት መኖርና አዳጊዎች በትምህርት ቤቶች ስለስፖርቱ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያለመደረጉ ባህላዊ ስፖርቱ እየተጋፈጣቸው ያሉ ዋና ዋና ችግሮች ስለመሆናቸው ይገለጻል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ መረጃ መሰረት በአሁኑ ወቅት የከተማ አስተዳደሩ ባህላዊ ስፖርቶችን ከወቅታዊ ዝግጅት ባለፈ በቋሚ መዋቅር ለመምራት የሚያስችሉ ተግባራትን እየከወነ ይገኛል። በከተማ አስተዳደሩ በኩል ይህን ባህላዊ ስፖርቶችን ለማነቃቃት በየዓመቱ የገና ጨዋታ ውድድሮችን የማዘጋጀት ልምድ እየዳበረ መጥቷል። እንደ ጃንሜዳ ባሉ ትልልቅ ክፍት ቦታዎች ባህላዊ የገና ጨዋታ በደመቀ ሁኔታ እንዲካሄድ ድጋፍ ይደረጋል። የተለያዩ ክፍለ ከተሞች የሚሳተፉባቸው መሰል ውድድሮችም ይካሄዳሉ።

የባህል ስፖርቶች በዘፈቀደ ከመካሄድ ይልቅ በወጥነት እንዲመሩ ለማድረግ በርካታ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። ውድድሮቹ በህግና በደንብ እንዲመሩ፣ የዳኝነት ስልጠናዎች እንዲሰጡ እየተደረገ ነው። የባህል ስፖርቶች በየዓመቱ በተወሰነ ጊዜና ቦታ እንዲካሄዱ በማድረግ ህዝቡ አስቀድሞ እንዲያውቃቸው የማድረግ ስራዎች ተጀምረዋል።

> “የባህል ስፖርቶች ውድድሮችን ሂደት፣ ውጤትና ታሪክ በማህበራዊ ሚዲያዎች በማስተዋወቅ ቱሪስቶች በስፖርታዊ ዝግጅቶቹ ላይ ለመታደም እንዲመጡ ማድረግ ይገባል”

የባህል ስፖርቶች በወጥነት እንዲካሄዱ ለማድረግ ትልቁ እርምጃ የተወሰደው በስፖርት ማህበራት አደረጃጀት ላይ ነው። የአዲስ አበባ ባህላዊ ስፖርት ፌዴሬሽን አሁን ላይ በየክፍለ ከተማው ያሉ ክለቦችን በማደራጀት የገና ጨዋታ በውድድር መልክ እንዲካሄድ እያደረገ ነው። ይህ ቀደም ሲል በየሰፈሩ ይደረግ ከነበረው ይዘት ወጥቶ በዳኝነትና በደንብ እንዲመራ አድርጎታል። የከተማዋ ስፖርት ኮሚሽን በየዓመቱ ለበዓል ስፖርቶች የሚሆን በጀት በመመደብ፣ አሸናፊዎች የሚሸለሙበትና የሚበረታቱበትን ሥርዓት ስለመዘርጋቱ የፌዴሬሽኑ መረጃ ያሳያል።

አሁን ላይ እየተካሄደ ያለው 16ኛው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የባህል ስፖርቶች ውድድር እና ፌስቲቫልም ስፖርቱን በማሳደግ ረገድ ሚናው ከፍተኛ ነው፡፡ 'የባህል ስፖርቶች ተደራሽነት ለሀገር ማንሰራራት' በሚል መሪ ቃል በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ አስተናጋጅነት መካሄድ ጀምሯል። በማስጀመሪያ መርሃ ግብሩ ላይ የተገኙት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ በላይ ደጀን የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች መገለጫ የሆኑት የባህል ስፖርቶች አብሮነትን፣ ወንድማማችነትን እና እህትማማችነትን ለማጠናከርና ህብረብሔራዊ አንድነትን ለማጎልበት ሚናቸው የጎላ በመሆኑ ከትውልድ ወደ ትውልድ አጠናክሮ ማስቀጠል ይገባል ብለዋል።

የባህል ስፖርቶች ለዘመናዊ ስፖርት መነሻ ናቸው ያሉት አቶ በላይ በከተማ አስተዳደሩ በትምህርት ቤቶች የአዳጊ ወጣቶች የባህል ስፖርት የስልጠና ፕሮጀክቶች በመክፈት ተተኪ ስፖርተኞችን ለማፍራት ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል። የውድድሩ ዋና ዓላማም የከተማ አስተዳደሩን ወክለው በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚካሄዱ ሀገር አቀፍ የባህል ስፖርቶች ውድድር የሚሳተፉ ውጤታማ ስፖርተኞችን መምረጥ እንደሆነ የቢሮ ኃላፊው አሳውቀዋል።

በ12 የስፓርት አይነት በሚካሄደው ውድድር አስራ አንዱም ክፍለ ከተማ እንደሚሳተፉ የገለጹት የስፖርት ማህበራት ውድድር ማደራጃ ዳይሬክተሩ አቶ አያሌው ታደለ ምርጥ ስፖርተኞ ሐረሪ ብሔራዊ ክልል በሚያዘጋጀው ሀገር አቀፍ ውድድርና ፌስቲቫል የከተማ አስተዳደሩን ወክለው እንደሚሳተፉ አሳውቀዋል፡፡

በ16ኛው ከተማ አቀፍ የባህል ስፖርቶች ውድድርና ፌስቲቫል ላይ ከአስር ሺህ በላይ የስፓርት ልዑካን ይሳተፋሉ፤ ውድድሩ ከታህሳስ 18 እስከ 26 ቀን 2018 ዓ.ም እንደሚካሄድ ተመላክቷል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የባህል ስፖርቶች ፌዴሬሽን ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ፍቃደ ጫካ ከዚህ ቀደም ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት ባሕላዊ ስፖርቶች ለዘመናዊ ስፖርቶች መነሻ በመሆናቸው ታሪካዊ እሴቶቻቸውን በመጠበቅና በማስፋፋት ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ እየተሰራ ቢሆንም በቂ አይደለም ይላሉ፡፡ የባህል ስፖርቶች ለዘመናዊ ስፖርት መነሻ ቢሆንም እንዲያድጉና ዓለም አቀፍ እንዲሆኑ ከማድረግ አንጻር ቀሪ የቤት ስራ መኖሩንም ገልጸዋል።

ስፖርቶች እንዲያድጉ እና ከትውልድ ወደ ትውልድ ታሪካዊ እሴቶቻቸውን ጠብቀው እንዲተላለፉና ስፖርቱ ይበልጥ እንዲዘወተር ውድድሮችን መጨመር፣ የባህላዊ ስፖርቶች ጠንካራ የስፖንሰር መሰረት እንዲኖራቸው በማድረግ ላይ በትኩረት እንደሚሰራ እስካሁን የተሰራውም ስራ በቂ ባለመሆኑ በቀጣይ በትኩረት ይሰራባቸዋል ያሏቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በባህል ስፖርቱ ላይ ተማሪዎች እንዲሳተፉ በማድረግ ውድድሮች እንዳይቋረጡ ጥረቶች ይደረጋሉ፡፡ በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ የአሰልጣኞች ስልጠና እንዲያገኙ በትኩረት እንደሚሰራ አስረድተዋል፡፡ የባህላዊ ስፖርት በትኩረት ተሠርቶበት አንዱ የቱሪዝም ዘርፍ መሆን ይገባዋል የሚለውም ሌላኛው አስተያየታቸው ነው፡፡

በተለይ እንደ የፈረስ ስፖርት ያሉ ባህላዊ ስፖርቶች በተለያዩ ሀገራት በመዝናኛነት፣ ገቢ ማስገኛ እና የሚጎበኝ የቱሪዝም ዘርፍ እስከመሆን ደርሷል። በዓለም እንደሚዘወተረው ዘመናዊ አሠራርን የተከተለ ያልሆነውን የፈረስ ስፖርት ወደ ነበረበት ዝናው ለመመለስ የውድድር ዕድሎችን ማመቻቸት፣ ከዓለም አቀፍ የፈረስ ስፖርት ማህበራት ጋር ግንኙነት ማጠናከር፣ የባለሙያዎችን ቁጥር ለመጨመር ስልጠናዎችን በማዘጋጀት አስታዋሽ የሚፈልግ ስፖርት ነው፡፡

በእርግጥ በአዲስ አበባ ከተማ የባህል ስፖርቶችን በወጥነት ለማካሄድ የተጀመሩት ተቋማዊ ስራዎች ተስፋ ሰጪ ናቸው። ሆኖም ስፖርቶቹ ከባህል ትርዒትነት ባለፈ ራሳቸውን የቻሉ የኢኮኖሚና የቱሪዝም ዘርፍ እንዲሆኑ የባለድርሻ አካላት የተቀናጀ ጥረት የግድ ይላል የሚሉት ደግሞ የባህላዊ ስፖርቶችን በዳኝነት የሚመሩት አቶ ይልቃል ደምሴ ናቸው። የአዲስ አበባን የበዓል ስፖርቶች ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ የሚከተሉት ነጥቦች በትኩረት ሊሰሩባቸው ይገባልም ይላሉ፡፡

የገና ጨዋታን እንደ 'የኢትዮጵያ ሆኪ' ለዓለም በማስተዋወቅ የውጭ ቱሪስቶች በበዓል ወቅት ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ማድረግ። በየክፍለ ከተማው ያሉ የባህላዊ ስፖርት ክለቦች ቋሚ ማዘውተሪያና የገቢ ምንጭ እንዲኖራቸው ድጋፍ ማድረግ። የውድድሮችን ውጤትና ታሪክ በገፀ ድሮችና በማህበራዊ ሚዲያ በማስተዋወቅ ወጣቱ ስፖርቱን እንዲለምደው ማድረግ እንደሚገባ ባለሙያው ይመክራሉ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግብ የበዓል ስፖርቶችን ወደ 'ከተማዊ ፌስቲቫል' ማሳደግ ነው። ስፖርታዊ ውድድሮቹ ዓለም አቀፍ እውቅና እንዲያገኙ የገና ጨዋታን እና ሌሎች ባህላዊ ስፖርቶችን በዩኔስኮ (UNESCO) ለማስመዝገብ የሚደረገውን ጥረት ማገዝ ይገባል።

የውጭ ሀገር ጎብኚዎች በገና ወቅት አዲስ አበባ መጥተው እነዚህን ውድድሮች እንዲመለከቱ በማድረግ የከተማዋን ገቢ ማሳደግ በሁሉም ሰፈሮችና ትምህርት ቤቶች የበዓል ስፖርቶች የውድድር አካል እንዲሆኑ ማድረግ በቀጣይ በትኩረት ሊሰራባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ የባህል ስፖርቶች ፌዴሬሽን የባህል ስፖርቶች እንዲጎለብቱ ልዩ ትኩረት አድርጎ እየሰራ ሲሆን፣ ኢትዮጵያም ለመጀመሪያ ጊዜ የአፍሪካ የባህል ስፖርቶች ውድድር እና ፌስቲቫል እንድታዘጋጅ መመረጧ ይታወሳል።